መቅድም

ይህችን የመጀመሪያ ጽሑፌን፤ የእናትነት ጡቶቿን እያጠባች ላሳደገችን ቤተክርስቲያን ሳበረክት ሁሉን የፈጸመልኝን እግዚአብሔርን በማመስገን ነው። ምንም እንኳ በነገረ ቅዱሳን የሰፋ የዕውቀት አድማስ ባይኖረኝም ከተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍት በመጭመቅና ከአባቶቼ ሊቃውንት ያገኘሁትን በማስተባበር ይህችን ጽሑፌን በኦርቶዶክሳውያን ወገኖቼ ላይ መናፍቃን ከሚሰነዝሩባቸው የቃላት ጦር ጋሻ ትሁናቸሁ ብዬ አዘጋጅቻታለሁ።

የመጽሐፉን ርዕስ ንቅዓ ገነት ልላት የቻልኩት ስለ ሦስት አበይት ምስጢር ነው። አንደኛው ንቅዓ ገነት ማለት የገነት ምንጭ ማለት ሲሆን ይህችውም በምስጢር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት መኃ 4÷15 "አንቺ <u>የገነት ምንጭ</u> የሕየወት ውኃ ጉድጓድ ከሊባኖስም የሚፈስስ ወንዝ ነሽ"። እያለ ጠቢቡ ሰሎሞን ገና ከመወለዷ አስቀድሞ ውዳሴን ያጎርፍላት ነበር። በገነት ምንጭ በመኖሩ ገነት ለምልማ አብባና ደምቃ ትታያለች ድንግል ማርያም ባለችበት ሕይወት (ጎጆ) ውስጥ ልምላሜ ጽድቅ እንጂ ከጸጋ መራቆት አይኖርም። እርሷ ያለችበት ሕይወት በጸጋ እግዚአብሔር የተዋበ ነው። ከፍቅሯ ምንጭነት ጠልቆ የጠጣ ሁሉ ሕይወቱ በበረከቷ ይረሰርሳልና ምእመናን ይህችን ጽሑፍ ሲያነቧት የእናታቸው የድንግል ማርያም ፍቅር እየታወሳቸው እንዲያነቡ ስለፈለግሁ የመጽሐፉን ርዕስ የገነት ምንጭ ብያታለሁ እርሷም ድንግል ማርያም ናት።

ሁለተኛውም በዚች መጽሐፍ ሰፋ ያለው ምዕራፍ ስለ ቅዱሳን መላእክት ተልዕኮና አገልግሎት ሲሆን የቀረውም ስለ ጻድቃን ምልጃና የበረከታቸው ኃይል ምን ያህል ወደእኛ እንደሚዘንብልን አቅርቤዋለሁ። ገነት የጸጋ ምንጭ እንደመሆኗ በገነት ያሉ ጻድቃን፤ ቅዱሳን መላእክት ሁሉ ከምንጩ እንዴት እንደሚያጋሩን አትታለችና መጽሐፉን የገነት ምንጭ ብያታለሁ።

በሦስተኛው ትርጉም ገነት የእመቤታችን፣ በውስጧ ያለው ምንጭ የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። ከእውነተኛዋ ገነት ከድንግል ማርያም የተወለደው የሕይወት ምንጭ ክርስቶስ ዳግም በማያስጠማ ምንጭነቱ ዮሐ 4÷13-14 በወርቀ ደሙ ፈሳሽነት 5500 ዘመን በመርገም ደርቆ የነበረው ሕይወታችንን አለምልሞልናልና በመጽሐፉ የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር እንዲታሰብ ርዕሷን የገነት ምንጭ አልኳት።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከምንም በላይ የእኛነታችን መታወቂያ ሃይማኖታችን ነው። ሀገራችን በሰው ኃይል ሳይሆን በእግዚአብሔር ኃይል ተጠብቃ የኖረች የምትኖርም መሆኗ ታሪክ የማይረሳው የዘንተ ዓለም ትውስታ ነው። "ሃይማኖት የሌለው ሕዝብ ታሪኩ የተሟላ አይደለም"። ስለዚህም በሃይማኖታችን ብንኮራ እንጂ የምናፍርበት ነቁጥ የለንም። የቤተክርስቲያናችን ብርቅዬ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ "በወንጌል አላፍርም" ብሎን የለ? ሮሜ 1÷16 የሀገርም ሆነ የትውልድ ኩራቱ ሃይማኖት ነው። እግዚአብሔርን የምናስደስትበት ሀብታችን ነውና። ዕብ 11÷6 "ያለ እምነት (ሃይማኖት) እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም"። ካወቅንበት የታደልን ነን። ሃይማኖት የለሽ አይደለንምና። ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማወቅ ከሌሎች ሀገሮች ቀድመን ብንሰለፍ እንጂ በዚህ ኋላ ቀር አይደለንም። ስለዚህ ማንም ሰው ለኦርቶዶክሳዊያን ወንጌልን ልስበክላችሁ ሊለን አይችልም። "እናት ለልጇ ምጥ ማስተማር" ይሆናልና።
ልጅ ለእናቷ

ሃይማኖት ከክርስቶስ ኢየሱስ ምንጭነት ተቀድታ በሐዋርያት በኩል ለእኛ ደርሳለች። እኛ ደግሞ ከአባቶቻችን የተረከብነውን መንፈሳዊ ሀብት እንደ ዓይን ብሌን ጠብቀን ልንይዝ ይገባናል። የእኛ አባቶች ባህልን፣ ታሪክን፣ እውነተኛይቱን ሃይማኖት አቆይተውናል (አውርሰ ውናል)። ቅዱስ መጽሐፍ እንደሚለው አባቶቻችን ክብራችን ናቸው። ምሳ 17÷6 "የሽማግሌዎች አክሊል የልጅ ልጆች ናቸው። የልጆችም ክብር አባቶቻቸው ናቸው"። የዚህ ሁሉ ሀብት ተረካቢዎች የሆንን እኛ ደግሞ በሚገባ ሃይማኖትን ተጠቅመንበት ለመጭው ትውልድ ማውረስ ይጠበቅብናል። ይህን ባናደርግ ግን ተተኪውን ትውልድ ከጸጋ እግዚአብሔር ስላራቆትነው፤ በተጨማሪም የአባቶቹን ሀብት ኣላወረስነውምና እኛን በማመስገን ፈንታ እንደሚረግመን አንጠራጠር። እዳችን በዚህ ብቻ አያቆምም የአባቶቻችን የተጋድሎ አጽም እንደሚፋረደንም አንዘንጋ።

ዛሬ ትውልዱ የራሱ ባህል እየጠፋ ሲሄድ፣ በየገዳማቱ ቅርሱ ሲቃጠል፣ ሃይማኖቱ ሲደፈር፣ በቤተክርስቲያን ላይ መናፍቃን ሲዘምቱባት ትንኝ ያረፈችበት ያህል እንኳን የማይሰማው ከሆነ እርሱን የአባቶቹ ልጅ ነው ለማለት አንደፍርም። የሚገርመው ነገር በቤቱ የአንዲት መርፌ መጥፋት የሚከነክነው የቤተክርስቲያን በእርዮሳውያን መፈራረስ ደንታ የማይሰጠው ትውልድ መብቀሉ ነው። የራሱ ኑሮ

አይጉደል እንጂ ምን ቸገረው? እኔስ አባቶቼ በጣም ያሳዝኑኛል። ተተኪ ልጅ ባለማግኘታቸው።

አንባቢያን ሆይ እባካችሁ ያለኝ ይበቃኛልን አውቀን የቤተክርስቲያንን ችግር ችግራችን እናድርግ። ስሚቷ ይሰማን። ቤተክርስቲያን እናታችን አይደለችምን? በክርስቶስ ስም ልናምን ብቻ ሳይሆን መጠራታችን በስሙ መከራ ለመቀበል እንደሆነም አንርሳ እንጂ ፊል 1÷29 ዛሬ ቤተክርስቲያን ግዴታውን አውቆ እፎይታን ሳይናፍቅ የአብያተ ክርስቲያናት ሀሳብ እረፍት የሚነሳው ልጅ ትፈልጋለች። 2ኛ ቆሮ 11÷28። እናም ....

`<u>ሁሉም ኃላፊነት ይሰማው፤</u> የአባቶቻችንን ታሪክ ተርከን ብቻ አናቆምም። ክርስትና ታሪክ ብቻ ሳይሆን በተግባር የሚገለጽ ሕይወት ነውና። እኛም በሃይማኖት ጸንተን ዳግም ታሪክ ሰሪዎች መሆን ይጠበቅብናል። ያለጽናት ቅዱስ ጊዮርጊስ ሰባት ዓመት የተጋደለላትን የድል አክሊል ልንጠብቅ አይገባም። እናም የተጠራንለትን አላማ አውቀን፣ የወንጌልን ጫማ ተጫምተን፣ ልባችንን ለእግዚአብሔር አንበርክከን የአባቶቻችንን ዱካ በመከተል የሃይማኖት አርበኛ ልንሆን ይገባል። እውቀታችንንም ሆነ ጉልበታችንን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ካዋልነው እንደሚጠቀምብን አንጠራጠር።

<u>አጭር ማስገንዘቢያ</u>

መጸሐፍን ለኅትመት ማብቃት አድካሚና ፦ዕግስትን የሚፈትን ነው። ትውልዱ ሊረዳው የማይችለውን፣ በቋንቋ ተመቻችቶለት ሊያነበው የማይደፍረውን የቤተክርስቲያን ጻሕፍት ጨምቆ ትውልዱን በሚመጥን መልኩ ማቅረብ ፈታኝ ነው። እናም ቤተክርስቲያን ድንቅ የሆኑ ምስጢራትን ተሸክመው የተቀመጡ መጽሐፍቶቿን በሊቃውንቶቿ በኩል አስተርጉማ ለትውልድ ብታስረክብና ትውልዱም የምስጢርና የትርጓሜ ደሀ ከመሆን ድኖ በሃይማኖት እንዲጸና ቢደረግ ስል በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ። "ንባብ ይገድላል ትርጉም ግን ያድናል" ተብሎ የለ? በተጨማሪም ሊቃውንት አባቶቼ ያላቸውን መንፈሳዊ ዕውቀት ነገ ልናገኘው አንችልምና በጽሑፍ እንዲያወርሱንና ብዕራቸውን እንዲመዙ ስል አሁንም ደግሜ በታላቅ አክብሮት እጠይቃለሁ።

ከዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ተፈራ

<u>መግቢያ</u>

"እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ ይኑር ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘለዓለም ሕይወት ነው"። 1ኛ ዮሐ 2÷24

"የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና" ዕብ 3÷14 መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንደነገረን እኛ ኦርቶዶክሳውያን እስከ መጨረሻው ልንጸና ይገባል። የመንግሥቱም ተካፋዮች እንሆናለን። ዘመኑ ክፉና የሰዎች ህሊና የተከፋፈለበት ጊዜ ነው። እያንዳንዱ ሰው በግል ቤቱ ውስጥ የግል እምነቱን መፍጠር ብቻ እንጂ የቀረው እምነቶች (ፋብሪኬት) ሆነው እንደሚወጡ የምርት ውጤቶች በየጊዜው ሲፈለሰፉ የምናየው እውነታ ነው። በዚህ አንደነቅም ይህ ሊሆን ትንቢቱም ሊፈጸም ግድ ነውና። እኛ ግን የትንቢት መፈጸሚያ እንዳንሆን በተቀደሰች ሃይማኖት ሆነን ልባችንን እንጠብቅ። ይሁ 1÷8-21 "በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባቾች ይሆናሉ። እነዚህ የሚለያዩ ሥጋውያን የሆኑ መንፈስም የሌላቸው ሰዎች ናቸው። እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ ሃይማኖት ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስም እየጸለያችሁ ወደ ዘለዓለም ሕይወት የሚወስደውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ምህረት ስትጠባበቁ በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ"። በመጨረሻው ቀን አሳቾች እንጂ እውነቶች ይነሳሉ አልተባለም። ትውልዱ ግን እነርሱን እየተከተለ ፣ ሃይማኖቱንም እይካደ በጥፋት አረንቋ ውስጥ ተዘፍቆ ጉዞውን ወደ ገሀነም በር ተያይዞታል። 1ኛ ጢሞ 4÷1-2 "መንፈስ ግን በግልጽ በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች የሚያስቱ መናፍስትንና በውሸት ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንት ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ" ይላል።

ዓለምን የምናሸንፈው በሃይማኖት ነው ዮሐ 5÷4-5 "ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምን የሚያሸንፈውም እምነታችን (ሃይማኖታችን) ነው። ዮሐ 16÷33 "በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ ነገር ግን አይዞአችሁ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ"። አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዓለምን ድል ያደርግልናልና በሃይማኖት ስር ልንሰድ ያስፈልጋል። ቄላ 2÷6-7 "እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን

እንደተቀበላሁ በእርሱ ተመላለሱ፤ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ እንደተማራችሁትም በሃይማኖት ጽኑ ምስጋናም ይብዛላችሁ”።

የመጨረሻው ዘመን ሰዎች መሆናችንን አንርሳ። ዘመን አመጣሽ የኑፋቄ ጎርፍ እንዳይወስደን ነው ሥር መስደድ የሚያስፈልገን። “ስር የሰደደ ዛፍ አይወድቅምና” ሥር ካልሰደድን ግን የጎርፉ ተሸናፊዎች መሆናችን አይቀሬ ነው። ይህ ዛፍ ደግሞ መጨረሻው ተሰባብሮ መማገድ ነው። ስለዚህም እንደገዛ ምኞታቸው ሊነዱን አይገባም 2ኛ ጴጥ 3÷3 ‘በመጨረሻው ዘመን እንደራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባቾች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ”።

ሃይማኖት የሌለው እግዚአብሔርም የለውም ወልድ ዋህድ የምትለውን እውነተኛይቱን የሐዋርያት ትምህርት የማይቀበል ሁሉ እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ገንትን ያህል ቦታ አጥቷል። 1ኛዮሐ 1÷9-11 “ለሚመጣ ሁሉ በክርስቶስ ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም። በክርስቶስ ትምህርት የሚኖር አብና ወልድ አሉት ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና”።

ሃይማኖት ከቅዱሳን ህብረት ጋር ታስተሳስረናለች። ቲቶ 1÷4 “በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጁ ለሚሆን ቲቶ ...” እንዳለ የቅዱሳን ልጅ ለመሆን በሃይማኖት እንጽና። ሃይማኖት ለቅዱሳን አንድ ጊዜ የተሰጠች ነችና በቅዱሳን የሃይማኖት ተጋድሎ ውስጥ እንቁም። ይሁ 3 “ለቅዱሳን አንድ ጊዜ ስለተሰጠች ሃይማኖት እንድትጋደሉ እየመከርኳችሁ እጽፍላችኋለሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ”። እንዳለ የቅዱሳንን ሃይማኖት የምታስተምረንና በፍቅር ከእነርሱ ጋር ልታስተሳስረን የምትችል ነቅዓ ገነት እነሆ....

ምዕራፍ አንድ

ቅዱሳን መላእክት

መልአክ (መላእክት) የሚለው የቃሉን ትርጉም ያላወቀ ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ይሰናከላል። መላእክት የማይፈጽሙትን ግብር ስለእነሱ የተናገረ መስሎ ስለተቀመጠ ያልጠበቀው ንባብ ነውና አንባቢው በውስጡ ጥርጣሬና መረበሽ ይፈጠርበታል።

መላእክት ማለት 1ኛ. መልእክተኛ ተላላኪ፤ (ይህ ለቅዱሳን መላእክት የሚሰጥ ነው) የእርቅ መልእክተኞች ናቸውና።

2ኛ. አለቆች፤ገዢዎች (ይህ ትርጉም በስልጣን ኮርቻ ላይ ላሉ ሰዎችና ለቤተክርስቲያን አለቆች የሚሰጥ ነው።)

3ኛ. ሰይጣናት እራሳቸው፤ (የጥፋት መልእክ ተኞች ናቸውና መላእክት ይባላሉ)

ብዙዎች ይህ ትርጉም ስላልገባቸው ለሰይጣን የተጻፈውን በስመ መላእክት ለቅዱሳን መላእክት እየሰጡ ብዙዎችን ወደ ክህደት ሲነዷቸው ይታያሉ።

ሰይጣናት

ኢዮብ 4÷18 “እነሆ በባሪያዎቹ አይታመንም መላእክቱንም ስንፍና ይከሳቸዋል” ይላል። የትርጉም ደሀ የሆነ ሰው ይህንን ጥቅስ እየጠቀሰ ቅዱሳን መላእክትን ይሰድብበታል ነፍሱን በክህደት ነበልባል ይጠብሳታል። ነገር ግን ሳጥናኤልና ሠራዊቱ ለእግዚአብሔር ባርያ ሆነው ነበር የተፈጠሩት። ሹመትና ክብር ሲሹ ሊታመኑ አልቻሉምና በስንፍና ክህደት ለክስና ለዘለዓለም ፍርድ ተላልፈው ተሰጡ። አዎን ዛሬ እግዚአብሔር ቀድሞ ባሪያዎቹ ይሆኑ ዘንድ በፈጠራቸው በሰይጣንና በሠራዊቱ አይታመንም።

መላዕክቱን ስንፍና ይከሳቸዋል ሲል የጥፋት መልእክተኞች

አጋንንትን እንጂ ቅዱሳን መላእክትን አይደለም። ብዙዎች ስንፍና የሚከሳቸው መላእክትን ለምን አማልዱን እንላለን በማለት ራሳቸውን በአላዋቂነትና በጥፋት ጦር ሲወጉ ያሳዝናል። ነገር ግን ስንፍና ይከሳቸዋል ሲል ክህደታቸው ያስፈርድባቸዋል ለማለት እንደሆነ እንረዳ።

ማቴ 25÷41 "በዚያን ጊዜ በግራ ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን <u>ለሰይጣንና ለመላእክቱ</u> ወደተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ"። ጌታችን የሰይጣንን ሠራዊት <u>መላእክቱ</u> አላቸው። የጥፋት መልእክተኞች ናቸውና። ለጥፋት መላእክት የተነገረውን ለቅዱሳን መላእክት ሰጥቶ ስንፍና አለባቸው አያማልዱም እያሉ መናገር ያስጠይቃል።

2ኛ ጴጥ 2÷4 እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ገሀነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ ለፍርድ ሊጠብቁ አሳልፎ ከሰጣቸው ... ብሎ ሰይጣናትን መላእክት ይላቸዋል።

<u>አለቆች</u>

ሮሜ ~~1ኛ ቆሮ~~ 8÷38 "ሞትም ቢሆን ህይወትም ቢሆን፣ <u>መላእክትም ቢሆኑ</u>፣ ግዛትም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን፣ ኃይላትም ቢሆኑ ከፍታም ቢሆን ፣ ዝቅታም ቢሆን ልዩ ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል ተረድቼአለሁ።"

በደረቁ ካነበብነው መላእክት ከእግዚአብሔር ፍቅር እንደሚለዩ መስሎ ነው የተቀመጠው። "ንባብ ይገድላል ትርጉም ያድናል" ነውና መላእክትም ቢሆኑ ሲል ገዢዎችም፣ አለቆችም፣ አላውያን ነገሥታትም ቢሆኑ ከእግዚአብሔር ፍቅር አይለዩንም ሲል ነው። መላእክትማ ምን ብለው ከእግዚአብሔር ፍቅር ይለዩናል? እንዲያውም በፍቅሩ እንድንጸና ይማልዱልናል እንጂ ቅዱስ ጳውሎስ አላውያን ነገሥታት የመከራ ቀንበር ቢጭኑብትም ከክርስቶስ ፍቅር ፈቀቅ እንደማይል በጽናት ቆሞ ሲናገር ነው።

" መዝ 2÷2 "የምድር ነገሥታት ተነሱ አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሁ ላይ" በግዕዙ "ወተንስኡ ነገሥተ ምድር

<u>ወመላእክትኒ</u> ተጋብኡ ምስለሆሙ ህቡረ ላዕለ እግዚአብሔር ወላእለ መሲሑ"። በመሢሕ (በክርስቶስ) ላይ የተነሱት አለቆች የአይሁድ አለቆች እንጂ ቅዱሳን መላዕክት አይደሉም።

<u>መላእክት መቼ ለምንና እንዴት ተፈጠሩ?</u>

ቅዱሳን መላእክት በዕለተ እሁድ በወርሀ መጋቢት 29 ቀን በመጀመሪያው ሰዓት ተፈጥረዋል። ሲፈጥራቸውም "እምሀበ አልቦ ሀበቦ" ካለመኖር ወደመኖር አምጥቶ ፈጥሮአቸዋል። አፈጣጠራቸው እንደ ሰው በነቢብ (በመናገር) አይደለም። በአርምሞ (በዝምታ) ነው። ሊፈጥራቸው አሰበ ፈጠራቸውም። የተፈጠሩበት አላማ ሰውንና ቅዱስ እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው።

<u>የተፈጥሮአቸው ሁኔታ (ኩነቱ ተፈጥሮአቸው)</u>

ቅዱሳን መላእክት ኩነተ ተፈጥሮአቸው ኢ መዋትያን (የማይሞቱ) ናቸው። ዝንተ ዓለም በቅድስና ቆመው ሲያገለግሉ ይኖራሉ። "ፈጻምያነ ፈቃድ" ናቸው። የሰውንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሲፈጽሙ ይኖራሉ። "አልቦ ፍጻሜ ለመዋዕሊሆሙ" ለዘመናቸው ፍጻሜ አይነገርላቸውም (የላቸውም)።

ተፈጥሮአቸው ከእሳትና ከነፋስ ነው። መዝ 103÷4 ይህም ሲባል እሳትና ነፋስ ናቸው ማለት አይደለም።

እሳት ኃያል ነው። ቅዱሳን መላእክትንም ኃያላን አድርጎ እንደፈጠራቸው ለማጠየቅ ነው።

እሳት ብሩህ ነው ቅዱሳን መላእክትም ብሩሀነ አዕምሮ ናቸው።

ነፋስ ፈጣን ነው ቅዱሳን መላእክትም ፈጣን መሆናቸውን ሲያሳየን ነው።

ነፋስ ረቂቅ ነው ቅዱሳን መላእክትም የማይጨበጡና የማይዳሰሱ

ረቂቃን ናቸው።

አንድም ቅዱሳን መላእክትን በእሳትና በነፋስ ጠባይ መፍጠሩ በእነሱ ተፈጥሮ ውስጥ ባሕርዩን ሲናገር (ሲገልጽ) ነው። እሳት ውኃ ካልገደበው በቀር ያገኘውን ያጠፋል። እኔም ቸርነቴ ካልገደበኝ በቀር ሁሉን ማጥፋት የምችል ነኝ ሲል።

ነፋስ ፈታሂ (የሚለይ) ነው። ምርቱን ከግርዱ ይለየዋል። እኔም መናፍቃንን ከምእመናን፤ ኃጥአንን ከጻድቃን የምለይ ነኝ ሲል እግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክቱን ከእሳትና ከነፋስ ባህርይ ፈጥሮአቸዋል።

<u>የሰባቱ ሊቃነ መላእክት ሥልጣንና ተልዕኮ በመጽሐፍ ቅዱስ</u>

ቅዱሳን መላእክት አስር ከተማ ሲኖራቸው ሰባት ሊቃነ መላእክት ተሾመውላቸዋል። እግዚአብሔርም ፍጹም ክብሩንና አድህኖቱን ይገልጽባቸዋል። ሊቃነ መላእክት ለእግዚአብሔር ቅርብ ከመሆናቸው ባሻገር ልዩ ልዩ ሰማያዊ ስልጣን ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ተሰጥቷቸዋል። የመጀመሪያው የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ስመ ትርጓሜው "መኑ ከመ አምላክ" (ማን እንደ አምላክ) ማለት ነው። ስልጣናቸው በደረጃ እንደሚከተለው ነው።

1. <u>ቅዱስ ሚካኤል</u>

1.1. <u>አብጻሄ ምህረት</u>: (ምህረት አሰጪ) የእግዚአብሔርን ምህረት ወደ ሰው ልጆች የሚያደርስ ሩህሩህ መልአክ ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ የባርነት ቤት ወጥተው የምድር ጌጥ ወደሆነችው ከነአን በሚያመሩበት ጊዜ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ናቸውና ያለ ቀናቸው እንዳይቀሰፉ በአማላጅነቱና በምህረት አሰጭነቱ እየመራ ወደናፈቋት ሀገራቸው ያስገባ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ዘፀ 33÷1-3 "እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረ ሂድ ለአብረሃም ለይስሐቅ ለያዕቆብ ለዘርህ እሰጣታለሁ ብዬ ወደማልኩባት ምድር ወተተትና ማርም ወደምታፈስው ምድር አንተ ከግብጽ ምድር ካወጣኸው ህዝብ ጋር ከዚህም ውጣ አንገተ ደንዳና

ህዝብ ስለሆንህ በመንገድ ላይ እንዳላጠፋህ እኔ በአንተ መካከል አልወጣምና <u>በፊትህ መልአክን</u> እሰዳለሁ"።

ዛሬም ላለነው እስራኤል ዘነፍስ ክርስቲያኖች በክርስትና መንገዳችን ስንጓዝ በሚገጥመን የሀጢያት ገጠመኝ እንዳንጠፋ የዚህ መልአክ በአማላጅነቱ ከፊታችን መቆም አጅግ ያስፈል ገናል። ቅዳሴያ ችንም "ተውህቦ ምህረት ለሚካኤል" ለሚካኤል ምህረት ተሰጠው የሚለው ቅዱስ ሚካኤል ለሰው ልጆች ምህረትን ማድረስ የተሰጠው ሀብት በመሆኑ ነው።

1.2 <u>ነአዴ ጻድቅ</u> :- (ጽድቅን መካሪ) ህይወታቸው ለተመሰቃቀለባቸው በምክሩ የሚያስተካክልላቸው መልአክ ነው። ጋለሞታይቱ ፋርስ ባቢሎን በዘማዊነቷ ተዳድፋና ረክሳ የነቢያትን ደም እያፈሰሰች እግዚአሔርን ባስቆጣችው ወቅት የእግዚአብሔር ንጹሐን ሰዎች ከበደሏ እንዳይተባበሩና የጥፋቷን ጽዋ እንዳይጎነጩ ይመክ ራቸው የነበረ የጽድቅ መካሪ ቅዱስ ሚካኤል ነው። ራዕ18÷1-10 የተሰጠው ሹመት ሰዎችን በምክሩ ማጽናት ነውና። ነቢዩ ዳንኤል በሀገረ ባቢሎን ስደቱ በሃይማኖቱና በጽድቁ እንዲጸና የሚመክር ቅዱስ ሚካኤል እንደነበር እራሱ ዳንኤል መስክሯል። ዳን 10÷21

1:3 <u>መልአከ ምክሩ ለልዑል</u>:- እግዚአብሔር ልዑለ ባህርይና ሁሉን አዋቂ ስለሆነ በባህርዩ አማካሪ አያሻውም ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ቸርነት ድንበር ስለሌለው ለቅዱሳኑ ያለውን ፍቅር ሲገልጽ፤ የእነርሱን ሀሳብና ልመና ተቀብሎ በሥራ ላይ ያውለዋል። መዝ 88÷6-7 "እግዚአብሔርን በሰማይ የሚተካከለው ማን ነው? ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማንይመስለዋል? <u>በቅዱሳኑ ምክር</u> እግዚአብሔር ክቡር ነው።" ስለተባለ ከቅዱሳኑ ሁሉ ደግሞ ቅዱስ ሚካኤል የምክሩ አበጋዝ ሆኖ ተሹሟል። በቅዱስ ሚካኤል ልመና እግዚአብሔር ክቡር የሆነው የማዳኑ ሥራ ይገለጻል። እዚህ ላይ እራሳቸውን ለሚያመልኩና ትህትናን ለናቁ ሰዎች እግዚአብሔር እያስተማራቸው እንደሆነ እናስተ ውል። ብዙዎች ከሌላው ወንድማቸው ሀሳብ መቀበል ውርደት

ይመስላቸዋል። እግዚአብሔር ግን ለሠራው ሕጸጽ የሌለበት ጌታ ሲሆን ዝቅ ብሎ የቅዱሳኑን ሀሳብ መቀበሉ ትህትናውን ያስተ ምረናል።

1.4. <u>ተራድኦተ ሰብዕ</u> :-(ሰውን መርዳት) የአሦር ንጉሥ የሚሆን ሰናክሬም በሠራዊቱ ብዛትና ባቆመው ጣዖት ተመክቶ ኢየሩሳ ሌምን ከእግሩ ሥር ለማዋል ሰልፍ ወጣ። ክህነትን ከምስፍና ደርቦ የያዘ ሕዝቅያስ ወደ ፈጣሪው እንባውን አረጨ። ቅዱስ ሚካኤል እልፍ አዕላፋት መላእክትን አስከትሎ ደረሰለት። ሰናክሬም የተመካበትን መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ሠራዊት አራግፎ ለሕዝቅያስና ለወገኖቹ ድልን አጎናጽፎአቸዋል። "ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንምና" መዝ32÷16 ሕዝቅያስ ግን ያለቀሰበት አምላክ አላሳፈረውም 2ኛ ነገ 19÷35-37 መላእክት ለአድኅኖት የሚላኩ ቅዱሳን መናፍስት ናቸው ዕብ 1÷14 "ሁሉ <u>መዳንን ይወርሱ ዘንድ</u> ስላላቸው ለመርዳት የሚላኩ የሚያገ ለግሉም መናፍስት አይደሉምን?"ዛሬም በሰናክሬም ከሚመሰለው ከዲያቢሎስና ከሠራዊቱ ሊያድኑን በዙሪያችን እንደሚሰፍሩ በእምነት ልንቀበል ያስፈልጋል። መዝ 33÷7 "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ያድናቸውማል። እንደተባለው ኢያሱ ከተፋፋመ የጦርነት ዓለም ውስጥ ወጥቶ ከኢያሪኮ አጠገብ ተቀምጦ ሳለ ፍርሀቱን ሊያርቅለት፣ ጭንቀቱን ሊያረግብለት የመጣው ቅዱስ ሚካኤል ነው። ኢያ 5÷13-14 ቴዎድሮስና ገላውዲዮስ ከጠላቶቻቸው ከመክሰምያኖስና ከድማትያኖስ ጋር የሞት ትንቅንቅ በተያያዙበት ጊዜ የረዳቸውና ሰይፍንም የሰጣቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው። እርሱ በሰጣቸውም ሰይፍ ጠላትን አንበርክከውበታል። ቅዱስ ሚካኤል ወዳጆቹን መራዳት ልዩ ሀብቱ ነውና።

1.5. <u>መጋቢ ብሉይ</u>:- ቅዱስ ሚካኤል ለእስራኤላዊያን የጉዞአቸው መሪ ሆኖ በሕግ መጽሐፋዊ ከመግቦተ እስከ ተራዳኢነት ያገለገላቸው መልአክ ነው መዝ77÷24-25። "ይበሉም ዘንድ መና አዘነበላቸው ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው የመላእክትንም እንጀራ ሰው በላ" መላእክት እንጀራ የሚበሉ ሆነው ሳይሆን በመላእክት እጅ

የወረደውን እንጀራ (መና) ሰዋች ስለበሉ የመላእክት እንጀራ ሰው በላ ተባለ። ካወረደላቸው ዋነኛ መጋቢ ብሉይ ቅዱስ ሚኬኤል ነው።

1.6. <u>መገሰጸ ሰይጣን</u>:- ሊቀ ነቢያት ሙሴ አርብ ቀን እንደሚሞት ተነግሮት ነበር ይህችን ቀን ተጠንቅቆ ይጠብቃት እንጂ ብዙ አርብ ቀኖች ስለተፈራረቁበት ተዘናጋ። ሱርያል መልአከ ሞት ወደእርሱ መጣ "ሰላም ለከ አ ሙሴ ወልደ አንበረም"የእንበረም ልጅ ሙሴ ሰላም ላንተ ይሁን አለው። ሙሴም ይህችን ድምጽ ስለተጠራጠረ "መኑ አንተ" አንተ ማን ነህ? ቢለው "አነ ውእቱ መልአከ ሞት ዘፈነወኒ እግዚአብሔር ሀቤከ" እግዚአብሔር ወዳንተ የላከኝ መላእከ ሞት ነኝ አለው። ሞትን የማይፈራ የለምና "ሰላምከ ይግባ ላዕሌከ" ሰላምህ ወዳንተ ይመለስ ብሎ ከመልአኩ ተሰናበተ። ሙሴም ከእግዚአብሔር ቃል ፈቀቅ ማለቱን ስላልወ ደደ መልአኩን "በእግዚአብሔር ስልጣን ይዤሃለሁ እዚህ ጠብቀኝ" አለው ሄዶም ቤተሰቦቹን ተሰናብቶ ወደ ናባው ተራራ ወጣ። መላእክት በአምሳለ አረጋውያን ሲቆፍሩ አገኛቸው። ምን ትቆፍራላችሁ? ቢላቸው በመንደራችን አንድ ሰው ሞቶብን ልንቀብረው ነው አሉት። ሙሴም ልርዳችሁ ብሎ መቆፈሪ ያቸውን ተቀብሎ ቁፋሮውን ተያያዘው። ቆይቶም ጉድጓዱ እንዳይጠብ እንዳይሰፋም የምትቀብሩት ሰው ማንን ያህላል? አላቸው። ሁለንተናው አንተን ያህላል አሉት። ከሆነማ ገብቼ ልለካው ብሎ ጉድጓዱ ውስጥ ቢተኛ እንቅልፍ በዚያው መስጠው። ከመቅጽበት ነፍሱ ከሥጋው ተለየች። መላእክቱም በክብር ቀበሩት።

"ሙሴ ቢቀበር ታሪኩ አይቀበርም ዝንተ ዓለም ሲወሳ ይኖራል።" የሙሴን መቃብር እስራኤላውያን ሳያዩ በስውር መከናወኑ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው። ምክንያቱም የእስራኤል ልጆች ለሙሴ ያላቸው ፍቅር መጠን ስለሌለው በሙሴ መቃብር ላይ ሐውልት አቁመው "አምላካችን ሙሴ" እያሉ እንደሚ ያመልኩት እግዚአብሔር አስቀድሞ ስለሚያውቅ መቃብሩን ሰውሮባቸዋል። ሙሴ በሕይወተ ሥጋ እያለ እግዚአብሔር

በሙሴ ላይ አድሮ ይህንን ስራ በማለት ፈንታ ሙሴ ይህን
ስራ እያሉ ሊያመልኩት እንደደረሱ አይቶአቸዋልና፤ ወደ
ቃብሩ ሄደው ከአምልኮት ጠርዝ ወጥተው ከእግዚ.አብሔ
እንዳይጣሉ ሙሴም ከአማላጅነት ክብሩ ሌላ የእግዚ.አብሔር
ክብር ሰጥተውት ጸጋው እንዳይሸሸው የፈለገ ጌታ መቃብሩ
ሰውሮባቸዋል። ለጥፋት የሚፋጠን ሰይጣን የእስራኤን ልጆ
ቀስቅሶ የሙሴን መቃብር ሊያሳዩቸውና ከእግዚ.አብሔር ሊያ
ቸው ተነሳ። በዚህ ጊዜ ስለሙሴ የመቃብር ውስጥ ሥ
የመላእክት አለቃ ቅዱስ ሚካል ተከራከረ ይሁዳ 9 እግዚ.አብሔ
የሰወረውን ምስጢር አንተ ልትገልጸው አትችልም። ብ
መገሰጸ ሰይጣን ነውና ገሰጸው፣ አጠፋውም የሰይጣንም ዓላ
በአየር ላይ በኖ ቀረ። ዛሬም የጠላታችንን ዓላማ እንደ ጠ
ሊያበንልን የሚቆም ግሩም መልአክ እንደሆነ አንጠራጠር

1.7. <u>መሥዋዕት አሳራጊ</u>፦ የእስራኤል ልጆች የእግዚ.አብሔርን ክብ
ወደ ጎን ብለው በየማምለኪያ አጸዶቻቸው ኡሚምና ቱራፊ
ማምለክ ጀመሩ። በአምላክነቱ ቀናኢ የሆነው እግዚ.አብሔ
ለጠላት አሳልፎ ሰጣቸው። ለሰባት ዓመታት ያህል የምድያ
የባርነት ቀንበር ጀርባቸውን ሲያቆስለው ኖረ። ነፃነት የተጠ
እስራኤላውያን በደላቸው ያስከተለባቸው ሰቆቃ ውስጣቸው
በሀዘን ስለሰበረው የንስሐ እንባቸውን ወደእግዚ.አብሔር ፊን
ያለማቋረጥ ዓይኖቻቸው የዕንባ ምንጮች ሆኑ የሚደነቀው
ዛሬ እኛ ሰይጣን የሥጋ ፍላጎት ተሸናፊ (ባሪያ) አድ
ሕይወታችንን በሐጢአት እያቆሰልን በማልቀስ ፈንታ እንስቃለ
እንባቸውን የተመለከተ እግዚ.አብሔር ፊቱን ወደ እስራ
ላውያን መለሰ በአንዲት መጥመቂያ ዛፍ ስር ስንዴ ሲ
እራሱን በቅድስና ወስኖ የቆመውን ብላቴና ጌዴዮንን እግዚ
ብሔር መረጠው። እስራኤልን ከባርነት ነጻ ያወጣ ዘ
በመልአኩ አማካኝነት ጠራው። መልአኩ "አንተ ጽኑ ኃያል ሰ
እግዚ.አብሔር ከአንተ ጋር ነው" አለው። ጌዴዮን ማለት
ኃያል ብርቱ ማለት ነውና። መልአኩ ይህንን ብሎ እስራኤ
ነጻ እንዲያወጣ ነገረው። ጌዴዮን ግን "የእስራኤልን በ
ነጻ አወጣ ዘንድ እኔ ማን ነኝ" ብሎ እራሱን በትህትና ቀ

መልአኩም እርሱ እንደተመረጠ ደግሞ ነገረው። ጌዴዮንም እግዚ.አብሔር እኔን ለመምረጡ ምልክት አሳየኝ ብሎ የመጀመሪያውን ምልክት ከመልአኩ ጠየቀ። መልአኩም ፍቃደኛ ሆነለት ጌዴዮንም አለ "አንተም እስክመለስ ድረስ ቁርባንም

አምጥቼ እስካቀርብልህ እባክህ ከዚህ አትላወስ" አለው። መልአኩም እስክትመለስ ድረስ እቆይሃለሁ አለው. ጌዴዮንም ገባ። የፍየል ጠቦት፣ የኢፍ መስፈሪያ ዱቄት፣ የቂጣ እንጎቻ፣ ሥጋውንም በሌማት አኖረ። መረቁንም በምንቸት ውስጥ አደረገ። ሁሉንም ይዞ በአድባር ዛፍ አቀረበለት። የእግዚ.አብሔር መልአክ የሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ ወስደህ በዚህ ድንጋይ ላይ አኑር መረቁንም አፍስስ አለው። እንዲህ አደረገ <u>መልአኩም በእጁ ያለውን የበትሩን ጫፍ ዘርግቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ አስነካ እሳትም ከድንጋይ ውስጥ ወጥቶ ሥጋውንና የቂጣውን እንጎቻ በላ</u>። የእግዚ.አብሔር መልአክም ከዓይኑ ተሰወረ። መሳ 6÷11-21 መሥዋዕቱም በመልአኩ ምክንያት ዐረገለት ይህ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነው። መልአኩ መስዋዕት ማሳረግ የተሰጠው ሰማያዊ ጸጋ ነውና ምኩዝ በሆነ ተልእኮ ክህነት የጌዴዮንን መስዋዕት እንዳሳረገ የኛንም የጸሎታችንን፣ የምስጋናችንን ፣ የዝማሬያችንን፣ የአገልግሎታችንን መስዋዕት ሁሉ የሚያሳርግልን ድንቅ መልአክ ነው። በተለይም ቅዱስ ሚካኤል ሊቀመልአክ ከሰባቱ መንበላእተ ብርሃን(የብርሀን መጋረጃ) ደርሶ ችግራችንን በእግዚ.አብሔር ፊት ያቀርብልናል። የመናፍቃን ውድቀታቸው እዚህ ላይ ነው። መላእክት ከእግዚ.አብሔር ወደ ሰው ይላካሉ እንጂ ከሰው ወደ እግዚ.አብሔር ምንም አይነት ነገር ማሳረግ አይችሉም በማለት በድፍረት ይናገራሉ። "ቅዱስ መጽሐፍ ይዳኘን" ምነው የጊዴዮንን መስዋዕት መልአኩ ዐሳረገለት? ጌዴዮንስ መላእክት ከሰው ያለውን ነገር ሁሉ ወደ እግዚ.አብሔር የማያሳርጉ ከሆነ ስለምን መስዋዕትን በፊቱ አቀረበለት? እራሱ ጸልዩ አያሳርግም ነበር? መናፍቃን ለነዚህ ጥያቄዎቻችን መልስ ቢሰጡ ደስ ይለናል። እኛ ግን እንደ ጊዴዮን በመላእክት አማላጅነት በምትታመነዋ ቤተክርስቲያን ውስጥ ስላለን እግዚ.አብሔርን እናመሰግነዋለን።

ምሳሌና ምሥጢሩ

- ጌዴዎን የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ጌዴዎን መስዋዕት አቅርቦ ጠላቶቹ ምድያማውያንን ድል አድርጎ እስራኤልን ከባርነት ነፃ እንዳወጣቸው ክርስቶስም እራሱን ለመስዋዕት አቅርቦ አጋንንትን ድል አድርጎ ምእመናንን ከተያዙበት የሲኦል ባርነት ነፃ አውጥቷቸዋል።

- መልአኩ የያዘው ዘንግ የእርፈ መስቀል ምሳሌ ነው። መልአኩ መስዋዕቱን በእጁ እንዳልነካ በዘንግ ነክቶ እንዳሳረገው ዛሬም ዲያቆኑ ደመ መለኮትን ለመንካት ስልጣን እንደሌለው በእርፈ መስቀል ለማቀበሉ ምሳሌ ነው። (ካህናት ግን እለት እለት ይፈትቱታል) "ዘኢትገብረ ለመላእክት ተገብረ ለካህን" ለመላእክት ያልተገባ ለካህን ተገባ መባሉም ለዚሁ ነው።

- አንድም መልአኩ የያዘው የወርቅ በትር የሥልጣን እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። በትር ሁሉን እንደሚቀጠቅጥ ስልጣን እግዚአብሔርም ሁሉን ይገዛል። ሥልጣነ እግዚአብሔር የማይገዛው ፍጥረት የለምና።

- ዘንጉ የወርቅ መሆኑ ወርቅ ንጹህና ክቡር፣ጽሩይ ነው። ስልጣነ አግዚአብሔርም ንጹህ፣ክቡር ገናና ጽሩይ ለመሆኑ ምሳሌ ነው።

- እንድም መልአኩ በትር መያዙ ካህናት መስቀል ለመያዛቸው ምሳሌ ነው። በበትር የባብን ጭንቅላት ቀጥቅጠው እንደሚጥሉበት በመስቀልም ዲያቢሎስን ቀጥቅጠው ይጥሉታልና።

- እስራኤል የምእመናን ምሳሌ ናቸው። እስራኤልን ከባርነት እየመራ ያወጣቸው ጌዴዎን እንደሆነ ምእመናንንም የሲኦልን የብረት አጥር ሰብሮ ከባርነት ቤት፣ ከሲኦል በረት ያወጣቸው መድህነ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

- እሳቱ የኃይለ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው። እሳት በአግባቡ ከተጠቀሙበት እንደሚጠቅም በአግባቡ ካልያዙት እንደሚያጠፋ

ኃይለ እግዚአብሔርም ፈርተው ለሚጠጉት ያድናል። ከክፉም ይሰውራል። በአግባቡ ከአላመለኩትና ካልፈሩትም ያጠፋል።

- ሥጋው የሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

- መረቁ የደመ ወልደ እግዚአብሔር ምሳሌ ነው።

- መልአኩ የጌዴዎንን መስዋዕት ካሳረገለት በኋላ ከዐይኑ መሰወሩ መልአክት በረድኤት የማይለዩን ቢሆኑም ረቂቃን ፍጥረት መሆናቸውን የሚያስረዳን ምስጢር ነው።

2. ቅዱስ ገብርኤል

ገብርኤል ማለት ስመ ትርጓሜው አምላክ ወሰብ፣ እግዚእ ገብር (ገብረ እግዚእ)፣ አብሳሪ ትስብዕት ማለት ነው። ሥልጣኑም እንደሚከተለው ነው።

2.1. መልአከ መበስር

ሀ. የሐዲስ ዜና አብሳሪ ነው።

ለ. ሳጥናኤል እኔ ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ ፈጣሪያችን እስኪገለጽ ድረስ በያለንበት እንቁም ብሎ የእምነትን አቋም ያበሰረ ነው።

ሐ. አዳምና ሔዋን ጸጋቸውን ተገፈው በምድረ ፋይድ ወድቀው ሳለ ለአዳም አምላኪችሁ እግዚአብሔር ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ብሎሃል ብሎ የድኅነትን ተስፋ ያበሰራቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው።

መ. ሶምሶን ናዝራዊ እንዲሚሆን ፀጉሩንም እንዳይላጩት፣ የወይን ጠጅን እንዳይቀምስ ለአባቱ ለማኑሄ ያበሰረው ይኼው መልአክ ነው። መሳ 13÷4።

ሠ. ትፀንሺአለሽ ብሎ የአካላዊ ቃልን በተዋህዶ ሥጋ መሆን ለቅድስት ድንግል ማርያም ያበሰራት መልአክ ቅዱስ ገብርኤል ነው።

ረ. የመጥምቁ ዮሐንስን መወለድ በቤተ መቅደስ ለዘካርያስ

ያበሰረው ይሄው መልአክ ነው። ሉቃ 1÷13

ሸ. ለእረኞች ዓለምን በደሙ የሚዋጅ ጌታ በቤተ ልሄም እንደተወለደ አብስሮአቸዋል። ሉቃ 2÷9 እግዚአብሔርም ከመላእክት መካከል ቅዱስ ገብርኤልን መላኩ ከላይ እንደተገለጸው የስሙ ትርጓሜ የተዋህዶን ምስጢር ያዘለ በመሆኑ ነው።

2.2. መጋቢ ሐዲስ

ከሰማይ የወረደ መና፣ የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት፣ የሕይወት ምግብ ክርስቶስ በቤተ ልሔም እንደተወለደ መልአክ ዜና ነውና አብስሮናል። ሉቃ 2÷9-13። እነሆ የጌታ መልአክ ወደእነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ መልአኩም እንዲህ አላቸው። "እነሆ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምስራች እነግራችኋለሁ አትፍሩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኅን እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶ ላችኋልና።"

2.3 አይራጊ ጸሎት ወመስዋዕት

ጸሎትንና መስዋዕትን አሳራጊ፤ ጸሎትንና መስዋዕትን ከየስፍራው ከበረሃም፣ከዋሻም፣ከየቤታችንም፣ ከየቤተክርስ ቲያናቱ ተቀብሎ በአንድላይ ምኡዝ በሆነ እጣኑ የማሳረግ ስልጣን የተሰጠው ቅዱስ ገብርኤል ነው። ራእ 8÷3-5 "ሌላ መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ በመሰዊያው አጠገብ ቆሞ በዙፋኑ ፊት ባለው በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት እንዲጨምረው ብዙ እጣን ተሰጠው። የእጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።"

ጸሎት በመልአኩ እጅ ባለው ማእጠንት አማካኝነት በእግዚአብሔር ፊት ይደርሳል። የወጣኒውን እንደወጣኒነቱ፣ የማእከላዊውን እንደማእከላዊነቱ፣የፍጹሙን እንደፍጹምነቱ አስማምቶ አዕኳትያን ዘበሥጋ (በሥጋ የሚያመሰግኑትን)

ወዳስያን ዘበነፍስ (በነፍስ ረቂቅ ምስጋና የሚያመሰግኑትን) በአንድነት ከምኡዝ እጣኑ ጋር ያሳርጋል። ሉቃ1÷10 " በእጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ ውጪ ቆመው ይጸልዩ ነበር። የጌታ መልአክ በእጣኑ መሰዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ ፍርሀትም ወደቀበት መልአኩም እንዲህ አለው "ዘካሪያስ ሆይ ጸሎትህ ተሰምቶልሀል አትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ወንድ ልጅ ትወልድልሀለች።" የዘካሪያስን ጸሎት እራሱ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል እንዳሳረገለት ያውቃልና ጸሎትህ ተሰምቶልሀል ብሎ በመሰዊያው ቀኝ ቆሞ የጸሎቱን ማረግ የዮሐንስን መወለድ አበሰረው። በቀኝ መቆሙ በምህረት፣ በኃይል በአማላጅነት፣ በጽድቅ ቆሚልሃለሁ ሲለው ነው። አንድም ሰውን ሁሉ አስተምሮ ወደቀኝ የሚመልስ ልጅ ትወልዳለህ ሲለው፤ በቀኝ ቆሞ ለዘካሪያስ ታየው። መላእክት ቅኖችና የማናዊያን ናቸውና በቀኝ ይቆማሉ።

2.4. ነአዴ ጥበብ (ጥበብን አስተማሪ)

ቅዱስ ገብርኤል ጥበብን አስተማሪ የጥበብን ሚስጢር ገላጭ ሆኖ ተሹሟል። ይህ መልአክ ለነብዩ ለዳንኤል የጥበብንና የማስተዋልን ጸጋ በተሰጠው ስልጣን (ያጎናጸፈው) መልአክ ነው። ዳን 9÷20-22 "እኔም ገና ስናገር ስጸልይ በኃጢያቴና በህዝቤም በእስራኤል ኃጢያት ስናዘዝ በአምላኬም በእግዚአብሔር ፊት ስለተቀደሰው ስለ አምላኬ ተራራ ስለምን ገናም በጸሎት ስናገር አስቀድሜ በራእይ አይቼው የነበረው ሰው ገብርኤል እነሆ እየበረረ መጣ በማታም መስዋዕት ጊዜ ዳሰሰኝ አስተ ማረኝም ተናገረኝም እንዲህም አለ። "ዳንኤል ሆይ ጥበብንና ማስተዋልን አስጥህ ዘንድ አሁን መጥቻለሁ።"

... ጥበብና ማስተዋል የጎደለን የቅዱስ ገብርኤልን ወዳጅነት ጠበቅ አናድርግ በተሰጠው ጸጋ ማስተዋልን ለዳንኤል እንደሰ ጠው ለኛም ይሰጠናል። ብዙዎቻችን የእግዚአብሔር ቃል ምስጢር ተሰውሮብናልና። ዳን 8÷15-19

2.5. አቃቤ ገነት (የገነት ጠባቂ)

ቅዱስ ገብርኤል የገነት ጠባቂም ነው። ለሦስቱ የገነት በሮች ጠባቂ ቅዱሳን መልአክት ተመድበውላቸዋል። ምስራቃዊ የገነት በር ጠባቂ ቅዱስ ገብርኤል፣ ሰሜናዊ የገነት በር ጠባቂ ቅዱስ ዙጡኤል፣ ደቡባዊ የገነት በር ጠባቂ ቅዱስ ኢዮሩማኤል ናቸው። (ምንጭአክስማሮስ) "አዳም ከዕፀ ህይወት ወስዶ እንዳይበላ ወደ ህይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ ለመጠበቅ ኪሩቤልንና የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍን በኤደን ገነት ምሥራቅ አስቀመጠ።" ይላል ዘፍ 3÷24። ገነትን ለመጠበቅ ከታዘዙት መላእክት አንዱ ቅዱስ ገብርኤል ሲሆን በኤደን ገነት ምሥራቅ በር የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ ይዞ የቆመውም እርሱ ነው። አቃቤ ገነት (የገነት ጠባቂ) ነውና።

3. ቅዱስ ሩፋኤል

3.1. መልአከ ጥኢና ወሰላም (የሰላምና የጤና መለአክ)

ቅዱስ ሩፋኤል የሰላምና የጤና መልአክ ነው። በሰው ልጆች ጤንነት ላይ የተሾመ መንፈሳዊ ሐኪም ነው። በሰውነታችን ላይ የሚመጣውን ደዌም ሆነ ቁስል ይፈውስ ዘንድ ከልዑል እግዚአብሔር ስልጣን ተሰጥቶታል። መጽ ሄኖ 6÷3 "በሰው ቁስል ላይ የተሾመ ከከበሩ መላእክት አንዱ ቅዱስ ሩፋኤል ነው" ይላል። ለቆሰሉ ፈውስን ሊያስተላልፍላቸው ለማሕጸን ችግር ሁሉ ለሴቶች እረዳታቸው ቅዱስ ሩፋኤል ነው። ሴት በፀነሰች ወራት ቅዱስ ሩፋኤል አይለያትም ሕፃኑ አርባ ቀን ሞልቶት፣ በማሕፀን እያለ "ተስእሎተ መልክዕ" በሥላሴ አርአያ መልኩ መሳል ከጀመረበት ቀን አንስቶ ቅዱስ ሩፋኤል ሕፃኑ እስከሚወለድበት ጊዜ ድረስ አይለየውም። ሴቶች በወሊዳቸው ቀን ከሚደርስባቸው ጭንቀት ሰሙን ጠርተው ቢማጸኑት ጭንቀታቸውን ያቀላል ፈታሔ ማሕፀን ነውና።

ቅዱስ ሩፋኤል በሰውነት ያለን እረቂቅ እርኩስ መንፈስ

ያውቃል። አስማንድሮስ የተባለ ጋኔን በወለተ ራጉኤል ጭን ላይ አድሮ ባሎቿን እየገደለ ቢያሰቃያት በቅዱስ ሩፋኤል አማካኝነት እረቂቁን መንፈስ አስጨንቆ አስወጥቶታል። መ.ጦቢ.ት3÷8-17።

ሄኖ 3÷5 "ዳግመኛ እግዚአብሔር ሩፋኤል አዛዝኤልን እጁን እግሩን አስረህ በጨለማ ውስጥ አግዘው" ባለው መሠረት ለቃኤል ልጆች የምንዝር ጌጥ ማጌጥን፣ መቀንደብን ያስተማረ አዛዝኤል የተባለን ጋኔን በእሳት ሰይፍ እየቀጣ በረቂቅ አስሮና ወደ ጥልቁ የጣለ ይሄው መልአክ ነው። ሄኖ 2÷18።

የሰው ልጆች ከተያዙበት የኃጢአት ቁስል የፈውስ ዘንድ በአማላጅነቱና በጸሎቱ ፍቱን መልአክ ነው። ሄኖ 10÷13። "ሁለተኛም በበሽታ ሁሉ ላይ በሰው ልጆች ቁስል ላይ የተሾመ ቅዱስ ሩፋኤል ነው አሉኝ።" ተብሎ እንደተነገረ በኃጢአት የቆሰልን ሰዎች ስሙን ብንጠራ አናፍርም።

3.2. መልአከ ሰላም

ሰላም በራቀበት ሁሉ ሰላምን ለማቅረብ የታዘዘ መልአክ ቅዱስ ሩፋኤል ነው። ሰላም ደፍርሶባቸው ዛሬ በየቤቱና በየሀገሩ ልባቸው የጭንቀት ጎሬ የሆነ ጥቂቶች አይደሉም የቅዱስ ሩፋኤልን ወዳጅነት ጠበቅ ቢያደርጉት መልካም ነው።

4. ቅዱስ ዑራኤል

ዑራኤል ስመ ትርጓሜው ኦርያሬስ (የፀሐይ ብርሃን) ሲሆን ዑራኤል ደግሞ የብርሃን መልአክት ማለት ነው።ሄኖ26÷1።

4.1. አይራጌ ብርሃናት

:- ቅዱስ ዑራኤል በሰማያዊ ተልዕኮው በብርሃን፣ በመብረቅና በነጎድጋድ ላይ የተሾመ ግሩም መልአክ ነው። ለሄኖክ ብርሃናዊ ምስጢርን ገልጾለት የሥነ ፈለክን ነገር አሳይቶታል ቅዱስ ዑራኤል ፀሐይ በስንት ኬክሮስ መጥታ በስንት ኬክሮስ መጥለቅ እንዳለባት ሰዓትን እየመጠነ ብርሃናትን

በሰዓታቸው መመጠን ተሰጥቶታል።

በተጨማሪም መብረቅንና ነጎድጓድን እንዲቆጣጠር የተሾመ መልአክ ነው። ሄኖ 6÷2 "ብርሃንን በምን ያህል ኪክሮስ ወደሰው ልጆች እንደሚደርስ በብርሃን ዓመት እየለካ ለሄኖክ አስቀድሞ ያስተማረ (ያሳየው) ድንቅ መልአክ ነው። መ. ሄኖ 28÷13-19 "ከከበሩ መልአክ ዑራኤል ሁሉንም አሳየን ይሄውም ሁሉን የሚመራቸው ነው"። በመሆኑም ቤተ ክርስቲያናችን ለዘመናዊ ጥበብም ቢሆን ፋና ወጊ ነችና ደስ ሊለን ይገባል። ይህ ብቻ አይደለም የመዛግብተ በረድን፣ መዛግብተ ነፍሳትና መዛግብት ብርሃናትን እያዞረ በማሳየት አስተምሮታል። ሄኖ 26÷33-37።

እግዚአብሔር አመፀኞችን ሊቀጣ መብረቅና ነጎድጓድን ሊያመጣ ሲያስብ በብርሃናት ላይ ቦተሾመው በቅዱስ ዑራኤል በኩል ያዛል ዑራኤልም ለኃጢአተኛ የወረደ መቅሰፍት ለጻድቃን እንዳይተርፋቸው አድርጎ መብረቅና ነጎድጓድን በተፈለገው ቦታ የማድረስ ተልዕኮ ገንዘቡ ነው። በብርሃናት የተሾመ ነውና።

4.2. <u>ወሀቤ ጥበብ (ጥበብን ሰጪ)</u>

ቅዱስ ዑራኤል ለወዳጆቹ ጥበብን የመስጠት ሀብት ያለው ግሩም መልአክ ነው። ጥበብ ሰጪነቱም ከላይ እንዳየነው በሄኖክ ላይ በተጨማሪም በዕዝራ ላይ ተገልጾአል። በዕዝራ ጊዜ የኦሪት (የሙሴ) መጽሐፍት ወድመው ነበር። ዕዝራም ህይወትን ለቅድስና የሚያበቁና የሚገነቡ መጻሕፍት በመጥፋታቸው ልቡ በሀዘን ፈርሶ ዐይኖቹ የእንባ ምንጭ ሆነው ቀሩ። ዛሬ ቅርሶቻችን ሲዘረፉና ሲቃጠሉ የሚሰማን ስንቶች እንሆን? ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ የሆነ ጌታ ለዕዝራ ዑራኤል መልአክን ላከለት። ዑራኤልም የብርሃን ጽዋ ይዞለት መጣ አጠጣውም። በዚህ ጊዜ የጠፉ የመጻሕፍት ምስጢር ተገልጦለት ከጎኑ ባሉ ጸሐፍት አርባ ሌሊት አርባ መዓልት ሙሉ እየነገራቸው በማጻፍ የኦሪትን መጽሐፍ እነሆ ዛሬ ለእኛ አስተላልፈውልናል።

ይህ የሆነው በቅዱስ ዑራኤል ወሀቤ ጥበብነት (ጥበብ ሰጪነት) በዕዝራ ተቀባይነት መሆኑን እንዘንጋ መጽሐፍትን ስናነብ ከወዲሁ በቅዱስ ዑራኤል ምስጢር አቀባይነት በዕዝራ ተቀባይነት እኛ ጋ እንደደረሰ በማስተዋል ውለታቸውን አንርሳ።

ዕዝራም ከዚያ አንስቶ ሱቱኤል የተባለውን ቅጽል ስም አገኝቷል። ስትየ ጠጣ፣ ሱቱኤል የጠጣ ማለት ነው። የብርሃን ጽዋ ጠጥቷልና። ዛሬም የመጻሐፍት ምስጢር የተሰወረብን የማስተዋልና የጥበብ ድሆች የሆንን ሁሉ ወደእግዚአብሔርና ወደ ባለሟሉ ቅዱስ ዑራኤል ጠጋ ብለን ብንለምን መልካም ነው። የብዙዎች ልብ እውቀት በጥንቆላ ይገኛል ብሎ ያምናል። ለዚህ አስተሳሰብ ሥፍራ ሳንሰጠው ሥጋዊ ደማዊ ሰው ለኛ ምስጢር መግለጽ እንደማይችል አምነን ሕይወታችንን ለእግ ዚአብሔር ልንለይ ይገባል። ማቴ 16÷16 "የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ በሰማይ ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጸልህምና ብፁዕ ነህ"።

4.3. <u>ካህነ መስዋዕት</u>

ቅዱስ ዑራኤል <u>የመስዋዕት ካህን ነው።</u> ዛሬ ዲያቆኑ የመድኃኒታችንን ደመ መለኮት ይዞ እንደሚያቀብል ቅዱስ ዑራኤልም የዲቆንን አይነት አገልግሎት ያገለግላል። ለዕዝራ የብርሃን ጽዋ ይዞለት እንደመጣ ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን የዓለም መድኃኒት ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ቤዛነትን በፈጸመበት ጊዜ ከጌታችን የሚፈሰውን እውነተኛ ደመ መለኮትን ከአምስቱ ችንካሮች እየቀዳ በደመ ክርስቶስ ምድርን የቀደሰ የሕይወት መልአክ ዑራኤል ነው። ዛሬ የክርስቶስ ደም በነጠበበት ቦታ ላይ ቤተ ክርስቲያን ትሠራለች።

5. <u>ራጉኤል</u>

ራጉኤል ስመ ትርጓሜው መስተበቅል (የሚበቀል) ማለት ነው። አንድም ራጉ ኃያል ማለት ሲሆን ራጉኤል ማለት

ኃያል የኃያላን ኃያል እግዚአብሔር ማለት ነው። ራጉ - ጽኑዕ ኤል- እግዚአብሔር (ጽኑ እግዚአብሔር) ማለት ነው። የቅዱሳን መላእክት ስማቸው ለእግዚአብሔር ማንነት መግለጫ ነው። (እግዚአብሔር በሥነ ፍጥረቱ ይታወቃልና)።

5.1. ሳዳዬ አጋንንት (አጋንንትን አሳዳጅ)

"ዲያቢሎስን የሚበቀል አጋንንትንም የሚበቀላቸው ከከበሩ መላእክት አንዱ ራጉኤል ነው"። ሄኖ 6፥4

ሰይጣናት የሰው ልጆችን ሕይወት በጥልቁ ጨለማ ውስጥ ለማኖር የሚፋጠኑ ናቸውና። እነዚህን ክፉ መናፍስት ቅዱስ ራጉኤል ይበቀላቸው ዘንድ ተሹሟል። የሰው ልጅ ረቂቃን አጋንንትን በሥጋ ጠባይ መዋጋት አይችልም። እነርሱ ረቂቅ እኛ ግዙፍ ነንና በመሆኑም ረቂቃን ርኩሳን መናፍስትን በረቂቃን ቅዱሳን መላእክት እርዳታ ውስጥ ሆነን ማሸነፍ እንችላለን። ቅዱስ ሚካኤል ቅድስት አፎሚያን ከሰይጣን ክንድ እንዳላቀቃት፣ ትውልዱ ግን ይህን ማመን ተስኖታል። እኛ ግን ጠላት ፈተናን ሲያጸናብን ራጉኤልንና መሰሎቹን ቅዱሳን መላእክትን በአማላጅነታቸው እንማጸን። ቅዱሳን መላእክት አጋንንትን የገቡበት ገብተው ይበቀላሉና።

በተጨማሪም ቅዱስ ራጉኤል ሰላም ለራቃቸው ሰዎች ሰላምን የሚመላ የሰላም መልአክ ነው። አሁንም ሰላም የጠፋብን የመልአኩን ምልጃ ሙጥኝ እንበል።

5.2. መጋቢ ብርሃናት

ቅዱስ ራጉኤል በአገልግሎት ተልዕኮው ውስጥ ከቅዱስ ዑራኤል ጋር ህብረት አላቸው። ሁለቱም በብርሃናት ላይ የተሾሙ ናቸው። ራጉኤልም ብርሃናት ሰዓታቸውን መጥነው ለሰው ልጆች አገልግሎት እንዲውሉ ማድረግ ተሰጥቶታል።

ምንጭ አክሲማሮስ መጽሐፈ ምስጢር

6. ፋኑኤል

6.1 አቃቤ ጻድቃን :-(የጻድቃን ጠባቂ)

ቅዱስ ፋኑኦ ኤ መልአክ የጻድቃን ጠባቂ ነው። ቅዱሳን በሚገጥማቸው ፈተና ገጠመኝ ሁሉ አይርቃቸውም። ባህር ሆኖ የሚያሰጥማቸውን ፈተና መርከብ ሆኖ ያሻግራቸዋል። ተራራ ሆኖ ከፊታቸው የሚደቀነውን ፈተና ሜዳ ያደርግላቸዋል በድካማቸው አበርቺ መልአክ ነው። የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር እስራኤልን በቁጥጥር ስር አውሎ፤ ሰማርያን ከትሞ በያዘበት ወቅት የነቢዩ የኤልሳዕ ረድዕ (አገልጋይ) ግያዝ በጭንቀት ተዋጠ። ኤልሳዕንም ሆነ የእስራኤልን ልጆች ለማዳን ቅዱስ ፋኑኤል መልአክ እልፍ አእላፋት ሠራዊቱን አስከትሎ በከተማዋ ሰፈረ። የጠላትን ዓይን አጠፋ ለኤልሳዕም ሆነ ለእስራኤል ልጆች የድልን ዝናር በአንድ ምሽት አስታጥቆአቸው ከዐይናቸው ተሰወረ። 2ኛ ነገሥ 6፥14 ፋኑኤል መልአክ ፈተናን ያርቃል። ሰይጣን ከሚከፍተው ፍልሚያ ፈጥኖ ደራሽና ግንባር ቀደም በመሆን የእግዚአብሔርን ሰዎች ይታደጋቸዋል። ሰዳዴ ሰይጣናት ነውና። (ምንጭ አርኬ ዘታህሳስ3)።

6.2. መጋቢ

ሊቀ መልአክ ቅዱስ ፋኑኤል መጋቢ ነው። ነብየ እግዚአብሔር ኤልያስ ንጉሥ አክአብን ከንግሥቲቱ ከኤልዛቤል ጋር እያሳደዱ ሥፍራ ባሳጡት ጊዜ የአንድ ቀን የምድረ በዳ ጉዞውን ተጉዞ በክትክታ ዛፍ ስር እረፍት የናፈቀው ሰውነቱን አሳረፈ። ሰውነቱ በረሃብ ጠውልጎ ነበር። ዓለም ዙሪያውን የምትከፍትበትን የጦር ሾተል በመሸሸ ሰውነቱ በድካም ዛለ። የሰው ልጆችን ድካም ከሰማይ ዙፋኑ በፍቅር ዐይኖቹ የሚቃኝ እግዚአብሔር መጋቢ የሆነውን መልአክ ፋኑኤልን ላከለት። 1ኛ ነገ 19፥5-18 "በክትክታም ዛፍ በታች ተጋድሞ እንቅልፍም አንቀላፋ እነሆ የጌታም መልአክ ዳሰሰውና ተነስተህ ብላ አለው። ሲመለከትም እነሆ በራሱ አጠገብ የተጋገረ እንጎቻና በማሰሮ ውኃ አገኘ። በላም ጠጣም ተመልሶም ተኛ። የእግዚአብሔር

መልአክ ደግሞም ሁለተኛ ጊዜ መጥቶ ዳሰሰውና የምትሄድበት መንገድ እሩቅ ነውና ተነስተህ ብላ አለው። ተነስቶም በላ ጠጣም። በዚያ ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ።"

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በቤተ መቅደስ ስትኖር ሕብስተ አኮቴት ጽዋዐ በረከት እያወረደ ይመግባት የነበረ ቅዱስ መልአክ ቅዱስ ፋኑኤል ነው። ምንጭ (ድርሳነ በአታ፣ ታህሳስ ሦስት ስንክሳር)እመቤታችን በቤተ መቅደስ ኑሮዋ ተንከባካቢዎቿ ቅዱሳን መላእክት ነበሩ። "ድንግል ሆይ የሚያ ታልሉ ጎልማሶች ያረጋጉሽ አይደለሽም፤ የሰማይ መላእክት ጎበኙሽ እንጂ" እንዳለ አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም።

6.3. ካህነ ንስሐ

ሕይወት ፈተናዋ እልፍ ነው። በተለይም በክርስቲያን ሕይወት ላይ የማፅበሉ ነውጥ የፈተናው ብዛት ጥቂት አይደለም። ዛሬ እግዚአብሔርን በሚያስደስት ሕይወት ውስጥ ብንኖር ነገ በኃጢአት መውደቅና መሰባበርም ሊገጠመን ይችላል። የሁን እንጂ "ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜም ይነሳል" ምሳ24፥16 ተብሎ እንደተነገረው መውደቅ እንዳለ ሁሉ መነሳትም አለ። ስለዚህ ክርስቲያን ተስፋ አይቆርጥም ንስሐ ገብቶ የቅድስና ግብሩን ይጀምራል። ራዕ 2፥5።

በዚህ ጊዜ የሰው ልጆችን ንስሐ፣ ቀኖናቸውን ጭምር በአጠቃላይ ለኃጢአታቸው ስርየት የፈጸሙትን ድካም ተቀብሎ ወደ እግዚአብሔር በማሳረግና የእግዚአብሔርን ምህረቱንና ጸጋውን ንስሐ ለሚገቡ ሰዎች በማድረስ ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ላይ (በተነሣሕያን ላይ) የተሾመ ቅዱስ ፋኑኤል ነው። ሄኖክ 10፥15 "አራተኛውም የዘለዓለም ሕይወት የሚወርሱ ሰዎች ተስፋ ሲሆን ንስሐ በሚገቡ ሰዎች ላይ የተሾመ ፋኑኤል ነው"። አለኝ ብሎ ሄኖክ የፋኑኤልን ካህነ ንስሐነት አስረግጦልናል።

7. ሳቁኤል

ሳቁኤል ማለት ስመ ተርጓሚው

ዕብራይስጥ	ግዕዝ
ሳ.ስን	ስቡሀ
ቁ.ቆና	ቅሩብ
ኤል. እግዚአብሔር	

ስቡሀ፣ ቅሩብ እግዚአብሔር። በአማርኛው ምስጉን ለእግዚአብሔር የቀረበ ማለት ነው። ቅዱስ ሳቁኤል ሊቀ መላእክት ለእግዚአብሔር ቅርብ ነውና፤ የሰው ልጆችን ውስጣዊ ችግር ወደ ፈጣሪው የሚያቀርብ ግሩም መልአክ ነውና ቅሩብ እግዚአ ብሔር ተብሏል። (ፍኖተ ሕይወት ነው ሰዎችን ወደ ሕይወት መንገድ ይመራል) ምንጭ: መጽሐፈ ምስጢር

7.1. አዕራጌ ደመናት

ደመናትን በየመዛግብቶቻቸው የሚስይማቸው በደመናት ላይ ስልጣን የተሰጠው መልአክ ቅዱስ ሳቁኤል ነው። ሴርኤል እና ቴርኤል በተባሉ ቅዱሳን መላእክት አማካኝነት (አጋዥነት) አንዱ በወደል ጋዝ፣ ሌላው በነፋስ አውታር በበው ደመናትን ያመላልሳሉ ሳቁኤል በደመናት ላይ ኃይል ያለው፣ ደመናትን መስየም የተሰጠው ግሩም መልአክ ነው። መዝ 67፥34-37 "ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ ግርማው በእስራኤል ላይ ኃይሉም በደመናት ላይ ነው እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነውና"።

ኃይሉን በደመናት ላይ ለማድረግ እግዚአብሔር ፈቃዱ ሲሆን ቅዱስ ሳቁኤልን ለዚህ አገልግሎት ይጠቀምበታል።

በደብረ ታቦር አብ በደመና ሲገለጥ፣ በዮርዳኖስ አብ በደመና ሲገለጥ፣ ጌታችን በደመና አምድ ሲያርግ ደመናትን ያመላለሰና ያሳረገ አዕራጌ ደመና ቅዱስ ሳቁኤል ነው።

ሌላው በኪሩቤልና በሱራፌል መካከል ያለውን

መልዕክትየሚያመላልስ መልአከ ቅዱስ ሳቁኤል ነው።
ምንጭ: አክሲማሮስ፤ድርሳነ ባስልዮስ።

መላእክት በግብራዊ ተልእኮአቸው

ቅዱሳን መላእክት ለብዛታቸው ቁጥር አይገኝለትም። ኢዮብ 25÷3 "በውኑ ለሠራዊቶቹ ቁጥር አለውን?"

ቅዱሳን መላእክት ለእያንዳንዱ ፍጥረት ጥበቃ ይቆማሉ ከዋክብትን ሦስት አንድን ሰውን ሁለት ማቴ 18÷10 እያንዳንዱን ሥ ፍጥረት አንድ አንድ መላእክት ይጠብቁታል። ቅዱሳን መላእክት ዕጽዋት ነዶቀር ፍሬን እንዲሰጡ ይንከባከባሉ። ከወዲሁም ሰዎች እግዚአብሔርን ሲያሳዝኑ በትእዛዘ እግዚአብሔር እጽዋትንና ተክሉን በመምታት ፍሬ ነባ ሊያደርጉት ይችላሉ።

ቅዱሳን መላእክት በየነገዳቸው ግብራዊ ተልዕኮአቸውን እንደሚከተለው ይፈጽማሉ።

1ኛ) እሳታውያን ነገደ መላእክት

እነሂ ሀያ ሦስት (23) ነገድ ናቸው። ለእሳት ውስጥአገልግሎት በሲኦል ውስጥ በመላክ ታላቅ ሚና አላቸው። ሰዎች በእሳት ውስጥ ቢወድቁ ለአድኅኖት የሚላኩላቸው ከእሳታውያን ነገድ መላእክት ነው ቅዱስ ገብርኤል ነበልባል ውስጥ ሰለሦስቱ ደቂቅን እንደአዳነ። ዳን 3÷24-25

እሳታውያን ነገደ መላእክት በእሳታዊ ግርማቸው እጋንንት እየተረገጡ መንፀሬ ደይን ያወርዷቸዋል። ከጠላት እኛንም ያድኑናል ዕብ 1÷14 "ሁሉ መዳንን ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ ማናፍስት (መላእክት) አይደሉምን?"

2ኛ) መላእክተ መዓት

እኚህ አስራ ሁለት (12) ነገድ ናቸው። ማቴ 26÷51-53። ሰዎች በምድር ላይ የአመፃን ግንብ ሲገነቡ ፣ ሕይወታቸው በኃጢአት ድቅድቅ ጨለማ ሲዋጥ ፣ እነርሱነታቸው በኃጢአት ሲቆስል፣ ንስሐ አንገባም ብለው የእልከኝነትን ዝናር ሲታጠቁ ያን ጊዜ እግዚአብሔር ከትዕግስቱ በስተጀርባ ቅጣት አለውና ዓለሙን ለመቅጣት የሚልካቸው መላእክተ መዓትን ነው።

ፈርዖን በእስራኤል ልጆች ላይ የባርነት ቀንበርን ጭኖ ሲያስጨንቃቸው ሕዝበ እስራኤልን እንዲለቅ ከእግዚአብሔር ተነግሮት ነበር። እርሱም "መኑ ውእቱ እግዚአብሔር" እግዚአብሔር ማን ነው? "እስራኤልንም አለቅም እግዚአብሔርንም አላውቅም።" አለ በዚህ ጊዜ የግብጻውያንን የበኩር ልጅ ሁሉ ይቀስፍ ዘንድ እግዚአብሔር መላኩቱን ላከ። እኒህ መላእክት መላእክተ መዓት ናቸው። ዘፀ 12÷23

እስራኤል አምልኮተ እግአዘ.አሔርን ስተው እግዚአብሔርን በአምልኮቱ ባስቀኑት ጊዜ በሚያለቅሱትና ስለኃጢአታቸው በሚተክዙት ላይ የድህነት ምልክት በየግንባሮቻቸው ላይ ከጻፉ በኋላ የቀሩትን ሳይራሩ ከቤተ መቅደስ ጀምሮ እንዲቀስፉ መላእክተ መዓትን የላካቸው ጊዜ ነበር። ሕዝ 9÷1-8

ይህን ስላደረጉ መላእክተ መዓት ጨካኝ ናቸው ማለት አይደለም። ለምህረትም የሚላኩበት ጊዜ አለና። ይሁን እንጂ አገልግሎታቸው አመፀኞችን ለመቅጣት የሚላኩ ነገድ በመሆናቸው እንደጨካኝ አይታዩም። ፖሊስ ሥነ ሥርዓት ስላስከበረና ወንጀለኛውን ቢ.ግባቡ ስለቀጣ ጨካኝ እንደማይሰኝ እነርሱም እንዲሁ።

3ኛ) ብርሃናውያን ነገደ መላእክት

ብርሃናዊያን ነገደ መላእክት 53 (ሀምሳ ሦስት) ነገድ ናቸው። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ ያለ እግዚአብሔር ብርሃናዊ ክብሩን አጎናፅፎአቸዋል። ከመለኮቱ ጋር ያለው ብርሃናዊ ግርማ ለሞገሳቸው ልዩ ውበትና ክብር ሰጥቶአቸዋል። ራዕ 18÷1 "ከዚህ በኋላ ታላቅ ስልጣን ያለው ሌላ መልአክ

ሲወርድ አየሁ ከክብሩም የተነሳ ምድር በራች”

የአንድ መልአክ ክብረ ብርሀን ብቻ ምድርን ያበራታል። ዲያቢሎስ የጨለማ እርሱነቱን ይዞ ሊቀርበን በሚያኮበኩብበት ጊዜ በብርሀናዊ ገጻቸውና በነጸብራቃቸው ወግተው ይጥሉታልና።

በጨለማ ሐዘን ስንዋጥ ጨለማውን ገፈው በብርሀንነታቸው ይከቡናል። ትካዜን ከእኛ ያርቁልናል። ሉቃ 2÷9 ላይ እነሆ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታም ክብር በዙሪያቸው አበራ ታላቅ ፍርሀትም ፈሩ” ራዕ 10÷1-3

(የጌታም ክብር) በመላእክት ላይ የእግዚአብሔር ክብር አለና። በላያቸው ካለው ክብር የተነሳ ግርማቸው ልዩ ነው። መላእክትን መንቀፍ ማለት በእነርሱ ላይ ያለውን የእግዚአብሔር ክብር መሳደብ ስለሆነ የቅዱሳን ተቃዋሚዎች ሊያስቡበት ይገባል።

4ኛ) መላእክተ ጽልመት

መላእክተ ጽልመት 12 (አስራ ሁለት) ሲሆኑ ለእግዚአብሔር እጅግ ቀናዒያን ናቸው። “ቀናዒያን እሙንቱ እለይነክንክዎሙ ለነፍሳተ ኃጥኣን” እንዲል አክሲማሮስ ከቀናዒነታቸውም የተነሳ ሰዎች ልዑል እግዚአብሔርን ሲያስቆጡ ትካዜአቸው ለየት ያለ ነው። የኃጥእ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ተቀብለው የሚቀጡና ለኢጋንንት የሚያስረክቡ እኒህ ናቸው።

ከመላእክተ ጽልመት ውስጥ ከመሬት በታች ያለውን የበርባሮስን ክፍል ለመጠበቅ የተሾሙ አሉ። ለአገልግሎት መሬትን ሰንጥቀው “ሀራንኮስ” ከዚያም አልፈው “ዱዳሌሽ” እስከ እንጦሮጦስ ድረስ በመግባት ተልዕኮአቸውን ፈጽመው ይመጣሉ።

በተጨማሪም አገልግሎታቸው ወደ እምነት ያልመጡትን ያልተጠመቁትን ሰዎች መጠበቅ ነው። ያላመነ ሰው እንዴት መላእክት ለጥበቃ ይታዘዙለታል የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል። ይሁን እንጃ እግዚአብሔር ለፍቅሩ ድንበር ለቸርነቱም ወሰን አናገኝለትም (ከመኢየኑ ዘእንበለ ጊዜሆሙ) እንዲል ያላመኑ ሰዎችም ቢሆኑ ነስሐ

ሳይገቡ እና ወደ እምነት ሳይመጡ ያለ ጊዜአቸው በሞት እንዳይቀጠፉ የማይፈቅድ እግዚአብሔር ጠባቂ መላእክትን አቁሞላቸዋል።

ከእምነት የወጡ ሰዎችን በመላእክተ ጽልመት እያስጠበቀ አልመለስ ካሉ በኋላ ቀጭዎቻቸውና ነፍሳቸውን በማስጨነቅ ለኢጋንንት የሚያስረክቡ እኒሁ ናቸው። መዝ 34÷5-6 “የእግዚአብሔር መልአክ ያስጨንቃቸው መንገዳቸው ዳጥና ጨለማ ይሁን የእግዚአብሔር መልአክ ያሳድዳቸው” ብሎ ነብዩ ዳዊት መላእክተ ጽልመት የበደለኞችን ነፍስ እንደሚያሳድዱና እንደሚያስጨንቁ አስቀድሞ ተናግሯል።

መላእክት በነገድ መቶ (100) ናቸው።

እሳታዊያን ነገደ መላእክት	23 ነገድ
ብርሃናውያን ነገደ መላእክት	53 »
ጽልመታውያን ነገደ መላእክት	12 »
መላእክተ መዓት	12 »
	100

ከብርሃናዊያን ነገደ መላእክት መካከል አንዱ የሳጥናኤል ነገድ ከክብሩ ወድቆ የሰው ልጅ በምትኩ ተተክቷል። (መቶኛው ነገድ የሰው ልጅ ነው።)

ምንጭ መጽሐፈ ምስጢር

መላእክት በየነገድ አገልግሎታቸው

ቤተክርስቲያናችን ሰማያዊ ነች ሥርዓቷ ምድራዊ ያይደለ ሰማያዊ፣ ሥጋዊ ያይደል መንፈሳዊ ነው። የሰማይ መላእክት ለሰማያዊ አገልግሎታቸው ሰፍራ ተወስኖላቸው በኢዮር፣ በኤረር፣ በራማ እንደማዕረጋቸው ያገለግላሉ። በቤተ ክርስቲያንም ያሉ ካህናት በየማዕረጋቸው በመቅደስ፣ በቅድስት፣ በቅኔ ማኅሌት ያገለግላሉ። መላእክት በነገድ መቶ ሲሆኑ በግብራዊ ተልዕኮ ለአስር ይከፈላሉ በዚህም ማዕረጋቸው ጸንተው ያወድሳሉ። ቤተክርስቲያንም በመላእክት ሥርዓት ትመራለችና አስር ማዕረጋት አሏት። በውስጧም ያሉ አገልጋዮች በየማዕረጋቸው ጸንተው ሲያገለግሉ ይኖራሉ።

1. ኪሩቤል :- መንበር ተሸካሚዎች ናቸው። እያንዳንዱ ስድስት ክንፎች አሏቸው። ሁለቱ ክንፎች ወደላይ ሁለቱን ክንፎች ወደታች ሁለቱን ወደጎን በመዘርጋት መስቀልያ ሠርተው ከእግዚአብሔር መለኮታዊ ግርማ ለመከለል ፊታቸውን በክንፋቸው ይሸፍናሉ። ፊታቸውን ክንፎቻቸው መጋረዳቸው ከመለኮታዊ ኃይሉ የሚያስጥላቸው ሆኖ ሳይሆን፣ ለምሳሌ ከፊት ለፊት ቀስት የሚወረወርበት ሰው የዓይኑን ርግብግቢት በቶሎ ይጨፍናል። ዓይኑን መጨፈኑ ከቀስት የሚያድነው ሆኖ አይደለም የፍርሃት መልክት ነው። የእነርሱም ፍርሃት በዚህ ይገለጻል።

የልዑልን መንበር ይሸከሙታል ሲባል ፍጡር እርሱን የሚሸከም ሆኖ አይደለም። እርሱ ፍጥረቱን ይሸከማል እንጂ. ነገር ግን ለወዳጆቹ ሲገለጥ በዘፈቀደ የመንብረ መንግሥቱን ክብር እንደተሸከሙ ተገልጾ ይታይባቸዋል። መዝ 79÷1 "በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ ተገለጥ" መዝ 17:10 ፣ 2ኛ ሳሙ 22:11 "በኪሩቤልም ላይ ተቀምጦ በረረ በነፋስም ክንፍ ሆኖ ታየ።"

ሕዝ 10:9-22 ፣ሕዝ 10:12 ፣ 10:21 ፣ 1:5-28። ኪሩቤል አለቃቸው ኪሩብ የተባለው መለአክ ነው። እኒህ መንበረ እግዚአብሔርን የሚሸከሙ ኪሩቤል የሊቃን ጳጳሳት ምሳሌ ናቸው። በፊትና በኋላ ሰውነታቸው ዓይኖች ሞልተውባቸዋል። ቀንና ሌሊት ለምስጋናቸው እየርፉም ሰውነታቸው በሙሉ በዓይን ተሸልሟል ዓይኖቻቸው የነብር

ለምድ ይመስላሉ።

2. ሱራፌል :-እንደኪሩቤል ስድስት ክንፍ አሏቸው በስድስቱ ክንፎቻቸው ገጻቸውን በመጋረድ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ፍርሃት ይገልጻሉ ሱራፌል በቅዳሴ ጊዜ ያላቸው አገልግሎት ይህ ነው አይባልም የአምላካቸውን ሥጋና ደም ስለሚፈሩት እንደ ሻሽም ይነጠፋሉ፣ እንደቅጠል ይረግፋሉ፣ ብዙዎቹ በቅዳሴ ሰዓት መላእክት እንደ ሻሽ ይነጠፋሉ ሲባል ስለማይታዩአቸው ተረት ይመስላቸዋል። የሶርያ ንጉሥ ወልደ አዴር የእስራኤልን ልጆች ሊያጠፋ ኤልሳዕንም ሊማርክ በተነሳ ጊዜ መላእክት ኤልዕን ከበው በሰፍራው ተነጥፈው ይጠብቁት ነበር። 2ኛ ነገ 6÷15። የኤልሳዕ አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስማ ሥጋው በሚቆረስበት፣ ደሙ በሚቀዳበት በቅዳሴ ሰዓት እንደምን አይነጠፉለት? እንደምንስ አይከቡት?!

ኢሳይያስ ለእግዚአብሔር ባለመታዘዙ 28 ዓመት ሀብተ ትንቢት ተነስቶት በለምጽ ቆስሎ ነበር (ምንጭ አክሲማሮስ) ኢሳ 6÷1-8 ልቡን በንስሐ በሰበረ ጊዜ ሱራፊ መልአክ የክርቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ የሆነውን ሰማያዊ እሳት በጉጠት ይዞለት ደረሰ በፍሙ ከንፈሩን ቢዳስስለት ከለምጹ ነጽቶአል። ሱራፌል በአማናዊው የክርስቶስ ሥጋና ደም ያላቸውን አገልግሎት ይህን ይመስላል። ንስሐ ሳይገባ፣ ምንነቱን ሳይረዳ፣ በምን ቸገረኝነት ቅዱስ ቁርባንን የሚቀበልን ሰው ከአፉ ነጥቀው በረሃ (ገዳም) ለወደቁ ቅዱሳን ያቀብሉታል። ተነጣቂው ክፍል የቀረበ ይመስለዋል ነገር ግን አልተቀበለም። አለማወቁ መላእክት ነጠቁኝ ብሎ ተስፋ እንዳይቆርጥ ነው። በረሃ ያለው ጻድቅ ሲቀበል እርሱ በማያውቀው ሁኔታ ነው። አለማወቁ ከኃጥእ ሰው ነጥቀው መላእክት ለእኔ አቀበሉኝ ለካስ በቅቼአለሁ? ብሎ በትዕቢት እንዳይወድቅ ሱራፌል ሁለቱንም በምስጢር ይፈጽሙታል። ሱራፌል የጳጳሳት ምሳሌ ናቸው። አለቃቸው ሱራፌ መልአክ ነው።

3. ኢጋእዝት :-አግአዘ ማለት ነጻ አወጣ ማለት ሲሆን ኢጋእዝት ነጻ አውጪዎች (ጌቶች) ማለት ነው። ኢጋእዝት የተሰኙት የመላእክት ክፍሎች የለምክንያት ይህ ስያሜ አልተሰጣቸውም የሰው ልጆች ከሚያዙበት የኃጢአት ባርነት፣ ከምንታሰርበት የበደል ምርኮ፣ ከምንጋዝበት ከጨለማ

ግዞት ነጻ እንድንወጣ ሁል ግዜም ያለማቋረጥ ይጸልዩልናልና ነው። እግዚአብሔርም ምልጃቸውን ተቀብሎ በምህረቱ ከእስራታችን ሁሉ የተፈታን ነጻ የወጣን ያደርገናል። ዘካ 1÷12-14 ስለዚህም በጸሎታቸው ነጻ ስለሚያወጡን አጋእዝት ተብለዋል።

አጋእዝት ጥንታዊና የመጀመሪያ አለቃቸው ሳጥናኤል ነበር። እርሱ ከክብሩ ሲወድቅ ቅዱስ ሚካኤል በምትኩ ተሾሞበታል።

"ሰው ለተሸነፈበት ኃጢአት እርሱ ባርያ ነው"። 2ኛጴጥ 2÷19 ዛሬ ሥጋዊነት አሸንፎን ባርያ ያደረገን ሁሉ ወደ አጋእዝት አንጨኽ አድራሻቸውም በአለቃቸው በቅዱስ ሚካኤል በኩል እናገኛቸዋለን በምልጃቸውም የተተበተብንበትን የኃጢአት ሰንሰለት ይበጣጥሱልናል። ነፃም ያወጡናል። አጋእዝት የኤጲስ ቆጶሳት ምሳሌ ናቸው።

4. ኃይላት :-የእግዚአብሔር ጋሻ ጃግሬዎች ናቸው። ኃይላት በመንፈሳዊ ህይወት ዝለው ፣ መንፈሳዊ ጽናት ላነሳቸው ክርስቲያኖች ብርታትና ኃይልን በጸሎታቸው ከአምላካቸው ያሰጣሉ። ያበረታታሉም። ተስፋ መቁረጥ ለሚያንገዳግዳቸው ኃይልን ይለግሳሉ። አጋር ከእመቤቷ ከሳራ ጋር ተጣልታ ወደ ቃዴስ በርኔ ስደትን ተያያዘችው። የበረሃው ዋእይ ሰውነቷን ኃይል አልባ አደረገው። ውስጧን ያደቀቀው ተስፋ መቁረጥና ብሶት ሳያንሳት የተጫናት የድካም ቀንበር እርሷነቷን እድትረሳ ነበር ያደረጋት። በረሃ ያደረቀው ጉሮሮዋን ለማርካት ወደ ሱር የሚወስደውን የምንጭ መንገድ ይዛ ስትሄድ የእግዚአብሔር መላእክ ወደርሷ መጣ። ዘፍ 16÷7። የመጣውም ድካሟን አውቆላት ነበር። አበረታትቷት፣ ድካሟን በጽናት ተክቶላት፣ ጥሟን አርክቶላት ወደእመቤቷ እንድትመለስ መክሯት ከፊቷ ተሰወረ። ዛሬ ውስጣችን ከእግዚአብሔር ብዙ ነገር የተጠማ ነው። በምልጃቸው ተደግፈን ጥማችን እንዲረካ መላእክቱን እንማፀን። ኃይላት ድካማችንን ያውቃሉ። ፈጥነው ይደርሱልናል፣ ኃይልንም ያላብሱናል። በአጠቃላይ ለድካማችን ብርታትን፣ ለውድቀታችን መነሳትን፣ ለስብራታችን መጠገንን፣ ለጥማችን እርካታን፣ ለማጣታችን ማግኘትን፣ ለመጥፋታችን መገኘት ቁልፍ ሆነው ከእግዚአብሔር በተሰጠው ጸጋ ያገለግሉናል። ኃይላት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ነው። በከተማቸው በአራተኛው ሰማይ በኢየሩሳሌም ስማያዊት ሰፍረው ይገኛሉ። የቆሞሳት ምሳሌ ናቸው።

5. አርባብ :-ረበበ ማለት ሸፈነ (ጋረደ) ማለት ሲሆን አርባብ ማለት ይሚጋርዱ (የሚሸፍኑ) ማለት ነው። መሸፈናቸው ስለሁለት ነገር ነው። አንደኛ የእግዚአብሔርን መንበር በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ፣ በብርሃናዊ ክብራቸው ይጋርዳሉ። ሁለተኛው ለእኛ ሕይወት ጠላት ከሚሰነዝርብን ፍላጻ ሽፋን ይሆናሉ ። መዝ 90÷1-12 "ክፉ ነገር ወደአንተ አይቀርብም መቅሰፍት ወደቤትህ አይገባም በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለአንተ ያዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሱሃል።" ከለላና አማላጅነታቸው ሽፋን ሆኖ ከክፉ መንፈሳዊ ውድቀት ያነሱናል። ለሙሉ ደህንነታችን በጸሎት ይቆሙልናል። የጠላትን መንገድ ይዘጉበታል። በለዓም እስራኤልን ሊረግም አህያይቱ ላይ ተጭኖ ክፉ ሀሳቡን በልቡ አርግዞ ሲጓዝ ለእስራኤል ደህንነት ሲል መልአኩ መጣ "እቋቋምህም ዘንድ መጣሁ። ዘኁ 22÷32 ብሎ መንገዱንም ዘጋበት የበለአምን ዓላማ አስቀይሮ በለአም እስራኤልን በመርገም ፈንታ መርቆ ተመለሰ። "ክፉ ነገር ወደአንተ አይቀርብም መላእክቱን ስለአንተ ያዛቸዋል።" ተብሏልና አርባብ በወዳጆቻቸው ላይ የሚረቡና ወዳጆቻቸው ከሚያውቁትም ሆነ ከማያውቁት ውድቀት ይጋርዷቸዋል። ስለዚህም አርባብ (የሚጋርዱ) ተብለዋል። አለቃቸው ቅዱስ ገብርኤል ነው። ጥበቃቸው እንዳይርቀን ልንጠራቸው ይገባል። በሁለተኛው ሰማይ አስፍሮአቸዋል። አርባብ የቀሳውስት ምሳሌ ናቸው።

6. መናብርት :- ነበረ ተቀመጠ ማለት ሲሆን መናብርት ተቀማጮች ማለት ነው። መናብርት ለእግዚአብሔር እጅግ ቅርብ ናቸው። የእግዚአብሔር ልዩ ውስጠ ምስጢርና ጋሻ ጃግሬዎችም ናቸው። መናብርት በብርሃናዊ ዙፋናቸው ተቀምጠው እግዚአብሔርን ያከብሩታል። "በቅዱሳኑ ምክር እግዚአብሔር ክቡር ነው"። መዝ 88÷6-7 ተብሏልና። ምናልባት በነቢዩ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ያማከረው ከቶ ማን ነው የሚል ቃል እናነባለን ኢሳ 44÷24 ኢዮ 36÷22 ነቢዩ ይህንን ሲል እግዚአብሔር ዓለምን በሚፈጥርበት ጊዜ አማካሪ እንዳላስፈለገው ለማለት ብቻ መሆኑን አንዘንጋ። በተረፈ እግዚአብሔርም ክቡር ፍጡራኑን ለወዳጆቹ (ለመናብርት) ያማክራቸዋል። አሞ 3÷7። እነርሱም የጌታ ሥራ ስለሚያስገርማቸው ተመስጠ ይመጣባቸዋል። በዚህ ጊዜ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ ለአምላካቸው ውዳሴን ያቀርባሉ። መናብርት ለፈጣሪያቸው ቅርብ እንደመሆናቸው የሰው ልጆችን ችግር

ወደ ፈ ገሪያቸው ያቀርባሉ አለቃቸው ቅዱስ ሩፋኤል ነው።

መናብርት ለሰው ልጆች ያላቸው ጥበቃ ድንቅ ነው። የመብረቅ ጋሻ፣ የእሳት ጦር ይዘው ወደሰው ልጆች የሚመጣውን የሰይጣን ኃይል እያቃጠሉት እንደ ንፋስ ሲፋጠኑ ይኖራሉ። "መላእክቱን የሰጠን ጌታ የተመሰገነ ይሁን።" እኒህ ምሳሌነታቸው ለዲያቆናት ነው።

7. <u>ስልጣናት</u> :- ፍጥረታትን በመጠበቅ ስልጣን አላቸው መዛግብተ ዝናማት አራት ናቸው። በአራቱም መዛግብተ ዝናማት ላይስልጣን አላቸው አስራ ሁለት የብርሃን መስኮቶች አሉ። በእነርሱም ላይ ስልጣን አላቸው። ሰዎች በምድር ላይ ኃጢአታቸው ቢበዛ በትዕዛዘ እግዚአብሔር በአዝርእት ላይ ቸነፈርንና የተለያዩ መቅሰፍቶችን ለማውረድ ስልጣን አላቸው። ለዚህም ስልጣናት ተብለዋል። ከወዲሁም ሰዎች በደላቸውን አምነው ልባቸውን ሰብረው ወደንስሐ ሲቀርቡ ምህረትን ለማምጣት የሚታዘዙ በምህረት ላይ ሥልጣን ያላቸው እኒሁ ክፍሎች ናቸው።

ስልጣናት የምጽአትን አዋጅ አብሳሪ ናቸው። ክርስቶስ ይቺን ዓለም ከነጓዟ እንደብራና ጠቅልሎ ሊያሳልፋት ሲመጣ አስቀድሞ የዓለምን ህልፈት ለሰዎች ያሰማሉ። በቅዱስ ሚካኤል መሪነት መለከት ይነፋል፣ ነጋሪት ይጎሰማል በምድር ትቢያ ያንቀላፉ ሙታን ይነሳሉ ሁሉም ለፍርድ ይቆማሉ ዳን 12÷1-2 ስልጣናት የምጽአትን አዋጅ ነግረው የሚቆሙ ብቻ ሳይሆን መጽሐፍ እንደሚል ማቴ 25÷31 ጌታችን በእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት ታጅቦ ለፍርድ ሲመጣ አምላካቸውን አጅበውት የሚመጡት ቅዱሳን መላእክት እኒህ ስልጣናት ናቸው 2ኛ ተሰ 1 ... ጌታ ኢየሱስ <u>ከስልጣናት መላእክት</u> ጋር ከሰማይ በእሳት ነበ... ሲገለጥ ..." ብሎ ቅዱስ ጳውሎስ ጌታችን አመጣጡ ከስልጣናት መላእክት ጋር እንደሆነ ያስረግጥልናል። አለቃቸው ቅዱስ ሱርያል መልአክ ነው። በሥስተኛው ሰማይ ሰፍረው ይገኛሉ። ምሳሌነታቸው ለንፍቀ ዲያቆናት ነው።

8. <u>ሊቃናት</u>:- ሊቃናት የሚባሉት ሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ናቸው። ካህናተ ሰማይ በውሳጤ መንጦላይት በጽርሃርያም ባለችው ቤተመቅደስ ያገለግላሉ። ቅዳሴአቸውም አይቋረጥም። የሰው ልጆች ጸሎት፣ ምስጋናና ሆነ መስዋዕት በሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ እጅ ባለው የወርቅ ማዕጠንት

...ሉል ያርጋል። ብዙዎች ጸሎታቸው ከአንደበታቸው እንደወጣ ወደ መንበረ ጸባኦት ሰተት ብሎ የሚገባ ይመስላቸዋል ነገር ግን ሥርዓቱ እንዲህ አይደለም። በቅድሚያ በሃያ አራቱ ካህናተ ሰማይ እጅ ባለው የወርቅ ማዕጠንት ውስጥ ይደርሳል እነርሱም ምዑዝ በሆነ እጣናቸው መንበረ ፀባዖትን እያጠኑ ከምስጋና ጋር ጸሎታችንንም ሆነ መስዋዕታችንን ያሳርጉልናል። ከዚህ በኋላ ሁሉን በፈቃዱ የሚያደርግ እግዚአብሔር ተቀብሎ የቸርነቱን ሥራ ይሠራብታል። ራዕ 5÷8 መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንስሶችና <u>ሃያ አራቱ ሊቃናት</u> በበጉ ፊት ወደቁ እያንዳንዳቸውም በገናንና <u>የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን</u> የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ" የወርቅ ዕቃ (ጥና) መያዛቸውን በንጽህ ...ጣናቸው የቅዱሳንን (የክርስቲያኖችን) ጸሎት የሚያሳርጉበት ...ልጣናቸው ነው ። ራዕ 4÷4 ከሀያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር ...በተደራቢነት የብርሀን አክሊል ደፍተው፣ በቀስተ ዳመና ከብረው፣ በወርቅ ያሸበረቀ ልብሰ ተክህኖ ለብሰው፣ ከሀያ አራቱ ካህናተ ሰማይ ጋር የሚያገለግሉ አሉ። እነርሱም:- ቅዱስ ሚካኤል፣ ቅዱስ ገብርኤል፣ ቅዱስ ኢዩራማኤል፣ ቅዱስ ዙጡኤል፣ ቅዱስ ሰራቃኤል፣ ቅዱስ አፍኒን ... ቅዱስ ሰላትያኤል፣ ቅዱስ ሳዳክያኤል ሲሆኑ። ከሰው ወገን አቡነ ...ገብረ መንፈስ ቅዱስ... ቅዱስ ዳዊትን የመሰሉት አብረው ያገለግላሉ ሊቃናት አለቃቸው ሰላትያኤል መልአክ ነው። በሥስተኛው ሰማይ ሰፍረው ይኖራሉ። ምሳሌነታቸው ለአና ጉንስጠሳዊያን ነው።

<u>መኳንንት</u> :- እግዚአብሔር መኳንንትን ልዩ ጠባቂዎች አድርጎ ...ሾሟቸዋል። መኳንንት ለፍጥረት ያላቸው ጥበቃ እጹብ ያሰኛል። የቅዱሳንን ...ለዘም ሳይቀር ይጠብቃሉ።

የእሳት ሰይፋቸውን ታጥቀው (ወድረው) የነፋስ ፈሳሽ፣ የእሳት ...ዘንግ ይዘው ሰይጣናት በክርስቲያኖች ላይ ከሚሰነዝሯቸው ጥቃት ሁሉ ...ሰው ያገበረከኩዋቸዋል ድልን ለወዳጆቻቸው ያስታጥቃሉ። ከመከራ ... ከመከራ ነፍስ በተሰጣቸው ኃይል ያድኑናል። ዘፍ 19÷19 "እነሆ ...በፊትህ ሞገስን አግኝቷል ነፍሴን <u>ለማዳን</u> ያደረክልኝን ...ምህረትህንም አብዝተሃል" እያለ ሎጥ የእግዚአብሔር መልአክ ...የደህንነት ሥራ ያደንቃል። ታላቁ አባት ያዕቆብም የልጁን ...ልጆች ሲባርክ ዘፍ 48÷16 "እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ

<u>ያዳነኝ መልአክ</u> እርሱ እነዚህን ብላቴናች ይባርክ... እያለ ከክፉ ነገ
ያዳነውን መልአክ ውለታ ሳይዘነጋ እንዲያውም ብላቴናቹን መልአከ
እንዲባርክለት ሲማጸን ይነበባል።

ቅዱሳን መልአክትን ያድኑናል ብለን ስንመሰክር ተቃዋሚዎ
ይቆጣሉ። ኢዩ 2÷12 "የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ይድናል" ስለሚ
እናንተ መጠራት የማይገባውን ስም እንድንበታለን ብላችሁ ለም
ትጠራላችሁላ ይላሉ። ሰዎች የምስጢር ድሆች ስለሆኑ እንጂ በመላእክ
ስም ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አለ። ከስማቸው ጫፍ በእብራይስ
(ኤል) የሚለው ቃል እግዚአብሔር ማለት ነው። አምላካቸውም እራ
ስሙ በእነርሱ ላይ እንደሆነ ነግሮናል ዘጸ 23÷21 ሚካኤል ስንል አብረ
የእግዚአብሔርን ስም ጠርተናልና እንድናለን። አንድም የእግዚአብሔ
ድብቅ (ህቡዕ) ስሞች በክንፎቻቸው ላይ ስላሉ ስሞቻቸውን ስንጠ
የስሙ አድኅኖት በእነርሱ ላይ ነውና እንድንባቸዋለን።

እግዚአብሔር ከቅዱሳኑ ይህ ነው የማይባል ፍቅር ስላለ
አጥንታቸውን እንኳን ይጠብቃል መዝ 33÷19-20 ለዚህ አገልግሎ
መኳንንትን አቁሟቸዋል። መኳንንት የቅዱሳንን አጽም ከየስፍራ
እየሰበሰቡ በከበሩ ገዳማት በክብር እያኖሩ ይጠብቁታል። ... ዮሴ
በግብጽ ሲኖር ለእስራኤል ልጆች ወደ ቅድስት አገራቸው ሲመለ
የራሱን አጽም ይዘውለት እንዲሄዱ ነግሯቸው ነበር። ዘፍ 50÷24-2
ዛሬም ዮሴፍን የመሰሉ ቅዱሳን አጽማቸው ወደ ቅዱስ ስፍራ በየገዳማ
በመላእክት ይወሰድላቸዋል።

መኳንንት ከሁለተኛው ሰማይ ላይ ሰፍረዋል አለቃቸው ቅዱ
ሰዳክያኤል ሲሆን ምሳሌነታቸው ለመዘምራን ሊቃውንት ነው።

10 <u>መላእክት</u> :-እኒህ በጭፍራው መላእክት ይባላሉ። ምድ
የተሸከመቻትን ፍጥረታት በሙሉ ለመጠበቅ ተሰልፈዋል። የእሳ
ድንጋይ፣ የእሳት ወንጭፍ ይዘው ለአዝእርት፣ ለፀሐይና ለጨረቃ ሳይተ
ዘብ የቆሙ ናቸው። አለቃቸው አናንኤል መልአክ ነው። በሦስተኛ
ሰማይ ሰፍረው ይገኛሉ። ምሳሌነታቸው ለአፃውተ አናተ
(ለቤተክርስቲያን በር ዘጊዎች) ነው።

<u>መላእክት በሰባቱ የተልዕኮ ዓይነቶች</u>

ጽርሐ አርያምን ያህል ታላቅና ቅድስት ሥፍራ ያለ ሥርዓት አልተሠራችም። ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊት ኢየሩሳሌም ምሳሌ እንደመሆኗ፤ ዲያቆኑ የካህኑን አገልግሎት እንደማያገለግል፤ ደብተራው የዲያቆኑን እንደማያገለግልና ሁሉም በሥርዓት እንደሚያገለገሉ መላእክትም ከተሰጣቸው እግሬ ተልኮ ውጭ በሌላው አገልግሎት ገብተው አይሠሩም፤ ሥርዓት ተሠርቶላቸዋልና።

1ኛ. <u>ሰባህያን ወዳስያን</u>

ከአስሩ የመላእክት ከተማ ውስጥ ሊቃናት የተባሉት ነገድ ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ ናቸው። እግዚአብሔርን ያለማቋረጥ ያወድሱታል ምስጋናውን ዕለት ዕለት ያቀርባሉ ዛሬ ካህናቱ ጌታን በሰዓታቱ በግብረ ሌሊቱ እነደሚያገለገሉ እነርሱም በሰማያዊው መቅደስ ምስጋናቸውን አያስቀሩም። ስለሆነም ሰባህያን፣ ወዳስያን በተባለው የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ ይገኛሉ።

2ኛ. <u>ቀዳስያን</u>

ዛሬ ካህናት አሐዱ አብ ቅዱስ አሐዱ ወልድ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብለው ድንቅ በሆነ ቅዳሴ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉት እኒህም መላእክት ይህን በመሰለ ጥዑም ቅዳሴ አምላካቸውን እየቀደሱ ያገለግሉታል። ለዚህ የተመረጡ <u>ሥልጣናት</u> የተባሉ የመላእክት ነገድ ናቸው።

3ኛ. <u>አዕኳትያን</u>

አዕኮተ - አመሰገነ፣ አዕኳትያን - አመስጋኞች ማለት ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች የሚያደርግላቸውን ድንቅ ሥራ በመመልከት ስለ ሰው ልጆች ተገብተው (ተወክለው) ፈጣሪያቸውን ያመሰግኑታል። ለመላው ቅዱሳን እግዚአብሔር ስለሚያደርገው ፍቅር ፈጣሪያቸውን ያወድሱታል። እግዚአብሔር

ለእንስሳትና ለአራዊት ስለሚያደርገው መግቦትና እንክብካቤ ጌታቸውን ያመሰግኑታል። ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ <u>አርባብ</u> የተባሉ የቅዱሳን መላእክት ክፍል ናቸው።

4ኛ. <u>ማኅሌታውያን</u>

ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔርን በማኅሌት ያመስግኑታል። ዛሬ አባቶቻችን መዘምራን በማኅሌት እንደሚያመሰግኑት እነርሱም እንዚራ በሆነ ማኅሌታዊ ጥበብ፣ በብርሃን ጸናጽል፣ በብርሃን ከበሮ የቅላጼው ውበት ሊነገር በማይቻል ሕይወትንና አጥንትን በሚያለመልም ድምጻቸው በማኅሌት ያወድሱታል። ማኅሌታውያን መላእክት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ሲሆን እርሱም ማኅሌታዊ መልአክ ነው። ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ ኃይላት የተባሉት የመላእክት ክፍሎችና <u>ሰባቱ ሊቃነ መላእክት</u> ጭምር ናቸው።

5ኛ. <u>ተራዳዕያን</u>

እነዚህ ለሰው ልጆች ችግርና አደጋ ፈጥኖ ደራሽ ናቸው። ሰዎች ከሚደርስባቸው ማንኛውም አደጋ ሁሉ ደርሰው አድኅኖታቸውን ይለግሳሉ። መዝ 33÷7 "የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሠፍራል <u>ያድናቸውማል</u>" ብዙዎች መላእክት አያማልዱም ሲሉ ሊያፍሩ ይገባቸዋል። እንኳንስ ጸልዮ ማስታረቅ (ማማለድ) በተሰጣቸው ጸጋ የማዳንም ሀብት አላቸው። ለዚህ አገልግሎት የተመረጡ በድምሩ መላእክት ናቸው።

6ኛ. <u>ፀዋርያን</u>

(የእግዚአብሔን ዙፋን ተሸካሚዎች) እነዚህ ፀወርተ መንበር ኪሩቤል ሲሆኑ ዙፋኑን ተሸክመው በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ቅዱስ፣ቅዱስ፣ቅዱስ እያሉ ያመሰግኑታል። እግዚአብሔርም ለወዳጆቹ ሲገለጥ በኪሩቤል ላይ እንደተቀመጠ በዘፈቀደ ይገለጽላቸዋል። ሕዝ 1 ስለ ኪሩቤል በገጽ 26 ላይ ተገልጿል።

7ኛ. <u>አጣንያን</u>

እነዚህ አጣንያን ሱራፌል ሲሆኑ እንደ ኪሩቤል ስድስት ክንፎች አሏአቸው። ኢሳ 6÷2 አገልግሎታቸውም ዛሬ ካህናት በቤተ ክርስቲያን ጸሎተ ዕጣን፣ ጸሎተ አኮቴት እንደሚያደርሱት እነርሱም አጠንተ መንበር ካህናተ ሰማይ ናቸውና በየጊዜውና በየሰዓቱ ከምድር ወዳሰያን፣ ከምድር ቀዳሰያን መስዋዕት ተቀብለው ምዑዝ በሆነ ዕጣናቸው ያሳርጋሉ። ራዕ 4÷8-11 እግዚአብሔርም ተቀብሎ የቸርነቱን ሥራ ይሠራብታል።

<u>ከሰባቱ ሊቃነ መላእክት ቀጥሎ ያሉ የመላእክት አለቆችና ተልዕኮአቸው</u>

[illegible] <u>ሰዳክያኤል አቃቤ ጻድቃን (የጻድቃን ጠባቂ)</u>

ጻድቃን በሚገጥማቸው ፈተና ሁሉ አበርቺ መልአክ ነው። [illegible] ጊዜ አጽናኝ ነው። ያዘኑትን ያረጋጋል። ይህ መልአክ ጌታ [illegible] ክርስቶስን እንኳ ሊያጽናና የመጣ መልአክ ነው። ሉቃ 22÷39-45 [illegible] ለሞት ተላልፎ ሊሰጥ ባለበት ሰዓት ሲጸልይ "ፈራ" ይላል ሞት [illegible] ቀርቧልና። እውን ጌታ ሞትን የሚፈራ ሆኖ ሳይሆን በአዳም ያለ [illegible] ፍርሀትን በፍርሀቱ ሊያርቅለት፣ በተጨማሪም መፍራቱ <u>(ለአጸድቆተ</u> [illegible]) ፍርሀት የሚስማማው ሥጋን መልበሱን ሲያጠይቅ ነው። [illegible] ነበር መልአኩ ሊያጽናናውና ሊያበረታው የመጣው። ጌታችን [illegible] አጽናኝ መልአክ ከአስፈለገው ለእኛስ አያስፈልገንምን? [illegible] <u>ጌታችን በመለኮቱ አጽናኝ መልአክ የሚያስፈልገው ሆኖ</u> [illegible] <u>እርሱ ራሱ የሚያጽናና አምላክ ነው</u>። ዮሐ 14÷1 ይሁን እንጂ [illegible] የመጣ አምላክ ነውና እኔ <u>በሥጋ</u> ሥርዓት ስመላለስ አጽናኝ [illegible] እንዳስፈለገኝ እናንተም የሚያጽናኑ፣ የሚያበረታቱ ቅዱሳን [illegible] ያስፈልጓችኋል ሲለን ነው። ስለዚህ ብቸኝነት በከበበን ጊዜ [illegible] መሰል መላእክቱን ልንጠራቸው ይገባናል።

2ኛ. ሰላትያኤል ነአዴ ጽድቅ (ጽድቅን መካሪ)

ይህ መልአክ የጽድቅ መካሪ ሲሆን ከቅዱስ ሚካኤል ሥልጣ
ጋር ህብረት አለው። ሐመረ ኖህ በተሠራች ጊዜ ኖህ አንድ ክንድ ሠር
ሲውል እርሱ አንድ ክንድ ሠርቶለት ያድር ነበር። ነአዴ ጽድቅ፣ ነአ
ጻድቃን ነውና (ጻድቃንን ይመክራል፣ ይረዳቸዋል፣ ያገለግላቸዋል)። ና
መርከቡን እንዴት መሥራት እንዳለበት ከእግዚአብሔር ተቀብ
መመሪያ ያመጣለት ነበር።

3ኛ. ሠራቃኤል

ይህ መልአክ አእምሮአቸውን ላጡ ለሕሙማን አዕምሮ ፈወ
ይሆን ዘንድ የተሾመ መልአክ ነው ሄኖክ 6÷6 "አእምሮአቸውን ባ
ሰዎች ላይ የተሾመ ከከበሩ መላእክት አንዱ ሠራቃኤል ነው።" ብዙዎ
አዕምሮአቸውን ያጡ ሰዎች በእሳት፣ በውኃ ውስጥና በሌሎችም አን
ሥፍራ ሲወድቁና ጉዳት ሳያገኛቸው ሲያዩ የያዘው ሰይጣ
ስለሚጠብቀው ነው ይላሉ። "ውሸት" ሰይጣን ያጠፋል እንጂ አይጠብቅ
የሚጠብቃቸው በሕሙማን ላይ የተሾመ ቅዱስ ሠራቃኤል መልአክ ነ

ስለዚህም የሠራቃኤል ጸበል ቢገኝና መልኩን ለሕሙማን አዕም
ቢጸልዩላቸው ሹመቱ ነውና በተሰጠው ሰማያዊ ሥልጣን ይፈውሳቸዋ
ሠራቃኤል አዕምሮአቸው ለጎደለ ሰዎች ሁል ጊዜ ዘብ የሚቆምላቸ
ሩህሩህ መልአክ ነው።

4ኛ. ዙጡኤል አቃቤ ገነት

ይህ መልአክ የገነት ጠባቂ ሹም ነው። ሹመቱ ከቅዱስ ገብርኤ
ጋር ህብረት አለው።

5ኛ. ኢይሩማኤ አቃቤ ገነት (የገነት ጠባቂ)

ይህ መልአክ የገነት ጠባቂ ሹም ነው። አገልግሎቱም ከቅ
ዙጡኤልና ከቅዱስ ገብርኤል ጋር ህብረት ያለው ሲሆን በተጨ
ከቅዱስ ዑራኤል ጋር ህብረት አለው። በልዑል እግዚአብሔር ፈ

ቀናትንና ሰዓትን መጥኖ ማኖር ተሰጥቶታል።

መላእክት የሚለው እያንዳንዱ ቃል ሲተረጎም

መ - መአድያነ ጽድቅ (የጽድቅ መካሪዎች)
- መሰድዳነ አጋንንት (አጋንንትን የሚያሳድዱ)
- መጋቢያነ ምስጢር (ምስጢረ እግዚአብሔርን የሚመግቡ)

ላ - ላዕላውያን (ከፍተኞች) ስለክብራቸው ከፍተኛነት (በላይ በሰማይ ያሉ)
- ላዕካነ ጽድቅ:- የጽድቅ መልዕክተኞች

እ - እቁባነ ምህረት (በምህረት የሚጠብቁ)

ከ - ክቡራን (ካደረባቸው ከእግዚአብሔር ክብረ ብርሃን የተነሳ ክቡራን ናቸው።)
- ክቡራነ አእምሮ ክቡር የሆነ አዕምሮ አላቸውና (በአዕምሮ የከበሩ ይላቸዋል)

ት - ትሁታን (ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጭ አይሆኑምና ትሁታን ይላቸዋል)
- ትጉሀን (ለአገልገሎታቸው እረፍትን አይናፍቁምና ትጉሀን ናቸው።)

ማጠቃለያ ሀሳብ

- ቅዱሳን መላእክት ለማንም ለማን የማያደላ ፍቅር አላቸው። ሀብታም፣ ደሀ፣ ትንሽ፣ ትልቅ፣ ኃጥዕ ጻድቅ ሳይሉ በእኩል ዓይን ሁሉን ይጠብቁታል። ጻድቁ በጽድቁ እንዲጸና፣ ኃጥዑም ከኃጢአቱ እንዲመለስ ይጸልያሉ። ሉቃ 13÷6-9

- ቅዱሳን መላእክት በሰው የልቡና ጓዳ ውስጥ የሚመላለሰውን

ሁሉ በግልጽ ያዩታል (ያውቁታል)። የውስጣችን ፍላጎት ግልጽ ሆኖ ይታያቸዋል።

- ቅዱሳን መላእክት አንድ ነገር ለማወቅ የሚወስድባቸው ጊዜ አይኖርም።

- ቅዱሳን መላእክት በእግዚአብሔር ፍቅር ሰጥመው በጸጋው ሰክረዋልና እግዚአብሔርን አመስግነው አይጠግቡትም ለምሳሌ የእግዚአብሔር ጠላት ሳጥናኤል ከክብሩ እንደተዋረደ ከደስታቸው የሚመነጨው ዝማሬ መጠን አልነበረውም። ከደስታቸው ብዛት ስፍራም አልተገኘላቸውም በዚህ ዝማሬያቸው ሌት ከቀን ሲያመሰግኑት የሴኮንድ 1/10 ያመሰገኑት አልመሰላቸውም ነበር።

- "የፈጣሪን ድንቅ ሥራ ሲያደንቁ ይኖራሉ" ቅዱሳን መላእክት በባህሪዩ የደመቀው የእግዚአብሔር ፊቱን አይተው አይጠግቡም።" በመንበሩ ዙሪያ የተሞላውን ብርሃናዊ ደመና ሲያዩ፣ከመበሩ ስር የሚወጣው የነጎድጓድ እሳት ሲደምቅ፣ መብረቁ ሲናወጥ ፣ የእግዚአብሔ መዓዛ ረድኤት ምግብ በሌለበት ስፍራ የተለያዩ ቅዱሳንን ሲመግባቸውና ፊታቸውን ሲያበራቸው፣ ይህ ነው በማይባል በባህርያዊ ክብሩ አምላካቸው ክብር ለማየት ሲያስቸግራቸው የፈጣሪያቸውን ድንቅ ሥራ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያሉ በተመስጦ ምስጋና ይገልጻሉ።

- ቅዱሳን መላእክት ለእግዚአብሔር ያላቸው ፍቅር ይህንን ይመስላል ብሎ መግለጽ አይቻልም። እግዚአብሔርም ለእነሱ ያለውን ፍቅር እንዲሁ መግለጽ አይቻልም። ለዚህም ነው ቅዱሳን መላእክትን እንዳናስቆጣበት ያዘዘን። ዘፀ 23÷20-23

- እግዚአብሔር የብርሃን መጎናጸፊያ አድርጎላቸዋል። "ክብርን ተጎናጽፋችኋል ሲላቸው ነው"።

- የብርሃን ጫማ አጫምቷቸዋል "አጋንንትን እየረገጡ መንጸፈ ደይን የሚያወርዱበት ኃይል ነው።"

- የብርሃን አክሊል (ዘውድ) ደፍቶላቸዋል። "የጸጋ ጌቶች ናችሁ ሲላቸው ነው።" ኢያ 5÷14 የብርሃን መስቀል ሰጥቶአቸዋል። የብርሃን ዝናር አስታጥቆአቸዋል። "የቅድስናን ዝናር እንዳስታጠቃቸው ሲያጠይቅነው"።

- ቅዱሳን መላእክት ረቂቃን ከመሆናቸው የተነሳ አንዱ መልአክ በሌላው መልአክ አካል ውስጥ ማለፍ ይችላል። ስለሆነም መንገድ ልቀቅልኝ (አሳልፈኝ) አይለውም። እኛ ግን ግዙፋን ነንና እንዲህ እናድርግ ብለን ግጭት (Collide) ፈጥረን እንቆስልና ወዲያው የሆስፒታል አልጋ ማሞቅ እንጀምራለን። በሥጋውያን ተፈጥሮ ውስጥ ይህ አይሠራም።

ምንጭ፡- አክሲማሮስ፣ ድርሳነ ባስልዮስ

ምዕራፍ ሁለት

የተቃዋሚዎች ጥያቄና መልሶቻቸው

"ማገልገል ያለብን ጌታ ኢየሱስን ብቻ ነው ከዚህ አልፋችሁ ቅዱሳንን ለምን ታገለግላላችሁ"

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምሳሌ ሲያስተምር የሰዎች ክብርን ማግኘት ያስቆጨውን ሰው "ዓይንህ ምቀኛ ናትን?"ብሎታል ማቴ 20÷15 ዛሬ እግዚአብሔር ያከበራቸውን ቅዱሳን ስላከበርናቸው የሚመቀኙ በዝተዋል።

በመጀመሪያ ማንም ሰው ተነስቶ ጌታ ኢየሱስንም ቢሆን ማገልገል አይችልም በቅድሚያ በሃይማኖት መቆም፣ ህይወቱን ማስተካከልና መስቀሉን መሸከም አለበት። ክህደትና ኑፋቄ በሸረሸረው ሕይወት ክርስቶስን ማገልገል አይቻልም። እግዚአብሔርም በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ አይከብርም። የኑፋቄን ዝናር ታጥቆ ይህንን አድርጌልሀለሁ፣ አገልግዬሀለሁ ማለት የሚያስከትለውን እንወቅ። ማቴ 7÷22-23 "በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንም በስምህ አጋንንትን አላወጣንም በስምህ በዙ ተአምራት አላደረግንም?" ይሉኛል በዚያን ጊዜ ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከኔ እራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ"።

ነገር ግን ያመነ ሁሉ ማንነቱን ካወቀና ራሱንም ካስተካከለ በኋላ እግዚአብሔርን በተሰጠው ጸጋ ሊያገለግልና መክሊቱን ሊያበዛ ይገባል።

ቅዱሳንንም እግዚአብሔር ለሰጣቸው ክብር ስንል <u>የጸጋ አገልግሎት</u> እናገለግላቸዋለን ነብዩ ኤልሳዕ መምህሩ ኤልያስን ቢያገለግል በኤልያስ ላይ የነበረ ሀብት መንፈስ ቅዱስ ሁለት እጥፍ ሆኖ አድሮበታል። 2 ነገ 2÷9 ተጠቀመ እንጂ አልተጎዳም። ለታመመ፣ ለወደቀ፣ ላጣና ለነጣ ቀዝቃዛ ውሃ ጠልቀን በቅዱሳን ስም መስጠት ቅዱሳንን ማገልገል ነው። ኤልሳዕ የኤልያስን ጸጋ እንዳገኘ በቅዱሳን ስም የምናደርገው አገልግሎት ክብራቸውን እናገኝበታለን። ማቴ 10÷40-43

ብዙዎች ቅዱሳንን ማገልገላችን ጣዖትን እንደማገልገል ይቆጥሩታል። የተሳሳተ አመለካከት ነው። ቅዱስ ጳውሎስ በሕይወት ዘመኑ ቅዱሳንን ያገለግል ነበር። ሮሜ 15÷25 "አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ" እና ቅዱስ ጳውሎስ ማንትን አገለገለን? አላደረገውም። እንደ ሐዋሪያው ክርስትና ኢየሩሳሌም (ቤተክርስቲያን) ሄደን ቅዱሳንን አገልግለን እግዚአብሔርን አመስግነንና አምልከነው፣ በረከትን ተቀብለን ብንመጣ ኃጢያታችን ምኑ ላይ ነው?።

ሮሜ 15÷31-32 "በእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ ወደ እናንተ መጥቼ ከእናንተ ጋር እንዳርፍ በይሁዳ ካሉት ከሚታዘዙ እድን ዘንድ ለኢየሩሳሌም ያለኝ አገልግሎቴ ቅዱሳንን ደስ የሚያሰኝ ይሆን ዘንድ ጸልዩ" ቅዱስ ጳውሎስ እንኳን እስከ ሦስተኛው ሰማይ ተነጥቆ እግዚአብሔርን በክብር ማየት የቻለ ሐዋርያ ዝቅ ብሎ ቅዱሳኑን ከማገልገሉ ባሻገር ለአገልግሎቱ መሳካት ምዕመናን በጸሎታቸው እንዲያግዙት ይማጸናቸዋል" እንዳንዶች እንደሚሉት ቅዱሳንም እኛም እኩል ነን። ለምን አገለግላቸዋለሁ? አላለም። ጌታስ ያስተማረን ዝቅ ብሎ ማገልገልን አይደለምን?

ማር 10÷43-45 "በእናንተስ እንዲህ አይደለም ነገር ግን ማንም ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ ባሪያ ይሁን። እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም"። ሉቃ 22÷27 "እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ"።

ዓለማትን የፈጠረ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ እንኳን የሰው ልጆችን ሊያገለግል መጥቷልና ዝቅ ብሎ የባሪያዎቹን እግር በማጠብ ትህትናውን ገልጿል ዮሐ 13÷2-17 "ባሪያ እኮ ከጌታው አይበልጥም" ጌታ ተንበርክኮ ባሪያዎቹን ካገለገለ እኛ ሊያውም ለሚበልጡን የቅዱሳን አገልግሎት ተንበርክከን ብንታይ ምን ያስነውራል? ስህተቱስ ምን ላይ ነው? ጌታችን "ከእኔ ተማሩ" ያለንን ቃል በምን ላይ ተግባራዊ እናደርገው? ማቴ 11÷29

ባሪያዎቹን በማገልገል አብነት የሆነው ክርስቶስ እርሱም

ኢየሩሳሌም ድረስ እየሄደ ቅዱሳንን በማገልገል ጌታውን መስሎታል
1ኛ ቆሮ 11÷1 "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ
ያለን ቅዱስ ጳውሎስ ለዚህ ነበር።

ዛሬ አንዳንዶች ድንግል ማርያምን ስናገለግላት ውስጣቸው
ይቆስላል። በመሠረቱ ቅዱሳኙንም ለማገልገል እኮ መመረጥ ያስፈልጋል
እንዲያውም አንዳንዶች ከጌታችን የተማርነውን ይህንን ቅዱስ ተግባ
በሰማያዊ ስፍራ ምንም ዋጋ የማያስጥ እርባና የሌለው እንደሆ
ይናገራሉ። ነገር ግን ዕብ 6÷10 "እግዚአብሔር ቅዱሳንን ስላገለገላች
እስከ አሁን ስለምታገለግሏቸው ያደረጋችሁትን ሥራ ለስሙ
ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ አመጸኛ አይደለም" ቅዱሳን
በማገልገላችን ለሰውም ስለምናሳየው ፍቅር እግዚአብሔር ዋጋችን
በሰማይ የሚረሳ አመጸኛ አይደለም ቅዱሳንን ማገልገል ተገቢ ያል
የሚመስላቸው ሰዎች ካሉ የእግዚአብሔርን ቃል መቃወማቸው ነው
"እራሱ ባለቤቱም ለቅዱሳን የምናደርገውን አገልግሎት በሰማ
እንደማይረሳ በቅዱስ ጳውሎስ እያናገረ፤ እርሱን ማገልገል ዋጋ የለው
ማለት ከሥጋ የመነጨ ሀሳብ እንደሆነ ግልጽ ነው።" እነርሱ ግን አመ
እያደረጉት ነው። ስለሆነም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ይህንን ብናደር
ብፁዓን እንባልበታለን። ዮሐ13÷17

እንዲህ ብለን ስናስረዳቸው ተቃዋሚዎች አንድ መልስ ያዘጋጁ
ይኸውም "በእርግጥ ክርስቶስ ተከታዮችን በማገልገል ለቅዱሳ
የሚገባውን አገልግሎት አሳይቶናል። ነገር ግን እርሱ ቅዱሳን
ያገለገላቸው በሥጋ አብሯቸው ስላለ ነው። ዛሬ ቅዱሳኑን የት አግኝ
እናገለግላቸዋለን? እነርሱ በአካለ ነፍስ አይደሉምን? ይላሉ ጥያቄው
በጥያቄ ብንመልሰው ይመረጣል። ተጠራጣሪዎች እራሳቸ
እግዚአብሔርን እናገለግለዋለን ይላሉ። እርሱን የት አግኝተውት ነ
የሚያገለግሉት? መልሳቸው ምን ይሆን? አዎን እግዚአብሔር በመን
አብሮን እንዳለ በማመን እናገለግለዋለን እነርሱንም እንዲሁ። ሆኖም
ይህ እንቢተኛ ልቦናቸውን ለማጽናት የሚጠቀሙበት ምክንያት
አያዛልቃቸውም።

ቅዱሳን እንኳን ሊያማልዱ በእሳት ያጠፋሉ። እንዴት?

"ጆሮአችን ጉድ ሳይሰማ አልውል አላድር አለ" ከማሕጸንና
...ን ጉድ ይወለዳል ይባል የለ? ሰዎች ቅዱሳንን አያማልዱም ሲሉ
...ም ይደንቀን ነበር። አሁን አሁን ደግሞ በተለይ በአውሮፓውያኑ
... ዓለም ያበቀለቻቸው እንክርዳዶች የእግዚአብሔርን ቅዱሳን
... ማስተማር ከጀመሩ ውለው አደሩ። ቅዱሳን እንኳንስ
...ማልዱና ድህነትን ሊያስጡ ይቅርና በእሳት የሚያጠፉና የሚቀስፉ
...ቸው ሌላ ርህራሄያቸውን አናውቅም የሚሉ ክፍሎች ተነስተዋል።

ምሥጢሩን ባይረዱትም ለዚህ የሞት ስብከታቸው አብነት
...ያደርጉት ኤልያስ ለበዓል (ለጣኦት) በሚንበረከኩት በአክአብ
...ት ላይ እሳት ማዝነቡን፣ 1ኛ ነገ 1÷1-16 ቅዱስ ገብርኤል ዘካሪያስን
... ማድረጉን ሉቃ 1÷19 እኒህ ኮከብ ጥቅሶቻቸው ናቸው። በዚህ
... ስብከታቸው ምዕመናኑን የክህደት ሰለባ ሊያደርጓቸው ስለሚችሉ
... ለሰጥበት እገደዳለሁ።

መልስ

በኤልያስ ዘመን እሳት መውረዱ፣ ዝናብ መቅረቱ ስለ አራት
... ምክንያት ነው።

1ኛ እሳት ከሰማይ መውረዱ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው።
2ኛ ኤልያስን ሊገድሉት በመምጣታቸው ነው።
3ኛ ኤልያስ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀናኢ ስለሆነ ነው።
4ኛ እግዚአብሔር የወዳጁ የኤልያስ ክብር እንዲገለጽ በመሻ
ነው።

1.1 <u>ፈቃደ እግዚአብሔር ነው</u>። መዝ 104÷14-15
"የቀባኋቸውን አትዳስሱ በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ሰወ
ክፉ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም ስለ እነር
ነገሥታትን ገሠጸ በምድርም ላይ ረሀብን ጠራ" ይላ

ነቢያቱን እንኳንስ ሊገድሉበት ይቅርና አትዳስሱ ያለ
አምላክ አክዓብ ኤልያስን ሊያጠፋው 150 (አንድ መቶ
ሀምሳ) ሠራዊት ሲልክ እግዚአብሔር ተመልክቶአል፡
እሳት ከሰማይ እንዲወርድ ኤልያስ ይጸልይ እንጂ ዳዊት
የተናገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ የእግዚአብሔር ሙሉ
ፈቃድ ሆኖ እሳት ከሰማይ ወረደ። ያለ እግዚአብሔር
ፈቃድ አንዳችም አይሠራምና ዮሐ 15÷5

<u>ስለ አነርሱ ነገሥታትን ገስጸ በምድርም ላይ ረሀብ</u>
<u>ጠራ</u> ብሎ እግዚአብሔር በዳዊት ያናገረውን ትንቢት
ይፈጽም ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ንጉሥ
አክአብ በድርቅ (በረሀብ) ተገሰጸ እንጂ ኤልያ
አያማልድም ብለን ልንጠቅስ የሚያስችለን ጥቅ
አይደለም።

ፈርኦን የአብረሃምን ሚስት ሣራን ቢነጥቅበት እግዚ
ብሔር ፈርኦንና የቤቱን ሳዎች በታላቅ መቅሰፍት መ
ዘፍ 12÷10-17 ይህ የሆነው አግዚአብሔር በነቢያቴ ክ
አታድርጉ ያለውን ቃል ፈርኦን በመተላለፉ የመ
መቅሰፍት እንጂ አብርሃም የሚወቀስበት አንዳች
ምክንያት የለም የኤልያስም እንዲሁ።

1.2. <u>ኤልያስን ሊገድሉት በመምጣታቸው</u> አሪት ሰውን የገ
ይገደል፤ ደምን ያፈሰሰ ደሙ ይፍሰስ ትላለች ዘፍ 9
የአክአብ ሠራዊት ኤልያስን ሊገድሉት አስበው መ
በእነርሱ አእምሮ ውስጥ ኤልያስ ሞቶአል። ሕሊና
መቃብረ ኤልያስ ነው። እንደ ብሉይ ኪዳን ህግ የገ
መገደል ስላለበት በእሳት ጠፉ (ሞቱ) የኦሪት ትእ
ይፈጸም ዘንድ መሞታቸውን ሳናውቅ ጨካኝ ና
አያማልዱም ለማለት ምን ያስሮጣል?

1.3. <u>ኤልያስ ለእግዚአብሔር ቀናኢ በመሆኑ</u> ሰዎች በዘ
ለአግዚአብሔር ኃይል ቦታ ሳይሰጡ ክብሩን ለበዓ

ለብኤልዜቡል (ለጣኦት) በመስጠታቸው ኤልያስ ለአምልኮተ እግዚአብሔር ቀና። ዝናምን አቆመ። ይህን ያደረገው ሰዎች የእግዚአብሔርን ኃይል አውቀው ወደ አምልኮቱ እንዲመለሱ እንጂ ለጭካኔም አልክነበረም። ቅዱስ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ቀንቶ የጽድቅ ጠላት የሆነውን የጠንቋዩን የበራየሱስን ዓይን እንዳጠፋው ማለት ነው። ሐዋ 13÷6-12 ኤልያስ ጨካኝ ቢሆንማ ኖሮ መበለቲቱ ሴት አንድ ልጇ ሞቶባት ስትጨነቅ እያየ ዝም ማለት በቀለለው ነበር። ግን ጸልዮ ከሞት አስነስቶ ሰጣት። 1ኛ ነገ 17÷27-22

1.4. <u>የኤልያስ ክብር ይገለጽ ዘንድ፤</u> እግዚአብሔር የወዳጆቹ ክብር ተዳፍኖ እንዲቀር አይፈልግም። ይልቁንም እንደምናምንቴ በሚመለከቷቸው ዘንድ የክብራቸውን ፋና ይንጸባረቅላቸዋል።

ቅዱስ እስጢፋኖስ ጠላቶቹ አይሁድ እየወገሩት ፊቱ በመንፈስ ቅዱስ እንደመልአክ እያበሩ ምስጢረ ሥላሴ ተገልጾለት ወልድን በጌትነቱ ያየው ነበር። (ህልውና ሥላሴን አይቷል) የእስጢፋኖስ ትልቁ ክብሩ ይህ ነው። የሐ ሥ 6÷14-15 የሐ ሥራ 7÷55-56 ሥላሴን ከማየት የበለጠ ክብር የለምና።

በመሆኑም በኤልያስ ጸሎት ተአምራት ተደርጎ እግዚአብሔር ክብረ ኤልያስን ሲገልጽ እሳት ከሰማይ አወረደ። የኤልያስን ነፍስ ከክፉዎች እጅ ለመጠበቅ በተጨማሪም ይህንን አድርጓል። መዝ 90÷10 "እግዚአብሔር የቅዱሳንን ሰውነት ይጠብቃል ከኃጥአንም እጅ ያድናቸዋል" ተብሎአልና።

<u>ቅዱስ ገብርኤል ዘካሪያስን ለምን ዱዳ አደረገው?</u>

1.1 በመጽሐፈ ቅዱስ ለመሰናከል ፈጣን የሆኑ ክፍሎች ቅዱስ

ገብርኤል ዘካሪያስን ዲዳ በማድረጉ መላእክት እንኳንስ ሊያማልዱና ሊያድኑ ይቅርና እንደበት ይዘጋሉ በማለት ሲሰናከሉ ይስተዋላሉ።

<u>መልስ</u>

ዘካሪያስ ምሁረ ኦሪት ነው። አብርሃምና ሣራ በእርጅና ወራታቸው ልጣቸው እርሶ፣ ጉድንዳቸው ተምሶ፣ ሰውነታቸው ሙቀት ተለይቶት የማይሳነው እግዚአብሔር ልጅ እንዳሰጣቸው ያውቃል። እያወቀም መልአኩ ሚስትህ ኤልሳቤጥ ልጅ ትወልድልሀለች ሲለው ይህ እንዴት ይሆናል? ሲል ተጠራጠረ እግዚአብሔር እንደማይሳነው በአብርሃምና በሣራ አስተምሮት ሳለ የተማረውን ባመለማድረጉ ኃጢያት ሆነበት። ያዕ 4÷7 "በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሰራው ኃጢያት ነው" ስለተባለ ቅዱስ ገብርኤልም አግባባዊ ቅጣት ቀጥቶታል።

እንዲሁም ሚስቱ ኤልሳቤጥ በመምከኗ ልጅ እንዲሰጣቸው እያዘኑ ይጸልዩ ነበር። እግዚአብሔር ቀኑን ጠብቆ የመሻቱን ሰጠው። የልጁን መወለድ በአብሳሪ መልአክ አስቀድሞ ቢነገረውም ቃሉን አልተቀበለውም። ልጅ ካልፈለገ ለምን ጸለየ? ከጸለየስ የጸሎቱን ዋጋ ለምን አልተቀበለም? ይህ ሁሉ የሚያስቀጣው በመሆኑ ተቀጣ እንጂ ቅዱስ ገብርኤልን ጨካኝ አድርገን መላእክት አያማልዱም የምንልበት ታሪክ አይደለም። የቅጣቱ ምክኒያታዊ ምስጢር ሳይገባቸው መላእክት አያማልዱም ለማለት ባይጣደፉ መልካም ነው። እስራኤል በፋርስ ባቢሎን ተግዘው ለሰባ (70) ዘመን ካሉበት ባርነት በጸሎትና በምልጃ፣ በርህራሄ ያላቀቃቸው የእግዚአብሔር መልአክ አይደለምን? ዘካርያስ 1÷12-17 ሰልስቱ ደቂቅን ከእሳት እቶን ያዳነ ቅዱስ ገብርኤል አይደለምን? ዳን 3÷95-26 ጨካኝ ቢሆን ነውን? አይደለም።

<u>ቅዱሳን ለሚጨክኑባቸው ሳይቀር ያማልዳሉ</u>

የሐ ሥራ 7÷58 ከከተማ ወደውጪ አውጥተው ወገሩት ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚባል በአንድ ጎበዝ እግር አጠገብ አኖሩ እስጢፋኖስም ጌታ ኢየሱስ ሆይ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጣራ

ይወግሩት ነበር ተንበርክኮም: ጌታ ሆይ <u>ይህን ኃጢያት አትቁጠርባቸው</u> ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ ይህንንም ብሎ አንቀላፋ"።

እስጢፋኖስ ይህን የጸለየው ለሚወዱት ሳይሆን እራሱን በድንጋይ ለሚቀጠቅጡት ጠላቶቹ ነው። <u>ይህን አትቁጠርባቸው</u> ባለው መሠረት በደሉ ሳይቆጠርበት በእስጢፋኖስ ምልጃ ምህረት ከተደረገለት አንዱ ሳውል የተባለው ቅዱስ ጳውሎስ ሆኖ ተገኘ። "እግዚአብሔር ይመስገን" ቤተክርስቲያን ጳውሎስን የመሰለ ብርቅዬ ሐዋርያ ያገኘችው በቅዱስ እስጢፋኖስ አማላጅነት ጭምር ነው። እንግዲህ ምን እንላለን ቅዱሳን የሚጨክኑባቸውን እንኳ ወደ እግዚአብሔር ክብር ሲስቡ ለሚያከብሩን ጨካኞች ናቸው ያስቀስፋሉ እንበልን? ይህንን ከእኛ ያርቅ"።

<u>1 ቆሮ 4÷11-13</u> "እስከዚች ሰዓት ድረስ እንራባለን፣እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንከራተታለን በገዛ እጃችን እየሰራን እንደክማለን ሲሰድቡን እንመርቃለን ሲያሳድዱን እንታገሳለን ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን።"

ክፉ ለሚናገራቸው ወደ እግዚአብሔር የሚማልዱለት ከሆነ ለእኛ ለሚያፈቅራቸውማ እንደምን አብልጠው አያማልዱም? እንኳንስ ለሰውና በእሳት ሊያጠፉ እነሱስ ለጠላቶቻቸው ይራራሉ። ለእንስሳውና ለአራዊቱ ሳይቀር።

<u>ምሳ 12÷10</u> "ጻድቅ ሰው ለእንስሳት ነፍስ ይራራ
የኃጥአን ምህረት ግን ጨካኝ ነው።"

<u>ዘጸ 10÷16-17</u> "ፈርኦንም ሙሴንና አሮንን በፍጥነት ጠራ አምላካችሁንም እግዚአብሔርን እናንተንም በደለልሁ አሁን እንግዲህ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ ኃጢያቱን ይቅር በሉኝ። ይህንንም ሞት ብቻ ከእኔ ያርቅልኝ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔርን ለምኑ አላቸው። ሙሴም ከፈርኦን ፊት ወጣ ወደ <u>እግዚአብሔርም ለመነ</u>።"

<u>1ኛ ነገ 13÷6</u> "ንጉሡም የእግዚአብሔርን ሰው አሁን ለምንልኝ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ፊት ለምን። እንጂ ወደ እኔ ትመለስ ዘንድ

ስለ እኔ ጸልይ አለው። የእግዚአብሔርም ሰው እግዚአብሔርን ለመነ
የንጉሡም እጅ ወደእርሱ ተመለሰች እንደቀድሞውም ሆነች።"

ዘፀ 8÷28-30 "ፈርዖን ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ በምድረ በ[illegible] ትሰው ዘንድ እለቃችኋለሁ ነገር ግን ርቃችሁ አትሂዱ ጸልዩልኝ አለ። ሙሴም እነሆ ካንተ ዘንድ እወጣለሁ የህዝብም መንጎች ከፈርኦን ከባርያዎቹ ከህዝቡም ነገ እንዲሄዱ ወደ እግዚአብሔር እጸልይልሀለሁ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ይሰዋ ዘንድ ህዝቡን እንዳይለቅ ፈርዖን እንደገና አያታልለን አለ። ሙሴም ከፈረዖን ዘንድ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም ጸለየ።

ሙሴ በግብጽ የእሥራኤልን ልጅ በባርነት ላስጨነቀ ለጠላ[illegible] የጸለየ ለእኛ ለወዳጆቹማ እንዴት አይጸልይልን? ኢዮርብአም በ[illegible] ኃጢያቱ እጁ ብትደርቅበት የእግዚአብሔር ሰው ጸልዮ እጁ[illegible] ካለመለመለት ቅዱሳን በኃጢአት የደረቀ (የሰለለ) ሕይወታችን[illegible] በጸሎታቸው እንዴት አያለመልሙ? ቅዱሳን ጭካኔ ቢኖራቸው[illegible] ስለጠላቶቻቸው በመጸለይ ፈንታ ጠላቶቻችንን አጥፋልን ብለው በጮኹ ነበር። አላደረጉትም።

ቅዱሳን ለሰው አይተርፉም እንዴት ?

ለብዙዎች እራስ ምታት የሆነባቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅስ ነ[illegible] ሕዝ 14÷21-22 ተጠራጣሪዎችም በእምነታቸው ቆመው ያሉ[illegible] ክርስቲያኖች በጠማማ ትርጉማቸው ገዝግዘው ለመጣል ሲሯሯጡ[illegible] ይታያል። ቤተክርስቲያናችን ግን የትርጉም እመቤት ነችና እን[illegible] የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ለምን፣ ለማንና መቼ እንደተናገረ እያመስጠ[illegible] በሃይማኖት ጡት ልጆቿን ታሳድጋለች።

በዚህ ጥቅስ ላይ "እነዚህ ሦስት ሰዎች ኖህና፣ ዳንኤል ኢዮብ[illegible] ቢኖሩባት በጽድቃቸው የገዛ ነፍሳቸውን ብቻ ያድናሉ እንጂ ወንዶ[illegible] ሴቶች ልጆቻቸውንም አያድኑም" የሚል ሦስት ተከታታይ አባባ[illegible] አሉ። ይህን በመያዝ ቅዱሳን በእርግጥ ድነዋል። ይሁን እንጂ ማንን[illegible] ሊያድኑ አይችሉም የሚሉ ክፍሎች አሉ።

መልስ

የእግዚአብሔር ቃል በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ እንደመሆኑ ይህ ቃል ስለሁለት ምክንያት የተነገረ ነው።

1ኛ ጥቅሱን ከመጀመሪያው እንደምናነበው የእሥራኤል ልጆች በጣኦት ፍቅር ተተብትበው ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር አስቆጡት። ይሁን እንጂ በዚያው ላይ ልውልን ባሳዘነ ህይወታቸው በቅዱሳን አባቶቻቸው [illegible] ጀመር ይህ ግን ከንቱ ትምክህት ነበር። ለምሳሌ ቤተ አይሁድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ድንጋይ እያነሱ አብርሃም አባት አለን ብለው ይመኩ ነበር። ዮሐ 8÷39 ፈጣሪ ላይ ድንጋይ ከማንሳት የከፋ አልነበረም። እናም አይሁድ አብርሃም አለን በማለታቸው ይድናሉ የሚል [illegible] ላይ አንደርስም። መጥምቁ ዮሐንስም በዚህ ከንቱ ትምክህታቸው እንደማይድኑ ነግሯቸዋል። ማቴ 3÷8-9 በሕዝቅኤልም ዘመን የተከሰተው ክስተት ይህንን ይመስል ነበር። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ጌትነት አቅመዝምዘው በመጣል ክብሩን በጣኦት [illegible] ሲያበቁ ዘወር ብለው ደግሞ በአባቶቻቸው በኖህ በኢዮብና በዳንኤል ቅድስና ላይ ትምክህታቸውን አስደገፉ። መሠረት የሆነ እግዚአብሔርን ትተውታልና ኖህም ቢሆን ኢዮብም፣ ዳንኤልም የገዛ ነፍሳቸውን ያድናሉ እንጂ ልጆቻቸውን አያድኑም ተብሎ በነብዩ [illegible]።

ፈርዖን ሙሴን ጸልይልኝ ብሎት ነበር ሙሴም ጸልዮለት ነበር። በጸለየለትም ፈርዖን ባህረ ኤርትራ ከመስጠም አልዳነም። የቅዱሳን [illegible] የማያድን ሆኖ አልነበረም። ነገር ግን ፈርኦን ሙሴን ጸልይልኝ [illegible] በፊት የሚመካበትን ጣዖት መጣል ነበረበት ዘጸ 8÷28-30 ነብዩ [illegible] ለሳኦል ቢጸልይለት እግዚአብሔር ሳሙኤልን እንዳትጸልይለት [illegible] ሳሙ 16÷1 የእግዚአብሔር ሳሙኤልን መከልከል [illegible] ድህነት የማያሰጥ ስለሆነ አይደለም። በቅድሚያ በሳኦል [illegible] የትምክህት ጣዖት መወገድ ስለነበረበት ነው።

በሕዝቅኤል የተነገረው ቃል ይህን ይመስላል። በጣዖት ላይ [illegible] ትተው ቅዱሳንን ብቻ በመጥራት ሊድኑ የሚፈልጉ ሰዎች

ስለነበሩ ለእነርሱ የተነገረ ቃል እንጂ ከጣዖት እራሳችንን ለይተን፣ እግዚአብሔርን እያመለክን በሚገጥመን የኃጢአት ጽንት አማልዱን ለምንላቸው ለእኛ የተነገረ አይደለም።

2. ቀጣዩ ትርጉም እግዚአብሔር ኖህም ቢሆን እዮብም ዳንኤልም ቢሆን ራሳቸውን ያድናሉ እንጂ ልጆቻቸውን አያድኑም" ያለው በአዳም ከመጣብን በደል (መርገም) ከሲኦል ቀጣት ሊያድኑን እንደማይችሉ ሲያጠይቅ ነው።

<u>እነርሱ እራሳቸውን ያድናሉ እንጂ</u> ማለቱ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ቅዱሳን በትሩፋታቸውና በቅድስናቸው ነፍሳት ሁሉ በሲኦል ሲሰቃዩ እነርሱ ግን ነባልባሉ ሳያገኛቸው በረድኤተ እግዚአብሔር ተጠብቀው መኖራቸውን ሊያስገነዝበን ነው። ቀሪው የሰው ልጅ ግን የሲኦልን የመከራ ጽዋ ሲጎነጭ 5,500 ዘመን ኖሯል።

በእርግጥ ቅዱሳን ልጆቻቸውን ከመርገመ አዳመ ሊያድኑ አልቻሉም ነበር። ከዚህ ስብራታችን የጠገነን የእግዚአብሔር የባህርይ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው። ከዚህ ላይ የፍጡር አማላጅነትም ሆነ ቅድስና ሊገባ አይችልም። በተረፈ ግን ለሌሎች ኃጢአቶች ቅዱሳን ልጆቻቸውን በተሰጣቸው ቃል ኪዳን መታደግ (ማማለድ) ይችላሉ።

<u>ሦስቱ ቅዱሳን ልጆቻቸውን ሲያድኑ</u>

<u>ኖህ</u> :- በኖህ ቅድስና እንኳንስ ልጆቹ የምድር እንስሳት፣ የዱር አራዊት፣ አእዋፋት ሁሉ ከንፍር ውኃ ጥፋት <u>ድነዋል</u> መላው ቤተሰቡም በኖህ ቅዱስና በታነጸችው መርከብ ውስጥ ድህነትን ተላብሰዋል። ዘፍ 7÷7-14

የኖህ ንጽህና የሳበው ጌታ ከጥፋት ውኃ በኋላ ለኖህ ዳግመኛ እስከዓለም ፍጻሜ ምድርን በንፍር ውኃ እንደማያጠፋት ቃል ኪዳን ሰጥቶታል። እስከ ህልፈተ ዓለም ድረስ የኖህ ልጆች ዳግመኛ ከንፍር ውኃ እንዲድኑ ኖህ ለመዳናቸው ምክንያት አልሆነም? ዘፍ 9÷8-17

<u>ኢዮብ</u>:- የኢዮብ ጓደኞች ኢዮብን በማሳዘናቸው የቅዱሳኑ ፍቅ[illegible]

[illegible] የሚለው እግዚአብሔርን አስቆጡት። አግዚአብሔርም ወደ ኢዮብ [illegible] እርሱ እንዲጸልይላቸውና እንዲድኑ እራሱ ነግሯቸዋል። ቅዱሳን [illegible]ቸው የእምነት ልጆቻቸውን እንደሚያድኑ ስለሚያውቅ እንደሆን [illegible]። ኢዮ 42÷8

እኛም በሃይማኖት እያለን ነገር ግን (በባህርይ ደካማነት በሚመጣ [illegible] ጉድለት ብንወድቅ እኛ ፈቃደኛ ከሆንን አምላካችን ስለ ቅዱሳኑ [illegible] ያነሳናል። "እመን ይደርግልሀል አይደል የሚለው ቃሉ" [illegible] በላይ ደግሞ የቅድስት ድንግል ማሪያም የአደራ ልጆች የሆንን [illegible] እንቆርጥም። አግዚአብሔርም የእናቱን ልጆች ያድናቸዋልና። [illegible] ግን ይበቀላል። ኢሳ 49÷25-26 "እግዚአብሔር ግን እንዲህ [illegible] በኃያላን የተማረኩ ይወሰዳሉ። የጨካኞችም ብዝበዛ ያመልጣል <u>ካንቺ</u> <u>[illegible] የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ</u> ልጆችሽን አድናለሁ። አስጨናቂዎችሽንም [illegible]ውን አስበላቸዋለሁ። እንደ ጣፋጭ ወይን ጠጅም ደማቸው[illegible] [illegible] ይሰክራሉ" ይላል። "በደም ከመስከር አግዚአብሔር ይሰውረን" [illegible] ጠላት መሆን ዕጣው ኪዚህ አይዘልም። ቅዱስ ጳውሎስ [illegible] ጥፋት ነው"። ብሎ የለ? ፊል 3÷18-19 እኛ ግን [illegible] ከቅድስት ድንግል ማሪያም ጀምሮ የቅዱሳን የቃል ኪዳን [illegible] እንደምንድንባቸው (ጽድቃቸው እንደሚተርፈን) እምነታችን [illegible]ውም በቅዱሳት መጻሕፍት የተመሰከረ ነው።

<u>ዳንኤል:-</u> ናቡከደናጸር ህልም አልሞ የሚፈታለት አጣ። [illegible] የተቀመጡት ጠቢባን ፍቺውን ተሰወረባቸው። ንጉሡ [illegible] ያለውን የንዴት ረመጥ መቆጣጠር ባለመቻሉ መኳንንቱን [illegible] ጠቢባኑን ወስደው እንዲገድሏቸው አዘዘ። ዳን 2÷14

ጠቢባኑ ወደ ሞት አደባባይ ሲወሰዱ ነቢዩ ዳንኤል አገኛቸው። [illegible] እንደሚሄዱ መኳንንቱን ቢጠይቅ እውነቱን ዘርዝረው [illegible] ቅዱሳን የሰው ሕይወት ከራሳቸው በላይ ያስጨንቃቸዋልና [illegible] የጠቢባኑን ሕይወት ከሞት ለማትረፍ ተፋጠነ። ንጉሡ ፊት [illegible] ያህል ጊዜ እንዲሰጠው ህልሙንም በዚህ ጊዜ ውስጥ [illegible] ጠቢባኑን ከሞት እንዲድኑ አጥብቆ ለመነ። ከንጉሡ [illegible] ቃል ስንቆ ወደሰለሰቱ ደቂቅ ጉዞውን አቀና። ከሰማይ [illegible] ምሥጢሩን ይማልዱ ዘንድ አስታወቃቸው። እርሱም በጾምና

በጸሎት ወደፈጣሪው ማለደ የንጉሡንም ራዕይ ምስጢር በሌሊት ተረዳ ለንጉሡም ፈታለት። ንጉሡም በመደሰት ለነቢዩ የጸጋ ስግደት ሰገደለት። ስለ ዳንኤልም ብሎ ናቡከደናጾር በጠቢባኑ ላይ የወሰነውን የሞት ትዕዛዝ ቀይሮ ሕይወትን ለማግኘት ችለዋል። ለጠባኑ ያልተገለጸ የራዕይ ምስጢር ለዳንኤል መገለጹ ቅድስናውን ያሳየናል። በእርሱም ቅድስና ጠቢባኑ ከሞት እንደዳኑ ግልጽ ነው። እንደውም የአናንያ የአዛርያ የሚሳኤል ጸሎትም ጭምር ለጠቢባኑ ከሞት መትረፍ ምክንያት ነው። ታዲ[illegible] ትርጉሙ ሳይገባን ቅዱሳን ለሰው አይተርፉም በሎ ማስተማር ኃጢአ[illegible] አይሆንም? ቅዱሳን ሰዎችን ከታዘዘባቸው መቅሰፍት በጸሎታቸው[illegible] አድነዋል።

አንድም ጻድቅ የለም? እንዴት?

የቅዱሳን ተቃዋሚዎች ለኃጥአን የተነገረውን ለቅዱሳን እየሰ[illegible] መሳደብ ልማዳቸው ነው። ራሳቸውን በጽድቅ ኮርቻ ላይ አስቀምጠ[illegible] አንድም ጻድቅ የለም በማለት ለቅዱሳን ክብር ሲነፍጓቸው[illegible] የአማላጅነትም ጸጋ እንደሌላቸው አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ። ለ[illegible] አባባለቸው የሚጠቅሱት ሮሜ 3÷11-18 አንድም ጻድቅ የለም አስተዋ[illegible] እንኳ የለም" የሚለውን ነው።

ይህንን ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ስለሁለት ነገር ነው።

1ኛ. በአዳም ምክንያት የገባው መርገም ሰዎችን ከክብር አጉድሎ ስለነበር የጨለማውን ዘመን እያሰበ መናገሩ ነው።

2ኛ. የተናገረው ለሮሜ ሰዎች ተግሳጽነው። በጊዜው ሮሜ ው[illegible] ትልቅ የችግር እሳት ይነድ ነበር በሮሜ ውስጥ ያሉ አሕ[illegible] አይሁድ በእምነት ተከፋፍለው በመካከላቸው ያለውን የመለ[illegible] ረመጥ ሊያጠፋው የሚችል ባለመገኘቱ ፍቅር በሮሜ ሰ[illegible] መካከል መንምና ጠፋች በዚህ ጊዜ ከጻብ ውስጥ ሳ[illegible] የወገኖቿ ፍቅር እጦት ያስጨንቃት የነበረች የክርን[illegible] ቤተክርስቲያን አገልጋይ የምትሆን ፌቨን ለቅዱስ ጳውሎስ [illegible]

ቆሮንቶስ ሂዳ ልትነግረው ወሰነች። በጊዜው ቅዱስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ወደብ ላይ ሲያስተምር ተይዞ አላውያን ነገሥታት በወህኒ ጥለውት ነበር። እርሱ ቢታሰር ቃሉ አይታሰርም ብላ ፌቨን ሴትነቷ ሳይበግራት ቅዱስ ጳውሎስ ወደታሰረበት ወህኒ አመራች በሮሜ ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ሁሉ ነገረችው። እርሱም የአብያተ ክርስቲያናት ነገር የሚያስጨንቀው ቀናኢ አባት በመሆኑ 2ኛ ቆሮ 11÷28 የችግሩን ቀንበር ለመስበር ወህኒ እንዳለ የሮሜን ሰዎች ሊያስማማ የሚችል ጽሑፍ ጽፎ የሮሜን መልዕክት በፌቨን በኩል ላከ። ሲልክም መልዕክቱንም ሆነ ፌቨንን በሚገባ እንዲቀበሉ አስጠንቅቆ ነበር። ሮሜ 16÷1 "ፌቨንን አደራ ብዬ እችኋለሁ ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሏት እርስዋ ለብዙዎች ለእኔም ለእራሴ ደጋፊዬ ነበረችና ከእናንተበምት ፈልገው በማናቸውም ነገር እርዱአት" ብሎ መልዕክቱን ላከ በዚህ መሠረት ለሮሜ ሰዎች የተጻፈበት ዋናው ዓላማ የተለያዩትን ወገኖች በምክርና በተግሳጽ አንድ ለማድረግ ነው።

ቅዱስ ጳውሎስ የሮሜን ሰዎች በመልዕክቱ ሲገለጽ "አንድም ጻድቅ የለም አስተዋይም የለም እግዚአብሔርን የሚያገለግል የለም ሁሉም ተሳስተዋል በአንድነት የማይጠቅሙ ሆነዋል ቸርነት የሚያደርግ የለም አንድስ እንኳ የለም ጉሮሮአቸው የተከፈተ መቃብር ነው በምላሳቸው ሸንግለዋል" አለ [illegible] በሌለበት ጽድቅ የለምና በመካከላቸሁ ጻድቅ የለም ያላቸው [illegible] ነው።

[illegible] ቅዱስ ለምንና ለማን እንደተነገረ ያልገባው [illegible] ይህንን ቃል አንግቦ ጻድቅ የለም ጻድቅ ጌታን [illegible] ነን እያለ ራሱን በትዕቢት ክቦ ቅዱሳንን [illegible]

[illegible]

[illegible] ጻድቅ ነኝ፥ እግዚአብሔር ግን ፍርዴን አስወገደ"
[illegible] ቅዱስ ነኝና እናንተም ቅዱሳን ሁኑ"
[illegible] እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና ለእኔም ትሆኑ ዘንድ

ከአሕዛብ ለይቼአችኋለሁና ቅዱሳን ትሆኑኛላችሁ"

1ኛ ዮሐ 3÷7 "ልጆች ሆይ ማንም አያስታችሁ እርሱ ጻድቅ እንደሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው" በዚህ ቃል መሠረት ጽድቅን ያደረጉ አበው ሁሉ ጻድቃን (እውነተኞች) ተብለው ይኖራሉ። ይህንን እያወቀ ቅዱስ ጳውሎስ ጻድቅ የለም አይልም።

መዝ 31÷11 "ጻድቃን ሆይ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ሐሴትም አድርጉ"

ሉቃ 1÷6 "ሁለቱም በጌታ ትዕዛዝና ህግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ (ዘካሪያስና ኤል ሳቤጥ)"

ማቴ 5÷45 "እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና በጻድቃንና በኃጢያተኞች ዝናብን ያዘንባልና"

ዘፍ 6÷9 "ኖህ በትውልዱ ጻድቅ ፍጹምም ሰው ነበር"

ሉቃ 2÷25 " እነሆም በኢየሩሳሌም ስምኦን የሚባል ሰው ነበር ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር ጻድቅ ትጉህም ነበር"

ሁሉም ካህን ነው እንዴ?

አንዳንድ የዋህን ከቅዱስ መጽሐፍ ጋር ብስለታዊ ግንኙነት ስለሌላቸው በጥሬ ቃል ተታለው ሁላችን ካህናት ነን በማለት እራሳቸውን ሾመው ተቀምጠዋል። ከሁሉም የሚደንቀን ሴቶቹ ሳይቀሩ ካህናት ነን በማለት እጃቸውን ወደ ሰው እራስ ላይ ሲጭኑ ስናይ ሳናዝን የምናልፈው አይደለም።

በመሠረቱ ሁሉም ሰው ካህን ሊሆን አይችልም። በመጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስ አስራ ሁለቱን ሐዋሪያት ከአስራ ሁለቱ ነገደ እስራ ኤል ለክህነት በመረጣቸው መሠረት እርሱ ለክብሩ የሚመርጣቸውን ካህናት በጸጋ አይለያቸውም። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ያለምክንያት እኔ ከዓለም መረጥኳችሁ አላላቸውም።

ለክህነት መርጧቸዋልና። ዮሐ 15÷18-19

ደግሞስ ሁሉ እረኛ ከሆነ መንጋው ማን ሊሆን ነው? ቅዱስ ጳውሎስ ኤፌ 4÷11 "እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋሪያት ሌሎችም ነብያት ሌሎችም ሰባክያን ሌሎችም እረኛና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" አለ እንጂ ለሁሉም እረኛ (ካህን) እንዲሆኑ ሰጠ አላለም።

ሁሉም ካህን ቢሆን ኖሮ በይሁዳ ፈንታ ሌላ ሰው መተካት ባላስፈለገም ነበር ነገር ግን ሊሆን ስለማይችል በርናባስና ማትያስ ዕጣ ተጣለላቸው እድሉ ለማትያስ ደርሶታል። ሁሉ ካህን ቢሆን ለሁለቱ ዕጣ መጣል ባላስፈለገም ሐዋ 1÷25-26።

በመጽሐፍ ቅዱሳችንም ሴት ልጅ ካህን ትሁን የሚል ስርዓት አንድም ቦታ የለም። ከመጸሐፍ ቅዱስ ውጪ ሰው የመሰለውን ስለተናገረ የሚሆን ነገር የለም። ሳጥናኤል ፈጣሪ ነኝ ስላለ አልሆነም።

ሁሉም ካህን ቢሆን ኖሮ የአሮን ልጆች ናዳብና አብዩድ ጥናውን ሰርቀው ሲያጥኑ ባልተቀሰፉም ነበር ዘሌ 10÷1-2 ባልተሰጣቸው የማይገባ ክህነት ሥራ ውስጥ ገብተው ስለተገኙ አይደለምን? ሁሉም ካህን ቢሆንማ ቅዱስ ጳውሎስ የመንፈስ ልጁ ጢሞትዮስን ወደ አንተ እጅህን ሁሉ ፈጥነህ አትሹም ባላለውም ነበር። ክህነት ለሁሉም ሰው የሚሰጥ ምስጢር ስላልሆ አይደለምን? አምላካችንም "እንደ ልቤ የሆኑ እረኞችን (ካህናትን) እሰጣችኋለሁ በዕውቀትና በማስተዋል ይጠብቋችኋል" ኤሬ 3÷15 አለን እንጂ ሁላችሁ ጠባቂዎች ናችሁ አላለንም ሁላችሁ ካህናት ነን ማለት ሁላችን ጠባቂዎች ነን ማለት ነው። ሁሉ ጠባቂ ከሆነ ተጠባቂ ማን ነው?

እንዲሁም ክህነት ይቅርና ሴት ልጅ በአደባባይ እንዳታስተምር መጽሐፍ አስቀምጦታል። ቆሮ 14÷34-35 "ሴቶች በማህበር ዝም ይበሉ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እልተፈቀደላቸውምና ሴት በማህበር መካከል መናገር ነውር ነውና ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤት ባሎቻቸውን ይጠይቁ።"

ሁላችን ካህን ነን የሚሉ ክፍሎች ትርጉሙ ቢፋለስባቸውም

አብነት አድርገንዋል የሚሉት የቅዱስ ጴጥሮስን ትምህርት ነው 1ኛ ጴጥ 2÷9 "እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚያስደንቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ የንጉሥ ካህናት ቅዱስ ሕዝብ የተለየ ወገን ናችሁ።" የሚለውን ነው።

ቅዱስ ጴጥሮስ ይህንን የተናገረው ለምስጢረ ክህነት አይደለም። ካህን የሚለው ቃል ተክህነ ከሚለው ግስ የወጣ ነው። ትርጉሙም አገልጋይ ማለት ነው። የንጉሥ ካህናት (አገልጋዮች) ናችሁ ሲል እግዚአብሔር በሰጠን የጸጋ ስጦታ ማገልገል እንዳለብን ሲናገር እንጂ ለምስጢረ ክህነት የተናገረው አይደለም።

ሁሉም ካህን ቢሆን ኖሮ ኦዝያን ያለ ሥልጣን ክህነት ቤተመቅደስ ገብቶ የክህነት ሥራ ሲሠራ ባልተቀሰፈም ነበር። 2ዜና 26÷17-23

<u>ታቦት ኃይል የለውም? እንዴት?</u>

ንዋየ ህሩይ ቅዱስ ጳውሎስ "በጥንቃቄ ተጠበቁ ቀናቱ ክፉዎች ናቸውና" ኤፌ 5÷16 ይለናል። አንባቢ ሆይ የሰው ልጆች ኃጢያት ሲበዛ (ሲከፋ) ጊዜውን ክፉ አሰኝቶታል። ጆሮአችን የክህደትንና የትዕቢትን ትምህርት (ድምጽ) በመስማት ደነቆረ። ታቦት ምንድን ነው? ኃይል የለውምኮ! እያሉ የትዕቢት ትምህርት የሚያስተምሩ ክፍሎች እንደ ችግኝ ፈልተዋል። ለዚህ አባባላቸው አብነት አድርገናል የሚሉት ለምን እንደተነገረ ባያውቁትም የሚከተለውን ጥቅስ ነው።

ኤር 10÷2-5 "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል። ... የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና ዛፍ ከዱር ይቆረጣል በሠራተኛም እጅ በመጥረቢያ ይሠራል በብርና በወርቅ ያስጌጡታል እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል። እንደተቀረጸአምድ ናቸው እነሱም አይናገሩም መራመድም አይቻላቸውምና ይሸከሟቸዋል። ክፉ መሥራትም አይቻላቸውም ደግሞም መልካም ይሠሩ ዘንድ አይቻላቸውም አትፍሩአቸው።" ይላል።

ብዙ ሰዎች የሚጎዱት የመጽሐፍ ቅዱስን ቁንጽል ሀሳብ ብቻ አንብበው በዚያች ጥቅስ ደርሶ ሰባኪ መሆን ስለሚፈልጉ ነው። ግን የሚቀጨን በጠባብነታቸው ጠፍተው ሰውንም ይዘው መጥፋታቸው ነው። ከላይ ያየነው አባባል የተነገረው ለጣኦት እንጂ ለታቦት አይደለም። ዝቅ ብለው ሳያነቡት ታቦትን በመናቃቸው እናዝንባቸዋለን። ለምሳሌ ቁጥር 8 ላይ ብንመለከት ከላይ ያነበብነው ሀሳብ ስለምን እንደተነገረ ይጨርስልናል። "በአንድ ጊዜ ሰንፈዋል ደንቁረውማል <u>ጣኦታት</u> የሚያስተምሩት <u>የእንጨት ነገር ብቻ ነው። የሠራተኛና የአንጥረኛ እጅ ሥራ የሆነ ከተርሴስ ጥፍጥፍ ብር ከአፌዝም ወርቅ ይመጣል ልብሳቸውም ሰማያዊና ቀይ ግምጃ ነው።</u> ሁሉም የብልሀተኛ ሥራ ናቸው። <u>እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው።</u> ብሎ ኤርምያስ ብልሀተኛ የሰው የሥራ ውጤት የሆነ የጣኦትን ከንቱነት፣ የእግዚአብሔርን እውነተኛ አምላክነት ግልጽ አድርጎ ያስቀምጠዋል። ተጠራጣሪዎች ዝቅ ብለው ቢያነቡት ምን ነበር? እኛ ግን ቃሉ ለታቦት ሳይሆን ለጣኦት እንደተነገረ ደግመን ለማየት እንሞክር። (በሁለቱ ቁጥሮች ላይ የተሰመረባቸው ቃላት ተባብረው ስለ ጣዖት እንደሚናገሩ እናገናዝብ።

<u>የአህዛብ ልማድ ከንቱ ነውና</u> አዎን በጣዖት ልማድ የሚመላለሱ የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነው። ከዱር የቆረጡትን እንጨት እያለዘቡ ያመልካሉና ዛፍ ከዱር ይቆረጣል አለ።

<u>በብርና በወርቅ ያስጌጡታል እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል።</u> ታቦት በችንካርና በመዶሻ ይቸነከራልን? ተደርጎም አይታወቅም። ነገር ግን አህዛብ ከእንጨት የሰሩትን የጣዖት ምስል በብርና በወርቅ ለብጠው ያስጌጡታል። ሕይወት የሌለው ስለማይቆምላቸው በችንካር ያቆሙታልና በችንካር ይቸነክሩታል ያለው ጣዖትን ነው። ታቦትማ እንዴት ይቸነከራል?

<u>እንደተቀረጸ ዓምድ ናቸው</u> በጣኦት የሚመኩ ሁሉ እንደተቀረጸ ዓምድ ናቸው። ታቦትን ለሰው ልጆች የሰጠ እግዚአብሐር አይደለምን? ዘፀ 32 እና እግዚአብሔር እንደተቀረጸ አምድ እንድንሆንና እንድንጠፋ ነው የሰጠን? ተቃዋሚ ክፍሎች

የሚናገሩትን ቢያውቁት መልካም ነበር።

- <u>እነርሱም አይናገሩም መራመድም አይቻላቸውምና ይሸከ ሟቸዋል</u> በተለይ ይህንን ቃል ለታቦት እንደተነገረ በማስመሰል ብዙዎችን ሲያሰናክሉ ይታያሉ። ነገር ግን አሕዛብ የቀረጿቸውን ጣዖታት መራመድ የማይችሉና በሰው ተሸካሚነት የሚንቀሳቀሱ መሆናቸውን ለመግለጽ እንደተነገረ ይግባን።

<u>ኃይልም አያደርጉም</u> ታቦት ኃይል አያደርግምን? 2ኛ ሳሙ 6÷8 አዝያን ያለ ሥልጣነ ክህነት የእግዚአብሔርን ታቦት ቢነካ ስለምን አንደ እንጨት ደርቆ ሞተ? ኃይል ባያደርግ ነውን? ኤሎፍ ላውያን ዳጎን የተሰኘ ጣዖታቸውን በትዕቢት በእግዚአብሔር ታቦት ላይ ቢያደርጉት ታቦተ ጽዮን ገነጣጥላ አልጣለችውምን? 1ኛ ሳሙ 5÷1-5 እስራኤላውያን ተንጣሎ የሞላባቸውን ባህረ ዮርዳኖስ ሰንጥቀው የተሻገሩት ታቦት ተሸክመው ፊት በሚመሩ ካህናት አልነበረምን? ኢያ 3÷1-13 ነገር ግን ኃይልን አያደ ርጉምና አትፍሯቸው ተብሎ በኤርምያስ የተጻፈልን ለጣዖት መሆኑን እንወቅ። ደግሞስ እግዚአብሔር ክብሩን የሚገልጽበት ታቦት ያልተፈራ ማን ይፈራ? የእግዚአብሔር ነብይ ኢያሱ እንኳን ልብሱን ቀድዶ በግንባሩ እንደተደፋለት አንርሳ። ኢ 7÷6 ዳዊትም የእግዚአብሔር ታቦት ከኤሎፍላውያን ወደ እስራኤል ስትገባ በዝማሬ ከተቀበላት በኋላ በእርሱ ቤት ይህ ታቦት እንዲቀመጥ ቢጠየቅ እኔ ኃጢያተኛ ነኝ። በቤቴ ታቦት ሊገባ አይገባም ነው ያለው። ታዲያ ታቦትን ማክበሩ አይደለምን 2ኛ ሳሙ 6÷10-11

አንዳንድ ደካሞች በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ጽላት መሰረቁን ሲሰሙ ኃይል ባይኖረው አንጂ መቼ በሌቦች ተይዞ ይሸጥ ነበር? ይላሉ። ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሁዳ በ30 ብር የሸጠው ኃይል ስላልነበረው ይሆን? አይደለም ትዕግስትን ሲገልጽ እንጂ። አይምሰለን እግዚአብሔር ከትዕግስቱ በስተጀርባ ቅጣት አለው። እስከዚያው ግን በንስሐ እንድ ንመለስ

ይታገሳል። <u>እንኳን ታቦት ፈጣሪ ተሸጦ የለምን?</u> እኛ ግን እግዚአብሔር እነዚህን ሰዎች ለንስሐ እየጠበቀ እንደሆነ ሳናውቅ የትዕግስቱንና የመቻሉን ነገር በመናቅ ታቦት ኃይል ባይኖ ረውነው እንጂ ወደሚለው ሃሳብ እንዳንሄድ ያስፈልጋል። ሮሜ 2÷4 "ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግስቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን? እንዳለው የትዕግስቱንና የመቻሉን ነገር ኃይል እንደሌለው የምንቆጥር ከሆነ የሞኝነት ነው። ሞኝነት!

- <u>መልካም መሥራት አይቻላቸውምና አትፍሩአቸው</u>

እንደሚታወቀው ሁሉ ጣዖታት በእኛ ላይ መልካምም ክፉም ያደርጉብን ዘንድ ሥልጣን የላቸውምና አትፍሩአቸው ተብ ለናል። ይህንን ቃል ለታቦት ለሚሰጡ ሰዎች ግን የሚከተለውን ጥቅስ እንሰጣቸውና መልስ ይስጡን። 2ኛ ሳሙ6÷11 "የእግዚ አብሔርም ታቦት በጌት ሰው በአቢዳራ ቤት ሦስት ወር ያህል ተቀመጠ። እግዚአብሔርም አቢዳራንና ቤቱን ሁሉ ባረከ" ታቦቱ በቤቱ የገባለት አቢዳራ ቤቱም የግል ሕይወቱም እንደተባረከ (እንደተቀደሰ) ከቃሉ ተምረናል። ለሕይወታችን ደግሞ በረከትን የመሰለ <u>መልካም</u> ነገር የለም።

የእግዚአብሔር ጸጋውና ኃይሉን የሚያስተላልፍበት ታቦት መልካም የማያደርግ ከሆነ የአቢዳራብ ቤት ስለምን በመልካም በረከት መላ?መልካም አያደርጉም የተባለው ጣኦታትን እንደሆነ ተረዳን? ለጣኦት የተነገረውን ለታቦት እየሰጡ በጠማማ ትርጉም ታቦትን አትፍሩ እያሉ ሰውን ወደ ምን መንዳት ጥቅሙ ምንድር ነው? የሚያስከትልባቸውን ፍርድ ሳያውቁ እም ወደማይገኝላት ርትዕት ሃይማኖት ቢመለሱ ይመረጣል።

2ኛ ዜና 8÷11 "የእግዚአብሔር ታቦት የገባበት ስፍራ ቅዱስ ነውና" ታቦት መልካም ስለሚያደርግ ታቦት የገባበት ስፍራ ቅዱስ እንደሚሆን ከቃሉ እንማራለን ከዚህ የተነሳ ቤተክርስቲያናችን ታቦት አለባትና ቅድስትና በበረከቱ ሙላት የተሞላች የጸጋው ምንጭ ናት።

ምዕራፍ ሦስት

ምንኩስና በማርቲን ሉተር እይታ

ዓለማችን ያበቀለቻቸው እንክርዳዶች ስለ ምንኩስናም ሆነ ምናኔ አላስፈላጊና ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሰው ሰራሽ ሥርዓት እንደሆነ አድርገው የክህደት ትምህርታቸውን ይረጫሉ። ምንኩስናም ሆነ ምናኔን ለመንቀፍ ሰይጣን የኑፋቄ ምንጭ ያደረገው ማርቲን ሉተርን ነው። ወደዚህ ነገር ከመሄዳችን በፊት ማርቲን ሉተር ማን እንደነበረና ምንኩስናን እንዴት ሊቃወም እንደቻለ በጥቂቱ እናትታለን።

ማርቲን ሉተር ዜግነቱ ጀርመናዊ ሲሆን ቤተሰቦቹ የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ነበሩ ሉተር በ1483 ዓ.ም ህዳር 14 ቀን በጀርመን “ሳክሶኒ” ግዛት “ኤይዝለብል” በተባለች ቦታ ተወለደ። በዚህ ስፍራ ይወለድ እንጂ ቤተሰቦቹ ቋሚ መኖሪያቸውን “ማንስፈልድ” በተባለች ከተማ በማድረጋቸው ሉተር ትምህርቱን በዚች ከተማ መስርቷል። ትምህርቱን ካጠናቀቀ በኋላ የሕግ ምሁር እንዲሆን የፈለገው አባቱ “ሃንስ” ወደ “ኤርፋርት” ዩኒቨርሲቲ እንዲገባ ስለገፋፋው ወደዚያው አመራ። ሉተር የመጀመሪያ ዲግሪውን ቀጥሎም የማስተር ብሎም የፍልስፍና ማስተር ዲግሪውን በዚያው ዩኒቨርሲቲ ያዘ። ሉተር ይህንን ዕውቀቱን ይዞ እያለ የሃይማኖት ምሁር ለመሆን ፈለገ። በዚህ አጋጣሚ “The maecimilain dictionary of biography” የተሰኘው መጽሐፍ እንዳተተው የአንድ ጓደኛው ሞት ጭምር ስላሳዘነው ወደ “አገስቲን” ገዳም ገብቶ ስለመንፈሳዊ ህይወት ምንም በማያውቅ ህይወቱ ምንኩስናን ተቀበለ። ይህው ከላይ የተጠቀሰው መጽሐፍ እደሚያትትለት ቅስና ተቀብያለሁ ብሎ ቅዳሴ እንደገባም ገልጿል።

በዚሁ በ16ኛው መ/ክ/ዘ ላይ ነበር አውሮፖ በከፍተኛ የፍልስፍናና የእምነት ነውጥ ላይ የወደቀችው። ሉተርም የሚኖርበት የምንኩስናን ይህወት ሊቋቋመው አልቻለም። “ቀንበሩ ከበደው” ትከሻው ዛለ፣ ከአቅሙ በላይ ሆነበት በዚህም ላይ ተምሮት የነበረው የፍልስፍና ትምህርት ከእምነት ጋር ሊጣጣምለት አልቻለም። “በሉተር ልብ ውስጥ ፍልስፍናና መጽሐፍ ቅዱስ ጦርነት ከፈቱ” ሉተርም ለፍልስፍና መወገን

[illegible]ሬ ፍልስፍና ጠልፎ ጣለው እምነትን ከፍልስፍና ጋር ሊያዋህደው [illegible]ለን በመጀመሪያ የሉተር ፍልስፍና ያነጣጠረው ከብዶት በነበረው ምንኩስና ላይ ነበር። በርሱ አይታ ምንኩስናም ሆነ ምናኔ ሰው ሰራሽ ሥርዓት እንጂ አምላካዊ ስርዓት አይደለም ብሎ ቆቡን ቀዶ ጣለ። ቆዳ [illegible] በገዳም መኖር ጠፍር መታጠቅ፣ የቅዱሳን አማላጅነት፣ የሕግ [illegible]ም ቢሆን አላስፈላጊ ነው ሲል በተጨማሪም ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደመሰለው መተርጎምና በመሰለው መንገድ መጓዝ ይችላል። [illegible] ፍልስፍናውን ተነበየ እነዚህ ነጥቦች ስህተት እንደሆኑ በቅዱስ መጽሐፍ ግልጽ ነው። በዚህ መልኩ የፕሮቴስታንትን (ተቃዋሚ) ድርጅት [illegible]መሰረት ዛሬ ለብዙ እምነቶች መፈልፈል ሉተር ምክንያት ሆኗቸዋል።

ሉተር ምርምሩን ከጨረሰ በኋላ እዚሁ ገዳም ውስጥ እንደርሱ ምንኩስና የከበዳትን “ካታሪና ቮንቦራ” የተባለችን ሴት አገኘ [illegible]ሉም አገባት ምንኩስናውን ጥሎ ከእርሷ አምስት ልጆችን [illegible]ወለደ ተከታዮቹም ጭምር ይመሰክሩለታል። “Great voyeses of the reformation” የተሰኘው መጽሐፍ ስለ ሉተር ሲያትት ኃይለኛና [illegible] አስቆጋሪና ቁጣው የሚያስደነግጥ ሰው ሲል ከከተበለት በኋላ [illegible]ም ባህርይውን እራሱ ሉተር እንደሚያምን ከወዲሁ ገልጿል።

መልስ

ሉተር በቅዱስ መጽሐፍ ሳይሆን በፍልስፍናው የተከላቸው [illegible] ዛሬ ዓለምን በክህደታቸው ከቅድስት ቤተክርስቲያን [illegible] ነው። ከአባታቸው ከሉተር በወረሱት ውርስ ቅዱስ [illegible] እንዳሻቸው ይተረጉሙታል። አባታቸውን ያስጠመ የፍልስፍና [illegible] ዛሬም ተከታዮቹን እያስጠማቸው ነው።

የድንግልና ህይወት፡- 1ኛ ቆሮ 7÷32 “ነገር ግን ያለሀሳብ [illegible] እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንደሚያሰኘው የጌታን [illegible] ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንደሚያሰኛት የዓለምን [illegible] ልቡም ተከፍሏል።” መናፍቃኑ የሐዋሪያትን ትምህርት ነው [illegible] ይላሉ ታዲያ ለምን የቅዱስ ጳውሎስን ትምህርት [illegible] ሐዋሪያው ሰው ሁሉ ቢችል እንደ እኔ (በድንግልና) [illegible] እወዳለሁ አያለ? እርሱ ድንግላዊ ነውና። በድንግልና መኖር

ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ህይወት ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስም ከመጽሐፍ ቅዱ
ውጪ የሆነ ሐዋሪያ ነዋ? አይደለም። ሉተርና ልጆቹ እንጂ እርሱ
እውነተኛ ነው። 2ኛ ቆሮ 6÷8 ዳሩ በፍልስፍና ያበደ ሰው ለእግዚአብሔ
ይገዛል ብሎ መጠበቅ ያስቸግራል ከሉተር የተማሩት አይደል?።

<u>ምናኔ</u> (ገዳማዊ ህይወት) አምላካዊ ሥርዓት እንደሆነ በማቴ 4
ጀምሮ የምናነበው እውነታ ነው። ተጠራጣሪዎች በሽንገላ ከንፈራቸው
እንወደዋለን የሚሉት እርሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ገዳመ ቆሮን
ገብቶ ምናኔን አስተምሮናል። ነገር ግን የጌታችንን ሥራ ያጥላሉታ
ሰው ሰራሽ፣ የሥጋዊያን ሥርዓት ሲሉ። ጌታችን ገዳመ ቆሮንቶስ የገባ
ሥጋዊ ሆኖ ነው? ይቅር ይበላቸው ከማለት ውጪ ምን እንላለን?።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ስብከቱ "ከኔ ተማ
ብሎናልና ማቴ 11÷29 ለመንፈሳዊ ህይወት ገዳም የተመረጠ እንደ
ከጌታችን ተምረናል። ከእኔ ተማሩ አለ እንጂ እኔ ያሳየኋቸው
እየኮነናችሁ አስተምሩ አላለም። አንባቢ ሆይ "መንፈስን ሁሉ መር
መናፍስት ጻድቅ መስለው የእግዚአብሔርን ሥራ እያ
የሚያስተምሩበት ጊዜ ነውና። 1ኛ ዮሐ 4÷1

<u>ጠፍር መታጠቅ</u> :- ከእነ ኤልያስ ጀምረን የቅዱሳን ገዳማውያንን ሕ
ስንመለከት ጠፈር ይታጠቁ ነበር <u>ምስጢሩ</u> ጠፈር ቀበቶ ሊሆን የሚች
በሬው ታርዶ ከሞተና ቆዳው ከሥጋው ተገፎ ከተለየ በኋላ
እንዲሁም ቅዱሳን ከሥጋ ጠባይ ተለይተው ውስጣዊ ስሜታ
በመንፈስ ቅዱስ ስለት ገድለው የንጽሕናና የቅድስናን ዝናር የ
መሆናቸውን የሚያመሰጥር የአለባበስ ስርዓት ነው።

ጌታችን "ስለ መንግሥተ ሰማያት ራሳቸውን ጃንደረባ ያ
አሉ ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው" ማቴ 19÷1-12 ብሎ የተና
ውስጣዊ የሥጋ ፈቃዳቸውን በመንፈስ ቅዱስ ስለት ቆርጠው በድን
ስለሚኖሩ ቅዱሳን አይደለምን?" <u>ሊቀበልም የሚችል ይቀበለው</u>" ያለ
የድንግድልናን ህይወት አይደለምን? ጌታችን ያልነቀፈውን የም
ሕይወት አትቀበሉ ብሎ ማስተማር ከሰይጣን ወይስ ከእግዚአብ

ለመንግሥተ ሰማያት ክብር ሲሉ ራሳቸውን ጃንደረባ ያደረጉ ልዩ ክብርና ጸጋ አላቸው። ኢሳ 56÷3-7 እኛ ግን በፍልስፍና ተነሳስተው የገዛ መንገዳቸውን የመረጡትን (ተጠራጣሪዎችን) ሳይሆን የሃይማኖታችን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረንና ያሳየንን የምንከተል ነን። ዕብ 3÷1።

ምዕራፍ አራት

ተአምራት (ምልክት) የሃይማኖተኛነት መለኪያ ሊሆን አይችልም

ዓለማችን ልቡ ጉድጓድ ነው። እምነትን የተመላ ልብ ከሰዎች እየሸሸ ነው። ብዙ የዋሀን ከኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ውጪ ወደሚደረገው ተአምራት ጎዳናቸው ስለሚያማትር ዲያብሎስ ድክመታቸውን አውቆ የእውነት ሃይማኖት አስመስሎ በማሳየት የዚህ የመጨረሻ ዘመን የጥፋት ሰለባ አድርጓቸዋል። እያደረጋቸውም ነው። ነገር ግን ተአምራትን ማድረግም ሆነ ምልክትን መስጠት የእውነተኛነት መለኪያ አይደለም።

በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሙሴና አሮን በትሩን በፈርዖን ፊት ቢጥሉ ተለውጦ እባብ ሆኖአል። ፈርዖንም በበኩሉ የግብጽን ጠንቋዮችና አስማተኞች (ኢያኔስንና ኢያንበሬስን) 2ኛ ጢሞ 3÷8 ጠርቶ ያንኑ የመሰለ ተአምራት እንዲያደርጉ ቢነግራቸው እነርሱም በትራቸውን ጣሉት በሰይጣንም ምትሃት ተለውጦ እባብ ሆነ። ታዲያ ተአምራት አድርገዋልና የግብጽን ጠንቋዮችና አስማተኞች እውነተኛ (የሃይማኖት) ሰዎች ናቸው እንበል? አይደለም። ሰይጣን አሠራሩን የመንፈስ ቅዱስ አስመስሎ ማቅረብ ይችልበታል ዛሬም ሰዎችን ግራ ለማጋባትና ከእውነተኛይቱ የእምነት ጠርዝ ለማስወጣት ተአምራትን ማሳየትን ተያይዞታል። ናእስ የተባለ ጠንቋይ ሰዎችን ከእግዚአብሔር ህብረት ለመለየት ፈለገ ለዓላማው ግብ መምቻ ያደረገው ተአምራትን ማሳየት ነበር። እስጢፋኖስ ማህበሩን ሰብስቦ ሲያስተምር የቀናው ናእስ በማህበሩ ፊት የቆመች ላህምን ተጠግቶ በጆሮዋ እፍ ብሎ እስትንፋሱን ቢነፋባት ላህሟ ለሁለት ተሰነጠቀች ብዙዎቹ የእግዚአብሔር ኃይል በእርሱ ላይ ነው ብለው ተከተሉት።

"ጻድቅ ለእንስሳ ነፍስ ይራራል" ምሳ 12÷10 እንደተባለ የእንስሳዋ ነፍስ ያሳዘነውና የሰዎች በናእስ ምትሀት መጥፋት ያስቆጨው ቅ/እስጢፋኖስ በላህሟ ላይ አማትቦ ቢጸልይባት ሰውነቷ እንደነበር ተመለሰላት በዚሁ ጊዜ ወደ ናእስ የሄደው ሕዝብ ወደ እስጢፋኖስ መጣ

(ምንጭ የሐዋርያት ሥራ ትርጓሜው)። ዛሬም ሰዎች ምልክትን እያዩ ህይወታቸው እንዲህ ይገለባበጣል። ምልክት የእውነተኛነት ማሳያ ቢሆን ኖሮ ናእስ እውነተኛ ነበር። ግን አይደለም። ቢሆንማ ኖሮ በመንፈስ ቅዱስ የተመላው የእስጢፋኖስ ጸሎት የናእስን አሠራር ባላፈረሰበት ነበር።

በሥጋ ወራት ጌታችን በምድረ ኢየሩሳሌም ሲመላለስ ቤተ አይሁድ ምልክትን እንዲያሳያቸው አጥብቀው ይለምኑት ነበር የሚፈልጉትም ምልክት እንደሙሴ ባህር ከፍሎ ጠላት አስጥሞ እንደ ኢያሱ በርድ አዝንሞ ፀሐይ አቁሞ፤ እንደ ጌዲዎን ጠል አውርዶ ጠላት ድል አድርጎ፣ እንደ ኤልያስ ሰማይ ለጉሞ እሳት አዝንሞ እንዲያሳያቸው ነበር። ጌታችን ግን ይህንን ማሳየት ሳያቅተው "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክትን ትሻለች" ማቴ 12÷38-39 ብሎ መለሰላቸው። አይሁድ ሃይማኖትን ሳይሆን ተአምራትን አነፍናፊዎች መሆናቸውን ስለሚያውቅ ምልክትን ላሳያቸውም ከነብዩ ከዮናስ በቀር ሌላ ምልክት እንደማያዩ ነገራቸው እንጂ ሉቃ 11÷29

ክፉና አመንዝራ:- አመንዝራ ሴት በአንድ ወንድ መወሰን የማትችል ግብሩ አንድ ሲሆን እርሷ ወንድ ማፈራረቅ ያስደስታታል። አይሁድም በአንድ ሃይማኖት መወሰን አይችሉም ነጋ ጠባ ተአምራት እንዲፈራረቅላቸው /እንዲለዋወጥላቸው/ ይፈልጋሉና አመንዝራ ተባሉ። ዛሬም ትውልዱ ከአመንዝራነት ስላልጸዳ በቀደመችው አንዲት ሃይማኖት ከመጽናት ይልቅ በየሰው አዳራሽ እየሄደ ተአምራትን ማማረጥና ሃይማኖትን ማፈራረቅ ይወዳል። ይሁን እንጂ ከእውነተኛይቱ ሃይማኖት የወጣ ተአምራት ሁሉ ለመንግሥተ ሰማያት አያበቃም ማቴ 7÷22 "በዚያን ጊዜ ብዙዎች ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ ዓመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።" ለመንግሥተ ሰማያት ካላበቃ ከቶ አላውቃችሁም የሚያሰኝ ተአምራት ጥቅሙ ምንድን ነው?

ተአምራትን አላደረግንምን? ብለን፤ ተመጻድቀን ከእኔ ራቁ ተብለን በሲኦል የምንጣልበት ተአምራት ቀርቶ በትህትና ሆነን "ኑ የአባቴ ብሩካን" ብንባል አይሻልምን?

ከቶ አላውቃችሁም:- "አስፈሪ ቃል ነው"። እግዚአብሔር ያላወቀን ማን ሊያውቀን ነው?። በእውነተኛይቱ ሃይማኖት በመንፈስ ቅዱስ ያልተሠራ ተአምራት ነውና አላውቃችሁም ይላቸዋል።

ሰይጣን የራሱ ሀሰተኛ ነብያትና የሀሰት ምልክትን የሚያሳይባቸው መጠቀሚያዎች አሉት እነዚህን እንኳን ተአምራት ሰሩ ብለን ልናምንባቸው ይቅርና ቃላቸውን እንዳንሰማ መጽሐፍ ቅዱስ አጥብቆ ይናገረናል። ዘዳ 13÷1-3 "በመካከልህ ነቢይ ወይም ህልም አላሚ ቢነሳ ምልክትን ተአምራትን ቢሰጥህ እንደነገረህም ምልክቱ፣ ተአምራቱም ቢፈጸም እርሱም ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወዱት እንደሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ህልም አላሚ አትስሙ።" ሰይጣን እራሱን የብርሃን መልአክ አስመስሎ እስከማሳየት ይፋጠናል። ዱካውን የሚከተሉ ደግሞ ራሳቸውን የጽድቅ አገልጋዮች መስለው ድንቅ ታአምራትን አደረግን ቢሉ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ስላልሆነ አይገርመንም። 2ኛ ቆሮ 11÷13 "እንደእነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስ ሐዋርያ እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ ውሸተኛ ሐዋሪያትና ተንኮለኞች ናቸውና ይህም ድንቅ አይደለም። ሰይጣን የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅ አገልጋዮች እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ቁም ነገር አይደለም ፍጻሜአቸው እንደሥራቸው ይሆናል።"

መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስን በሃይማኖት የምንከተለው እኛ አይሁድ ተአምራትን ሽተን መሆን የለበትም አድህኖቱን ፈልገን እንጂ ሐዋርያት ተአምራት አይተው አይደለም የተከተሉት መድኃኒትን ወደው እንጂ እርሱ ግን ጊዜውን ጠብቆ በቃና ዘገሊላ የመጀመሪያ ተአምራትን አሳይቶአቸዋል። ዮሐ 2÷11 "ሳያዩ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው" መባሉን እንርሳ ዮሐ 20÷29። እምነት የጎደለው ትውልድ ተአምራትን እንደ አይሁድ ያነፈንፋል እኛ ግን ተአምራት አየን አላየንም የቤተክርስቲያን ራስ ኢየሱስ ክርስቶስ ተአምር አድራጊ መሆኑን ሳናይ እናምናለን አምነናልም።

በቅዱስ መጽሐፋችን አስቀድመን ጽድቁንና መንግሥቱን እ...

ተአምራትን ፈልጉ አልተባለም። ማቴ 6÷33 ለመሆኑ ትምክህት አያስፈልግም እንጂ እንናገር ከተባለ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን የተአምራት ግምጃ ቤት አይደለችምን? መጥተህ እይ ዮሐ 1÷47።

ምዕራፍ አምስት

ድኅነት በቅዱሳን እንደሚተላለፍ

ብዙ ሰዎች በቅዱሳን በኩል ድኅነት እንደምናገኝ ስንነግራቸው መርዶ የነገርናቸውን ያህል ይደነግጣሉ። ለማመን ሚዳው ገደል ይሆንባቸዋል። ነገር ግን አንድ የተደበቀባቸው ምስጢር አለ።

ድኅነት በሁለት ይከፈላል:-

1ኛ. ድኂን አምላካዊ (Direct salvation)
2ኛ. ድኂን ምክንያታዊ (Indirect salvation)

እግዚአብሔር እራሱ ማንንም መጠቀሚያ ሳያደርግ ለሰው ልጆች የሚሰጠው ድኅነት ድኂን አምላካዊ ይባላል።

ደኂን ምክንያታዊ ግን እግዚአብሔር ቅዱሳንን፣ መስቀሉን፣ ጸበሉን፣ እምነቱን (ትቢያውን) ወዘተ... ምክንያት አድርጎ የሚሰጠን ድኅነት ነው።

ለማያምን ሰው ይጭነቀው እንጂ ለእኛ ለምናምን ግን በቅዱሳን በኩል ድኅነት ማግኘታችን እንግዳ አይሆንብንም። እንኳንስ በቅዱሳን በኩል ይቅርና እስራኤል በቀላተሳይዳ ልውልን አስቆጥተውት በጸአ በተመለሱ ጊዜ እግዚአብሔር ሙሴን የናስ እባብ እንዲሠራ እንዲሰቅለው እርሱንም ያየ እንደሚድንና በሕይወት እንደሚኖር ራሱ እግዚአብሔር ተናግሯል ዘኁ 21÷8-9 እባቡ አምላክ ሆኖ አይደለም ያዳናቸው። እግዚአብሔር ራሱ የድኅነት ምክንያት አድርጎ ለእስራኤል ልጆች ሰጣቸው እንጂ የእባብን ምስል ምክንያት አድርጎ እግዚአብሔር ልጆቹን ካዳነ ቅዱሳንን ምክንያት አድርጎ ያድነናል ብሎ ማመን ወንጀል ምኑላይ ነው?።

ከቅዱስ መጽሐፉ ወጥታችኋል የሚያሰኘው የት ላይ ነው? ቅዱሳን

ድኂን ምክንያታዊ ካልሆኑ ክብራቸው ከእባብ ምስል ማነሱ ነዋ ? አይሆንም። ከእባብ ምስል ይልቅ በነፍስ በሥጋ እግዚአብሔርን ያገለገሉ ቅዱሳን አይበልጡምን?።

እንዲህ ብለው ሲያስረዷቸው አንዳንድ ተጠራጣሪዎች እግዚአብሔር ራሱ ማዳን ሲችል ቅዱሳን ለምን አስፈለጉ ብለው የምርምር ጥያቄ ይጠይቃሉ። እነርሱ ሰዎችን ወደራሳቸው እየጠሩ ኑ እንጸልይላችሁ ትድናላችሁ ለምን ይላሉ? የእነርሱ ጸሎት የሚያድን ከሆነ የድንግል ማርያምና የቅዱሳን ጸሎት እንዴት አያድንም? እነርሱ ከቅዱሳን በልጠው ነውን? (ዳሩ ግን የተጠራጣሪ ጸሎት እንደማያድን እናምናለን ያዕ 1÷8 አሁ ቅዱስ የተባለ አባት ስለእግዚአብሔር ባህሪይ በተናገረበት ድርሳኑ "እግዚአብሔር በባህሪው ምክንያት ይፈልጋል" ብሎአል ዳዊትም በመዝሙሩ "እግዚአብሔር በቅዱሳን ላይ ድንቅ ነው" መዝ 66÷35 ብሎ ቅዱሳኑን ምክንያት አድርጎ የሚፈጽመውን ድንቅ ሥራ ከትቦአል። የብዙዎች ችግር ይህንን ማመን ነው።

አንዳንዶች ያዳነን ክርስቶስ ነው። እንዴት በቅዱሳን ድኅነት እናገኛለን? ቅዱሳን የሚያድኑ ከሆነ የክርስቶስ ሞት ለምን አስፈለገ ይላሉ። በርግጥ የመርገማችንን ቁስል ሁሉ በመስቀል ላይ ያደረቀልን ክብር ይግባውና ክርስቶስ ነው። ይሁን እንጂ ጠያቂዎቹ አንድ የዘነጉት ነገር ያለ ይመስላል። የቅዱሳን ማዳን እስከየት ድረስ? ለይተው ያላወቁት ይህንን ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ የሰጠን ድኅነት የሰው ልጅ በቅድስናው ሊሰጠን የማይችለውንና ፍጡር በዚህ የድኅነት ሥራ ውስጥ እጁን ሲያስገባበት የማይችለውን ድኅነት ነው። በተረፈ ነብያትም ሆኑ ቅዱሳን ሰማዕታትም ሆኑ ጻድቃን የዚህ ድኅነት ተቋዳሽ ናቸው (የድኅነቱ ተጠቃሚዎች ናቸው) ይኸውም በአዳም ምክንያት የወደቀብንን የሐጢያት ቀንበር ሰባብሮ መጣል የሚችለው ክርስቶስ ብቻ በመሆኑ ነው። ቅዱሳን ክርስቶ ያዳነንን ዓይነት ድኅነት ሰጥተውናል ብላ ቤተክርስቲያን አላስተማረችም በመስቀል ላይ ሞቶ መርገማችንን በደሙ ያጠበ ክርስቶስ ብቻ ነውና። የክርስቶስን ዓይነት ድኅነት መስጠት ይችላሉ ብሏል አምን የክርስቶስ መምጣት ለምን አስፈለገ ባሉ ነበር። ይሁን እንጂ

እኛ እንዲህ አንልም።

ቤተክርስቲያን ምን ብላ እንደምታስተምር ያላወቀ ሰው ያዳኖችሁን የማታውቁ ገና በጨለማ ውስጥ ትኖራላችሁ እያለ ይሳደባል። "እናት ለልጇ ምጥ አታስተምርም።" ያዳነንን እነርሱ ከሚያውቁት በላይ እናውቀዋለን። "ግያለም በጨለማ ውስጥ የሚኖረው ማን እንደሆነ በመከር ጊዜ ይለያል።"

የቅዱሳን ድኅነት ሰጭነት የአዳምን መርገም የማይመለከት መሆኑን ካስተዋልን ከሌሎች የኃጢአት ሥራዎች እንድንባቸው ዘንድ እነርሱንም ለእኛ የጸጋ መድኃኒት አድርጎ እግዚአብሔር እንደሰጠን ለማንዛቤ ያህል በጥቂቱ እንመለከታለን።

በቅዱሳን በኩል የጸጋ ድኅነት

ዘፍ 45÷7-8 "እግዚአብሔር በምድር ላይ ቅሬታን አስቀርላችሁ ዘንድ በታላቅ መድኃኒት አድናችሁ ዘንድ ከእናንተ በፊት ላከኝ" ብሎ ዮሴፍ ለወንድሞቹ የጸጋ መድኃኒት እንደሆናቸው ተናግሯል።

ዘፍ 20÷7 "አሁንም የሰውዩውን ሚስት መልስ ነብይ ነውና ስለ አንተም ይጸልያል ትድናለህም" የቅዱሳን ጸሎትና ምልጃ ያድነናል የምንለው ከዚህ ተነስተን ነው። ስለሆነም ድኅነ ምክንያታዊ ናቸው።

ዘዳ 7÷8 "ነገር ግን እግዚአብሔር ስለወደዳችሁ ለአባቶቻችሁም የማለላቸውን መሃላ ስለጠበቀ ስለዚህ እግዚአብሔር በጽኑ እጅ አወጣችሁ ከባርነትም ቤት ከግብጽ ንጉሥ ከፈርኦን እጅ አዳናችሁ"።

ዛሬም ለአባቶቻችን፣ ለቅዱሳን፣ ለድንግል ማርያም የገባላቸውን ቃል ኪዳን አስቦ በግብጽ ከምትመሰለው ከሲዖል የባርነት ቤት ከፈርኦናዊው ከዲቢሎስ ግዞት ያድነናል። ያን ጊዜ የነበረ እግዚአብሔር ዛሬም አለና። አይለወጥም ሚል 3÷6 ጥንት የቅዱሳኑን ቃል ኪዳን ያሰበ ጌታ ዛሬ የማያስብ አይደለም።

የሚደንቀው ነገር በቅዱሳን ድኅነት እንደምናገኝ እኛ

ኦርቶዶክሳዊያን ፈልሰፈን ያበቀልነው ወፍዘራሽ ትምህርት መስሏቸው መታየቱ ነው። ነገር ግን በቅዱሳን በኩል ድህነት እንደምናገኝ እራሱ ባለቤቱ የተናገረው እውነታ ነው። የቅዱሳንንም ምልጃ የመሠረተ ሰው ሳይሆን እግዚአብሔር ነው። አስቀድሞ ኤርምያስ በፋርስ ባቢሎን እያለ እስራኤል ከተያዙበት የባርነት ኑሮ ከደረሰባቸው የኃጢያት ቁስል በኤርምያስ ምልጃ እንደሚያድናቸው ፈጣሪያችን ተናግሯል።

ኤር 33÷1-9 "ኤርምያስ ገና በግዞት ቤት ሳለ አደባባይ ታስሮ ሳለ የእግዚአብሔር ቃል ሁለተኛ ጊዜ እንዲህ ሲል መጣለት ስሙ እግዚአብሔር የሆነ፤ ያደረገው እግዚአብሔር ያደነውም ዘንድ የሠራው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ወደ እኔ ጩህ እኔም እመልስልሃለሁ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገር አሳይሃለሁ የእስራኤልም አምላክ እግዚአብሔር ለአፈር ድልድልና ስለፈረሱ ስለዚች ከተማ ቤቶች ስለይሁዳ ንገሥታት ቤቶች እንዲህ ይላልና ከለዳዊያን ለመዋጋት መጥተዋል ነገር ግን በቁጣዬና በመዓቴ በገደልኋቸው ሰዎች እሬሳዎች ሊሞሏቸው ነው። ስለ ክፋታቸው ሁሉ ፊቴን ከዚህች ከተማ ሰውሬዋለሁና እነሆ ፈውስንና መድኃኒትን አመጣላታለሁ እፈውሳቸውማለሁ የሠላምንና የዕውነትን ብዛት እገልጥላቸዋለሁ የይሁዳን ምርኮ የእስራኤልን ምርኮ እመልሳለሁ ቀድሞም እንደነበሩት አድርጌ እሰራቸዋለሁ እኔንም ከበደሉበት ኃጢያት ሁሉ አድናቸዋለሁ እኔንም የበደሉኝን ያመጹብኝንም ኃጢያታቸውን ይቅር እላቸዋለሁ። ይህችም ከተማ እኔ የምሠራላቸውን በጎነትና ሠላም ለሚፈሩና ለሚደነግጡ አህዛብ ሁሉ ፊት ለደስታ ስም ለምስጋናም ለክብርም ትሆናለች።"

እስራኤላውያን ይህንን ሁሉ ፈውስና ምህረት ሊያገኙ የቻሉት በታላቁ ነብይ በኤርምያስ በኩል (ጩኸት) እንደሆነ ከንባቡ እንረዳለን።

እግዚአብሔር ቅዱሳንንም ሆነ ሥዕሉን፣ መስቀሉን፣ እምነቱን የድህነት ምክንያት ያደረገልንን በዚህ ሁሉ ፈውስ ወደ ህይወታችን ዘልቆ [illegible] የመዳን ዕድላችን እየሰፋ አንጂ እየጠበበ እንደማይሄድ ስለሚያውቅ [illegible] ጌታም ጥቂቶች ከሚድኑለት ዓለሙ ሁሉ ቢድንለት በጎ ፈቃዱ ነው። ዮሐ 3÷17 ዓለም በልጁ እንዲድን ነው አንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውም።

<u>የቅዱሳን ምልጃ በአጸደ ነፍስ</u>

በተቃዋሚዎች አስተሳሰብ ቅዱሳን በሥጋ ወራት አያሉ እንጂ ከሞቱ በኋላ እንኳንስ ሊያማልዱ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረሱ ተደርገው ይታያሉ። እግዚአብሔር ለወዳጆቹ በምድር የገባላቸውን ቃል ኪዳን የሚረሳበት አንጀት የለውም። እግዚአብሔር ወዳጆቹን ይረሳልን? ኪዳን የሚረሳበት አንጀት የለውም። "ኪዳኑንም ለዘለዓለም ያስባል" ተባለ እንጂ ይረሳል መዝ 110(111)-5 "ኪዳኑንም ለዘለዓለም ያስባል" ... መዝ 88÷34 "<u>ኪዳኔን</u> አላረክስም ከአፌም አልተባለም። ዘዳ 4÷31 መዝ 88÷34 "ኪዳኔን አላረክስም ከአፌም የወጣውን አልለውጥም" ብሏልና የገባላቸውን ቃል ኪዳን በአጸደ ነፍስም ቢሆን አይለውጥም። በምድር የሠሩት የምልጃ ሥራ በሰማይም ይከተላቸዋል። ራዕ 14÷13 "ከሰማይም ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ አዎን ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ <u>ሥራቸው ይከተላቸዋል</u> ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምጽ ሰማሁ"።

የተሰመረበትን ቃል እናስተውል ቅዱሳን በምድር የሠሩት ሥራ በሰማይ የሚከፈላቸው ከሆነ በሕይወቱ ሥጋ ከሠሩት ሥራ አንዱ የማማለድ ሥራ ነውና ምልጃቸው በሰማይም አለ ይከተላቸዋል ማለት ነው። ተጠራጣሪዎች ቅዱሳን በሥጋ እንደሚማልዱ እናምናለን ይላሉ። "በጣም ጥሩ" "ከመጣሽ ማርያም ታምጣሽ" ታዲያ በጌታ ፍቅር ውስጥ ሆነው የሞቱ ብፁዓን (ቅዱሳን) የምድር ሥራቸው በሰማይም እንደሚከፈላቸው መጽሐፍ ቅዱሱ እኮ ይናገራል። ይህንንም አብሮ ማመን ነዋ! አለበለዚያ መጽሐፍ ቅዱሱን ቢያስቀምጡት ይመረጣል። ምክንያቱም እያወቁ ላልተጠቀሙበት ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል ፍርዱ ይብሳልና 2ኛ ቆሮ 9÷13-14 እነርሱንና ሁሉን ስለምትረዱበት ልግስና እግዚአብሔርን ያከብራሉ እራሳቸውም <u>ስለእናንተ ሲያማልዱ</u> በእናንተ ላይ ከሚሆነው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሳ ይናፍቋችኋል" አዎን ቅዱሳን እኛ ... ቀን እየናፈቁ እነርሱ ወደአሉበት ቅድስት ሀገር የምንመጣበትን ቀን እየናፈቁ ያማልዳሉ።

የእኛ መዳን የሚናፍቃቸው ቅዱሳን የመጨረሻው ዘመን የ... የመከራ ቀን ቢ... ሰለባዎች እንዳንሆን ቀኒቱ እንድታጥር ያማልዳሉ። የመከራ ቀን ቢያጥር... እንጂ ቢረዝም ጥቅም የለውምና በፈተናው ዝለን እንዳንወድቅ ... 24÷22 "እነዚያ ቀኖችስ ስለተመረጡት ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ

ባልዳነም ነበር ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ። "ከተመረጡት ሁሉ የተመረጠች ድንግል ማርያም መሆኗን እንርሳ፤ እርሷና በሰማይ ያሉ ንጹሐን ባያሳስቡልን ኖሮ ሥጋ ለባሹ ሁሉ እንደማይድን ቅዱስ መጽሐፉ ጽፎልናል። ኃጢአት ጎርፍ ሆኖ ሰዎችን በሚያጥለቀልቅበት ይህ ክፉ ዘመን የምንሻገረው ስለ ምርጦቹ በተደረገው ምህረት መሆኑን አንርሳ። ሄኖ 9÷21-23 "በዚያም ቦታ ሌላ ራዕይ አየሁ የጻድቃን ማደሪያቸውን የቅዱሳን ቦታቸውን አየሁ ከዚያም ቦታ ዓይኖቼ ከመላእክት ጋር የሚኖርባት ማደሪያቸውን ከቅዱሳን ጋር የሚኖርበትን ቦታውን አየሁ ስለሰውም ልጆች አየሁ ፈጽሞ ይለምናሉ ይጸልያሉ "ማየት ማመን ነው" ሄኖክ በራዕዩ በሰማይ ያሉ ቅዱሳን ሲጸልዩልን ማየቱን ማየታችን አድርገን ምልጃቸውን እናምናለን።

የነብዩ የኤልሳዕ አጽም ሙት አስነስቷል 2ኛ ነገስ13÷20 አጽሙ ሙት ካስነሳ በአጸደ ነፍስ የሚያቀርብልን ምልጃማ እንዴት ከኃጢያት ሞት አያስነሳን? 2ኛ ቆሮ 5÷18-20 "ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፤ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር። <u>በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ</u>። እንግዲህ እግዚአብሔር <u>በእኛ እንደሚማልድ</u> ስለክርስቶስ መልዕክተኞች ነን"።

ቅዱስ ጳውሎስ ቅዱሳንን መከሉ እግዚአብሔር ለቅዱሳን የማስታረቅ (የማማለድ) ቃል ኪዳን እንዳኖረላቸውና በእነርሱም እግዚአብሔር እንደሚማለድ (እንደሚታረቅ) ግልጽ አድርጎ አስተምሮታል።

እንኳንስ በልዑልና ክብር፣ በአጸደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን ይቅርና ኃጢያት በተሞላበት ዓለም ውስጥ የሚኖሩ የፊሊጲስዩስ ክርስቲያኖች እንኳ በምልጃ እንዲጸኑ ቅዱስ ጳውሎስ ይመክራቸው ነበር። ፊል 4-6 ነገር ግን በጸሎትና <u>በምልጃ</u> ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን አስታውቁ..."

በቅዱሳን ስም ቤተክርስቲያን ማነጽ እንደሚገባ

አንዳንዶች በቅዱሳን ስም ቤተክርስቲያን ሲታነጽ ይከፋቸዋል። ቅዱሳንን ለማምለክ ሕንጻ ቤተክርስቲያኑን እንደምንሠራ አድርገው ይናገራሉ ያስተምራሉም። በመሠረቱ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ቅዱሳንን አምልኩ ብላ ያስተማረችበት ጊዜም የለም አታስተምርምም። ይህ የሰዎች ውንጀላ እንጂ አምላካችን ክብር ይግባውና ልዩ ሦስት አንድ እግዚአብሔር ነው።

በቤቱ ውስጥ የሚመለከው እግዚአብሔር ሆኖ ሳለ ለቅዱሳን ግን ቤቱ መታሰቢያቸው ነው። ልበ አምላክ ዳዊት "የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል" መዝ 111÷6 እንዳለ መታሰቢያቸው ለዘላለም መኖር ስላለበት በስማቸው ቤተ እግዚአብሔር እንዲታነጽ እግዚአብሔር ፈቅዷል። ኢሳ 56÷4-5 "እግዚአብሔር ሰንበቴን ለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝንም ነገር ስለሚመርጡ ቃል ኪዳንም ስለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላል በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣችኋለሁ። የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ" እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሰው ይነፍጋቸዋልን? እግዚአብሔር ያከበራቸውንስ ማን ይቃወማቸዋል? ሮሜ 8÷30-33 "በቤቴና በቅጥሬ" ብሏልና። በእግዚአብሔር ቤት በስማቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ ቤተክርስቲያ ይታነጻል። በቤተክርስቲያኑ የሚመለከው አግዚአብሔር ሲሆን ቅዱሳን በመታሰቢያነት ይታሰቡበታል።

እግዚአብሔር ያከበራቸውን ማክበር የእግዚአብሔር ሰው የሚያሰኝ ሠናይ ምግባር ስለሆነ አንዲት እግዚአብሔርን የምትፈራ ሱናማይት ሴት ነቢየ እግዚአብሔር ኤልሳዕን በመንደሯ ሲያልፍ ጠብቃ አክብሮቷን በመስተንግዶ ከገለጸችለት በኋላ በቤቷ ሰገነት አቁማለታለች። ሰገነቱ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነበር። 2ኛ ነገ 4÷9-11 ዛሬ በቅዱሳን ስም (ሰገነት) ቤተክርስቲያን ብናቆም ምን የምንወቀስበት ነገር ተገኘ? ሱናማዊቷ ስህተት አደረገችን?።

በደብረ ታቦር የተገለጸውን መለኮታዊ ምስጢር ለማየት የታደለ ቅዱስ ጴጥሮስም ጌታውን "ጌታ ሆይ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው"።

ካለው በኋላ ብትወድስ በዚህ ሦስት ዳስ፤ አንዱን ለአንተ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ እንሥራ ሲል በቅዱሳን ስም ቤተ እግዚአብሔር መሥራት እንደሚገባ ያስተምረናል። ቤተክርስቲያንን በቅዱሳን ስም ማነጽ አላስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ጴጥሮስ ጌታን ለአንተ ብቻ እንሥራ ብሎ ለሙሴና ለኤልያስ ሳይል በቀመ ነበር። ነገር ግን የቅዱሳን መታሰቢያ እንዳይጠፋ ከአምላኩ የተማረ ቅዱስ ጴጥሮስ አንዱን ለሙሴ አንዱን ለኤልያስ ነው ያለው። ጌታችንም በቅዱሳን ስም ቤተክርስቲያን ማነጽ አላስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ቅዱስ ጴጥሮስን ለምን እንዲህ አልክ ባለው ነበረ ግን አላለውም።

እኛም ከሐዋርያት ስብከት አንወጣም ከቃላቸውም ፈቀቅ አንልምና በቅዱሳን ስም ቤተክርስቲያን እናንጻለን።

ምዕራፍ ስድስት

"እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም"

ቅድስተ ቅዱሳን ድንግል ማርያም ከሀያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ይልቅ የከበረችና የገነነች ስትሆን የእግዚአብሔርም የምስጢር ግምጃ ቤት ነች። ስለ ክብሯም ጸዳል በሰው ልጆች አንደበት ይህንን ይመስላል ብሎ ለመናገር አይቻልም። ሁሌም ለሰው ልጆች ደኅንነትን ታስባለች። ምሳ 12÷5 "የጻድቃን ሀሳብ ቅን ነው። "እንደተባለ የጻድቃን እመቤት ድንግል ማርያም ደግሞ ለእኛ ቅንን ነገር ስለምታስብልን ድኅነታችንን ትናፍቃለች። ምሳ 11÷23 "የጻድቃን ምኞት በጎ ብቻ ነው።

በተለይም የዚህ የመጨረሻው ዘመን የጥፋት ስለባ እንዳንሆን በተሰጣት ቃል ኪዳን ድህነታችን እንዲፋጠን ወደ ልጇ ታሳስባለች። ማቴ 24÷22 "እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር። ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡ ሰዎች ያጥራሉ።

ከተመረጡ የተመረጠች ደግሞ ድንግል ማርያም ነች። ስለእርሷ ሲል የጥፋትን ዘመን አሳጥሮ ድኅነታችንን ያቃርባል። የመከራ ዘመን ማመጠሩ እንጂ መርዘሙን ማንም አይሻም። ስለሆነም የተመረጡ ቅዱሳን ወገኖቻቸው እንዳይጠፉ ድኅነትን ይማልዳሉ። ይልቁንም ከምርጦች ምርጥ የሆነችው ድንግል ማርያም።

ስለ ተመረጡ ሰዎች ቀኖቹ ባያጥሩ ሥጋን የለበስ ሁሉ ባልዳነም ነበር። የተመረጡት ቅዱሳን ባይታደጉን በእኛ ድክመት መዳን እንደማንችል ግልጽ ነው። የእኛ እናት ድንግል ማርያም ልጆቿ ነንና። በተሰጣት ቃል ኪዳን ታድነናለች። ምሳ 11÷21 "የጻድቃን ዘር ግን ይድናል" እንደተባለ እኛ እርቶዶክሳዊያን ከእመቤታችን ጀምሮ ለጻድቃን የቃል ኪዳን ልጆቻቸው (ዘሮቻቸው) ነንና እኛ ስንጠፋ ዝም የሚሉበት አንጀት የላቸውም። ምሳ 12÷10 "ጻድቅ ለእንስሳው ነፍስ ይራራል"እንደተባለ እንኳንስ ለእኛ ለልጆቻቸው ለእንስሳውም ይራራሉ። የጻድቃን እመቤት ድንግል ማርያም የተጠማውን ውሻ (እንስሳ) እንደራራችለንና ከጥሙ እንዳረካችው ድህነትን ለተጠማን ለእኛ እራርታ

ውስጣዊ ጥማችንን ሁሉ ታረካልናለች። (ምንጭ ታምረ ማርያም)
እንደ ሌሎች አባባል ሳይሆን እግዚአብሔር የለመነችውን አይከለክላትም። ምሳ 10÷24 "የጻድቃን ምኞት ትሰጣቸዋለች" የጻድቃን ንግሥት እመቤታችን ለእኛ የምታቀርበውን ልመናዋን ሁሉ መልስ ይሰጣታል። ትሰጣቸዋለች ተባለ እንጂ ይነፈጋቸዋል አልተባለም።

ምስጋናም ክብርም እንደሚገባት

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ስናመሰግናት አንዳንዶች በውስጣቸው የንደት እረመጥ ይቀጣጠላል። ምስጋና ክብርም ለአንዱ ለእግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለፍጡር ምስጋና ማቅረብ አይገባም ይላሉ። በእርግጥም እግዚአብሔር በባህርዩ ምስጋና ይገባዋል። ይሁን እንጂ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ጀምሮ ለቅዱሳን እግዚአብሔር ለሰጣቸው ክብር የፀጋ ምስጋና እንለግሳቸዋለን። መዝ 32÷1 "ጻድቃን ሆይ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ ለቅኖች ምስጋና ይፋባል" ስለተባለ።

ቅዱሳን ቅኖች ናቸው። ይልቁንም እመቤታችን። የቅኖች ቅን እርሷ ናትና ምስጋና ይገባታል። ቅዱስ ገብርኤል ነገደ መላእክትን ሁሉ ወክሎ "ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነው። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ።" ሉቃ 1÷28 ብሎ አመስግኗታል። ቅዱስ ገብርኤል መመስገን የሚገባው እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን እረስቶት ነውን? አይደለም። ለእመቤታችን የፀጋ ምስጋና እንደሚገባት አውቆ እንጂ።

ኤልሳቤጥም በመንፈስ እግዚአብሔር ተቃኝታ "አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ። የማሕፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።"ሉቃ 1÷42 ብላ ምስጋናን አበርክታላታለች። ማንም መንፈስ እግዚአብሔር ካገዘው በቀር እመቤታችንን ማመስገንም ማፍቀርም አይችልም። ሮሜ 13÷7 "ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ ግብር ለሚገባው ግብርን ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን መፈራት ለሚገባው መፈራትን ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ። "እመቤታችን ቶማስ ቢዲስስው የተቃጠለበትን መለኮት የፈጸች ቅድስት እመቤት ነችና መፈራት ይገባታል። እንፈራታለን።

የከበረውን አምላክ በማህጸኗ ተሸክማለችና ክብርት ነች። ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ ስለተባለ እናከብራታለን። የአምልኮት ያይደለ የአክብሮት ስግደት እናቀርብላታለን።

ከትዕዛዛትም አንዱ እናትና አባትህን አክብር ነው። ይህንን ያልፈጸመ (ከሕግ አንዷን የውጣ የሻረ) ሰማያዊ ቅጣት ይቆየዋል። ዘፀ 20÷12 ማቴ 5÷19 ምድራዊት እናታችን አለማክበር የገሀነም ፍርድ የሚያመጣ ከሆነ የሰማይና የምድር ንግሥት የሆነች አማናዊት እናታችን ድንግል ማርያምን አለማክበራችንማ እንደምን ያስቀጣ?

ልበ አምላክ ዳዊት በእግዚአብሔር መንግሥት መኖር የሚገባቸውን ሰዎች በመስፈርት ሲያስቀምጥ:- መዝ 14÷1-5

<u>"እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የሚያከብር</u>
ለባልንጀራው የሚምል የማይከዳ
ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር
በንጹህ ላይ መማለጃን የማይቀበል
<u>እንዲህ የሚያደርግ ለዘለዓለም አይታወክም"</u>

እግዚአብሔርን የሚፈሩ ከእመቤታችን ጀምሮ ቅዱሳን ናቸው። እነርሱንም የሚያከብር ለዘለዓለም በገሀነም እሳት አይታወክም (አይጨነቅም) ለድንግል ማርያም ክብርን የሚነፍጋት ግን በሰማይ በምድር፣በነፍስ፣ በሥጋ <u>ለዘለዓለም</u> ሲታወክ ይኖራል።

<u>የሚዘልፉት ሳይቀጣ አይቀርም</u>

የእግዚአብሔር ካህን ዘካርያስ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ባለመቀበሉ ተቀጣ ዲዳም ሆነ ሉቃ 1÷20 የድንግል ማርያምን ቃል አለመቀበል ደግሞ ሳያስቀጣ አይቀርም። የእርሷም ቃል ሉቃ 1÷48 "ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል" የሚል ነው። እርሷን ብፅዕት ውድስት፣ ክብርት ብሎ ለማመስገን የሚጸየፉና ቃሏን የናቁ ጥቂቶች አይደሉም። የእመቤታችንን ክብር በድፍረት የናቁና ቃሏን የተቃወሙ የዘለፏትማ እንደምን አይቀጡ?

መዝ 30÷18 "በድፍረትና በትዕቢት በመናቅም
በጻድቅ ላይ የሚናገሩ

የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ"

ተጠራጣሪዎች ስለእመቤታችን ሲነገራቸው እኛ እኮ እንወዳታለን ማለታቸው አይቀርም። ዘወር ብለው ግን በድንግልናዋ፣ በንጽህናዋ፣ በአማላጅነትዋ ላይ በድፍረት፣ በትዕቢት በመናቅ የሚናገሩት ቃል ለጆሮ ይሰቀጥጣል። እንደ እግዚአብሔር ቃል እንወዳታለን። ባለ ከንፈራቸው ይህንን ተናግረዋልና "የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ" የሚል እርግማን ወድቆባቸዋልና ያስቡበት።

<u>የሚጠሏት ሳይቀጣ አይቀርም</u>

መዝ 128÷5 ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ ይፈሩ
<u>ወደ ኋላቸውም ይመለሱ።</u>

ጸወነ ሥጋ ጸወነ ነፍስ (የሥጋም የነፍስም መጠጊያ) ድንግል ማርያምን የሚጠሉ በጌታ ምጽአት ያፍራሉ። ማቴ 7÷23 "የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቃችሁም እናንተ አመጸኞች ከእኔ እራቁ ብዬ እመሰክርባችኋለሁ።" ከዚህ የበለጠም ሀፍረት የለም። የእናቱን ክብር አላወቁምና እርሱም አላውቃችሁም ብሎ ያሳፍራቸዋል። እግዚአብሔር ያላወቀን ማን ሊያውቀን ይሆን?

<u>ወደ ኋላቸውም ይመለሳሉ</u>: ጌታችን በወንጌል "እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚመለስ የለም" ብሎ ነበር ሉቃ 9÷62። መናፍቃን ግን ከእውነተኛዋ ሃይማኖት ተለይተው ከህይወት ወደ ሞት፣ ከብርሃን ወደ ጨለማ፣ ከእውቀት ወደ ድንቁርና፣ ከመንግሥተ ሰማያት ወደ ገሀነመ እሳት ወደ ኋላቸው ተመልሰዋልና፤ ዳዊት ወደ ኋላቸው ይመለሱ ሲል አስቀድሞ ተናገረ።

ኢሳ 60÷12 "ለአንቺ የማይገዛ ሕዝብና መንግሥት ይጠፋል"

ኢሳ 49÷25-26 "ከአንቺ ጋር የሚጣሉትን እጣላቸዋለሁ
ልጆችሽንም አድናለሁ።

<u>አስጨናቂዎችሽንም ዋጋቸውውን አስብላቸዋለሁ</u>: የተባለው ,

ቃል እናስብ። ሄሮድስ ድንግል ማርያምን አስጨንቆ በግብጽ በረሀ ቢያሳድዳት መጨረሻው አዕምሮውን ስቶ የገዛ ሥጋውን እየቦጫጨቀ ክፉ አሟሟት ሞቷል። ፍጻሜውም የከፋ ሆኗል። (ቀዳማዊ ሄሮድስ) መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን ከእርሷ ጋር የሚጣላ ሕዝብም ሆነ መንግሥት ይጠፋል። (የሄሮድስ መንግሥት እንደጠፋ)

ምሳ 30÷17 "በአባቷ የምታላግጥን
የእናትዋን ትእዛዝ የምትንቅ ዓይን
የሸለቆ ቁራዎች ይጎጠጉጡአታል
አሞራዎችም ይበሉአታል"

ሰሙ:- በምድራዊ አባቱ የሚያላግጥ
የሸለቆ /የሲኦል/ ቁራዎች /አጋንንት/
ያስጨንቁታል።
አሞራዎች /አጋንንትም/ ያስጨንቁታል።

ወርቁ:- በሰማያዊ አባቱ በእግዚአብሔር ላይ የሚላገድን፣ የሰማያዊ እናቱ የድንግል ማርያምን ፍቅር የሚያቃልል ትዕዛዟንም የሚንቅ፣ትውልድ ሁሉ ብጽዕት ይሉኛል የሚለውን የማይቀበል የሲያል ቁራዎች /አጋንንት/ ያስጨንቁታል።አሞራዎችም ይበሉታል /አጋንንትም በገሀነም ያስጨንቁታል ሲል ነው።

<u>ኃጥእ ድንግል ማርያምን ያውኳታል</u>

<u>ምሳ 24÷15 "እንደ ኃጥእ በጻድቅ ቤት ላይ አትሸምቅ ማደሪያውንም አታውክ"</u>

ሰሎሞን በጥበብ ቃሉ <u>የጻድቅ ቤት</u> አላት የፀሐየ ጽድቅ የኢየሱስ ክርስቶስ የዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን ቤቱ ነችና <u>አትሸምቅ</u> በእርሷ ላይ ክፉ አትናገር /አታስተምር/ ማደሪያው ድንግል ማርያንም በክህደት አታውካት ሲል አስቀድሞ ይቀኝ ነበር።

<u>"ድንግል ማርያም ለአምላክ የምስጢር መዝገቡ ናት"</u>
<u>ሉቃ 2÷15-19 2÷41-51 "ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።"</u>
<u>"እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልባ ትጠብቀው ነበር።"</u>

ወንጌላዊው በአንድ ምዕራፍ ላይ ቃሉን ለምን ደጋገመ?

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በልባ እያሰበች ትጠብቀው የነበረው ምስጢር ምንድን ነው? በእርግጥም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከመጸነሷ በፊትና በኋላ በርካታ የእግዚአብሔርን ምስጢር በልባ ይዛ ነበር። ይህንንም የምስጢር ባለቤት እግዚአብሔር በልባ አኑሮላት ሳለ ምስጢሩን ትጠብቀው ነበር እንጂ ለማንም አትገልጸውም ነበር። የአምላክ ልዩ የምስጢር ጓዳው ነችና። ለምን አልተናገረችውም? ምስጢሮቹስ ምን ምን ናቸው?

ሀ. በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል የተነገረላትን ብሥራታዊ ቃል ሰምታ በልባ ይዛ ነበር። በድንግልና ጸንሳ በድንግልና እንደም ትወልድ ቅዱስ ገብርኤል ነግሯት እያለ እርሷ ግን መልአክ መጥቶ በድንግልና ትወልጃያለሽ አለኝ ብላ የእግዚአብሔርን ምስጢር ለማንም አልተናገረችም። "አልታበየችምም" የተነገራት ቃል ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ቃል ነው።"(በድንግልና ጸንሶ በድንግና መውለድ)"እግዚአብሔር ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ ሥራ በእኔ ላይ አደረገልኝ ብላ ለሰዎች አላወራችም።

ከእለታት አንድ ቀን ዮሴፍ ጸራቢ ነውና ንግድ ሄዶ ሦስት ወር ቆይቶ ሲመለስ ዮሐንስ የሚባል ፈላስፋ ወዳጁን አገኘ። ተጫውተው ሲሸኘው ዮሐንስ እንዲህ ሲል ጠየቀው "ብላቴናይቱ ማርያም ጸንሳለች። ከንቱ ነውን? ቢለው ዮሴፍም "እንኳንስ በገቢር (በሥራ) በሀልዩ (በሀሳብ) አላውቃትም"አለው። ዮሴፍም

እንዲጠብቃት ተሰጥታዋለችና ከባድ ጭንቀት ወድቆበት እመቤታችንን እንዲህ አላት "ኦ <u>ወለቱ</u> እስራኤል መኑ ቀረጸ

አክናፈ ድንግልናኪ" የእስራኤል ሴት ልጅ ማርያም ሆይ ከድንግልና ክብር ማን አሳነሰሽ ቢላት እርሷም መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል በድንግልና ጸንሰሽ በድንግልና ትወልጂያለሽ ብሎ ከነገረኝ በቀር ምንም ምን የማውቀው ነገር የለም አለችው እንጂ ሌላ አልመለሰችለትም። በመንፈስ ቅዱስ መጸነሷን በልቧ ታውቀዋለች ይሁን እንጂ ለአምላክም የምስጢር መዝገቡ ነችና በእርሷና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ምስጢር አልገለ ጸችውም።

ለ. እመቤታችን ቅድስት ደንግል ማርያም ጌታን ከመጸነሷ በፊት ለልጇ የሚነገረውን የትንቢት ቃል በልቧ ሰንቃ በተስፋ ትጠብቅ ነበር። በቤተ መቅደስ ውስጥ ስትኖር መጽሐፍትን ስታነብ ትንቢተ ኢሳይያስ ም. 7 ቁ 14 ላይ ብትደርስ "እነሆ ድንግል በድንግልና ትጸንሳለች። ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች። የሚለው ላይ ደረሰች። በዚህ ጊዜ ከዚህች ድንግል ከዘመኗ ደርሼ ውሃ ቀድቼ፣ እንጨት ሰብሬ፣ ባገለገልኳት አለች እንጂ ድንግል ሆና ሳለ የኢሳይያስ ትንቢት የሚፈጸመው በእኔ ላይ ነው ብላ የእግዚአብሔርን ምስጢር ያለጊዜው አላወጣችም። ለእኔ የተነገረ ትንቢት ነው ብላም አልታበየችም እናታችን ከንቱ ውዳሴን አጥብቃ ትጸየፈዋለች። ትሁትም ነችና።

ሐ. መልአኩ ሲያበስራት ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ ብሏታልና በሴቶች ያለ ልማድ ሁሉ በእርሷ ላይ የለም። ሴቶች ሲወልዱ በብዙ ጭንቅ ነው። ዮሐ 16÷21 እርሷ ስትወልድ ግን ጭንቅና መከራ አላገኛትም። ላብ ከሰውነት ሲወጣ ሰውነትን እንደሚያም ሁሉ አምላክ ከእርሷ ሲወለድ እንዲሁ ህመም አልተሰማትም ነበር። በክብረ ወሊድ ላይ ክብረ ድንግልናን እስተባብራ ይዛ፣ ያለ ህመም ፈጣሪዋን ወልዳ ሳለ ይህንን የእግዚአብሔርን ምስጢር ባለመታበይ ለማንም ሳታወራ በልባ ይዛ በምስጢር ትጠብቀው ነበር። የእግዚአብሔር ምስጢር ያለውን የሚገለጥበት ጊዜ አለውና "ከሴቶች ሁሉ ተለይቼ ያለሁን ወለድኩ አላለችም። ለአምላክ ልዩ የምስጢር መዝገቡ ነችና።"

መ. ቅድስት ኤልሳቤጥ ከአረጀች በኋላ በእግዚአብሔር ፈቃድ ዮሐንስን በጸነሰች ጊዜ ለአምስት ወር ያህል ከቤቷ ተሰውራ ነበር። ሉቃ 1÷24-25። መሰወሯ ስለ ሁለት ነገር ነው:-

1ኛ. እግዚአብሔር ነቀፌታዋን አስወግዶ ድንቅ አድርጎላታልና አምላኳ እግዚአብሔርን በሱባኤ ለማመስገን፤

2ኛ. የእግዚአብሔርን ክብር ባላወቁ ሰዎች ዘንድ በስተእርጅና መውለዷን አይተው የእግዚአብሔርን ሥራ ሊያናንቁትና በማያውቁት ምስጢር ተሰናክለው እንዳይቀሰፉ ስትል ለአምስት ወር ተሰውራ ነበር።

ዮሐንስ በተጸነሰ በስድስተኛው ወር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ወደ ኤልሳቤጥ ሄደች። ስትሄድም ከሰዎች ተሰውራ አትክልት አትክልቱን፣ ጮቃ ጮቃውን፣ እንጂ በሜዳ አልሄደችም። ይኸውም ሰዎች ከእውቀት አድማሳቸው በላይ የሆነው የጽንሷን ነገር በሥጋ ጥበብ እንመረምራለን ብለው እንዳይጎዱ (እንዳይሰነካከሉ) አስባና የእግዚአብሔርን ምስጢር ለመጠበቅ ስትል ነው።

ሠ. አምላክን በቤተ ልሄም ስትወልድ ድንቅ ድንቅ ተአምራት ተፈጽመዋል ይኸውም:-

1ኛ. የብርሃን ድንኳን ተተክሎ ቤተልሄም በዝማሬ መላእክት ተናውጣለች፤

2ኛ. የተራራቁት ሰውና መላእክት በአንድነት ሆነው ቀድሰዋል (አመስግነዋል)

3ኛ. ሰውና እግዚአብሔር ታረቁ ስትል ሚዳቋ ደስታዋን በመዝለል ገልጻለች፤

4ኛ. ሰውና መላእክት፣ ሰውና እግዚአብሔር፣ ሰማይና ምድር፣ ነፍስና ሥጋ ታርቀዋል፤

5ኛ. ሰብአ ሰገል /የጥበበ ሰዎች/ ከሩቅ ምስራቅ መጥተው እጅ መንሻን አቅርበዋል።

በወለደች ወቅት የተደረገውን ሁሉ እግዚአብሔር በፈቀደ ጊዜ እንደሚገልጸውና በሐዋርያቱም እንደሚያናግረው እርሷ በልባ

ስለምታውቅ ይህንን ምስጢር ለማንም አልገለጸችውም።

በአጠቃላይ ከመፀነሷ በፊት እና ከፀነሰች በኋላ፣ በወለደች ጊዜ፣ ከመውለዷ በኋላ፣ ይነበብ፣ ይነገር የነበረውን ድንቅ የእግዚአብሔር ምስጢራዊ ሥራ በልቧ ታስበው፣ ትጠብቀውም ስለነበር እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የአምላክ ታማኝ የምስጢር መዝገቡ ነች።

<u>ለምን በልቧ ታኖረዋለች? ስለምንስ አትገልጸውም?</u>

- ♦ አምላክን የመጸነሷን ነገር ብትናገር ሰዎች እርሷ ከደረሰችበት ብቃት ስላልደረሱ /ስለማይደርሱም/ በእምነት ሊቀበሏት ስለማይችሉ።

- ♦ ሰው እንዳያውቀው ፈልጋ ሳይሆን ጌታችን እንዳለው ማቴ 7÷6 "የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፣ እንቁአችሁንም በእሪያ ፊት አትጣሉ" ነውና የተቀደሰውን የእግዚአብሔርን ምስጢር ለመናፍቃን አደሁድ መስጠት ስለማይገባ ነው። ስለሆነም የአምላክን ድንቅ ሥራ ስለምታከብር፣ ለልጇም ክብር ብላ የጌታችንን ምስጢራዊ ሥራ በልቧ ታኖረው ነበር።

- ♦ ምስጢር ከማያምኑ ሰዎች መሰወር ያለ ነው። ጌታችንም ምስጢረ መለኮቱን በደብረ ታቦር በተራራ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ካሳያቸው በኋላ "የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሳ ድረስ ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ" ብሎ አዟቸዋል። ማቴ 17÷9

የእመቤታችን ልጆች ከሆንን ዱካዋን እንከተል። ወደ እኛ ሕይወት እንመለስና ስንቶቻችን የባልንጀራችንን እንኳን ምስጢር እንጠብቃለን? የወገኖቻችንን ጥፋት በአደባባይ ጎልጉለን ካላወጣን እረፍት የማይሰማን የውሸት ክርስቲያኖች ጥቂቶች አይደለንም። እስቲ ከእናታችን እንማር።

<u>ስለሆነም</u>:-እኛም ለባልንጀራችን፣ ለትዳራችን፣ ለቃል ኪዳናችን፣ ለቤተ ክ
ርስቲያናችን ምስጢር ወዘተ ታማኝ እንድንሆን እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።

<u>ምዕራፍ ሰባት</u>

<u>መስቀልና ክብሩ</u>

<u>መስቀል ከየት መጣ?</u>

ስለ መስቀል ስንናገር ነገርን ከስሩ ውኃን ከጥሩ እንዲሉ ከመሠረቱ ብንናገር ይቀለናል። መስቀል በገነት ውስጥ ካሉ የተለያዩ ዕፅዋት ግኝት ነው። ከዕፀ ዘይት፣ ከዕፀ ከርካህ፣ ከዕፀ ወይራ፣ ከዕፀ ሥርናይ

(ምንጭ ህማማተ መስቀል ገጽ 30)

ቃኤል ወንድሙ አቤልን በቅንአት ከገደለው በኋላ ጽኑዕ የእግዚአብሔር መርገም ባላዩ ላይ ወደቀበት ደም ያስከረው ቃኤል በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ሆነ። እርሱም ሰውን ባየ ቁጥር ይሸሻል። ሰውም በእርግማን የቆሰለው ሕይወቱን እያየ ይሸሸዋል።

"ማኅበራዊ ሕይወት ጀርባዋን የሰጠችው ቃኤል ብቸኝነት ስለከበደችው ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል የጸጸት ዕንባውን አረጨ። "እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ከምድር ፊት አሳድደከኝ ከፊትህም እሰወራለሁ በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል" አለ እግዚአብሔርም ቃኤልን ያገኘው ሁሉ እንዳይገለው <u>ምልክትን</u> አደረገለት።

<u>ይህ ምልክት ምንድን ነው?</u>

ቃኤልን የሚጠብቅ መልአክ ቅዱስ ሚካኤል ነበር። እግዚአብሔር ይህንን መልአክ በያዘው የነበልባል ሰይፍ የገነትን ዕፅ ቆርጦ ለቃኤል እንዲያመጣለት አዘዘው። መልአኩም የተባለውን ፈጸመ። አምጥቶም ተከለለት። ቃኤልም ያየው ሁሉ እንዳይገድለው ከጥፋት የሚሰወርበት የድህነት <u>ምልክት</u> ሆነለት። ዘፍ 4÷9-15

የዕፅ መስቀል ምስጢር ከዚህ ይነሳል። ይህ የገነት ዕፅ እስከ ሰሎሞን ድረስ ከደረሰ በኋላ ከሰሎሞን እስከ ክርስቶስ ልደት የነበሩ ሰላሳ ነገሥታት በእየ ዘመነ መንግሥታቸው ሲነሱ በየብሮቻቸው

ይለብጡታል። ከዚህ ብር የወሰደ ርጉም እንዲሆን ነበር /ካህናተ አይሁድ ጌታን ከይሁዳ በገዙት ጊዜ ለይሁዳ የሰጡት ከዚህ 30 ብር ነው። ከቃኤል ጀምሮ የነበረው እርግማን በይሁዳ ላይ ወድቋል/።

ጠቢቡ ሰሎሞን ስለዚህ ዕፅ መስቀል ትንቢት ተናግሯል። መኃ 3 "ዘእምኃሲሶን ይትገዘም ወበጎለጎታ ይተከል"ኃሲሶን ከሚባል ቦታ ተቆርጦ በጎልጎታ ይተከላል /የግዕዙን ዳዊት ተመልከት/

እንዳለ አይሁድ ይህንን ዕፅ ኃሲሶን ከሚባል ቦታ ወስደው በጎልጎታ ተክለውታል። በመጨረሻም አይሁድ ጌታችንን ለመስቀል ባሰቡ ጊዜ መስቀልን ከዚህ የገነት ዕፅ አዘጋጅተውታል። መስቀሉ ከተለያዩ የገነት ዕፅዋት የበቀለ እንደመሆኑ ክብደቱ መጠን የለውም" አይሁድ ጌታቸውን ጠልተውታልና መስቀል ተሸክሞ የቀራኒዮን ዳገት ሲወጣ ወገቡ እንክት ብሎ ይሙት ብለው ስላሰቡ ዕፅ መስቀልን ለሞቱ አዘጋጁለት።

ጌታችን ግን የመጣበት አላማ ነውና ሞትን /ዲያብሎስን/ በመስቀል ላይ ድል አድርጎ ለእኛ መስቀልን የድህነት ምልክታችን፣ ከጠላት ቀስት መሰወሪያችን አድርጎ ሰጠን /ለቃኤል የድኅነት ምልክት እንዳደረገለት/ ፍጻሜው ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች የድኅነት ምልክት አድርጎ መስቀልን ሲሰጠን ነው። መዝ 59÷4 ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው።" ተብሏልና

"ድኅነት በመስቀል ላይ የተፈጸመበት ምክንያት

የእኛ ጌታ ለሥራው ሁሉ ምክንያት አለው።

- ሞት በዕፅ /በዕፀ በለስ/ ምክንያት ስለመጣ ሕይወት በዕፀ መስቀል ምክንያት ተገኘ። በዕፅ ምክንያት የወደቀብንን የሞት ቀንበር በዕፅ ምክንያት ሲሰብርልን ነው።

- ዲያቢሎስ በዕፅ ምክንያት አዳምን ቢያሸንፈው ጌታችን በዕፀ የማለ መስቀል አሸነፈለት። ዶላን በዶላ እንዲመክቱ በዕፅ የማለ

ሰይጣን በዕፅ ተመክቶበት ጭንቅላቱን ተቀንጥሶ ወድቋል። የሰይጣንም ጥበብ በክርስቶስ ጥበብ ተንዶ ተሸንፏል። ጠቢባን ሁኑ እንዳለ በወንጌል ማቴ 10÷16 አንድም ሰውን በሞተበት ነገር ማዳን ለእግዚአብሔር ልማዱ ነው። በኖህ ዘመን ዓለም በውኃ ቢጠፋ ሰውን መልሶ በጥምቀት በኩል ውኃን ለድኅነታችን እንዳደረገልን ማለት ነው።ማር 16÷16

- በብሉይ ኪዳን መስቀል የወንጀለኞች መቅጫ ነበር። ጌታችን እንደወንጀለኛ ተቆጥሮ ተሰቀለበት። መስቀሉንም በደሙ ቀድሶ አሁን የወንጀለኞች መቅጫ ሳይሆን የወንጀለኛው የዲያቢሎስ መቅጫ አድርጎ ለእኛ ሰጠን።

- በብሉይ ኪዳን መስቀል የርጉማን መሰቀያ ተብሎ ይታመንበት ነበር። የርጉማን ደም መሬትን ያረክሳል ብለው ስለሚያምኑ ከምድር ከፍ ባለ መስቀል ላይ ይሰቅሉዋቸው ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የእኛን እርግማን በመስቀል ላይ ተሸክሞ ከህግ እርግማን ነፃ አወጣን። በቅዱስ ደሙ ቀደሰን።

የመስቀሉ ጥቅም

ለክርስያኖች ኃይል ነው።

ቆሮ 1÷18 "የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው። ሙሴም የእስራኤል ልጆች ከጠላቶቻቸው ጋር ሲዋጉ እጆቹን ጎንና ጎን ዘርግቶ መስቀል በመስራት ለእስራኤል ልጆች ድልን ያጎናጽፋቸው ነበር። ይህም በመስቀሉ ኃይል ድል እንደሚገኝ ያስተምረናል። ዘፀ 17÷8-16

ኢሳ 49÷22 "እነሆ እጄን ወደ አህዛብ አነሳለሁ አላማዬን ወደ ወገኖቹ አቆማለሁ።" አላማ የተባለ መስቀል ነው። ሙሴ ለእስራኤላዊያን የእባብንም ምስል ሰርቶ በአላማ ላይ ቢሰቅለውና ቢያቆምላቸው እስራኤላውያን ያንን አይተው እንደተፈወሱ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ዘነፍስ ለሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች አላማ የተባለ መስቀልን

ማቆሙ እንዲፈወሱበት ነው። ዘኁ 21÷8-9 ዮሐ 3÷14-15 ንጉሥ ቆስጠንጢኖስ መስቀልን ታጥቆ፣ ዘገር ነጥቆ ከጠላቱ ከመክስምያኖስ ጋር ቢዋጋ ድልን ተላብሶ ሮምን በእጁ ይዞታል።

መስቀል ለሐዋርያት መመኪያቸው ነው።

ገላ 6÷14 "ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ስለ ዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።

መስቀል አራት ማዕዘን የመሆኑ ምስጢር

የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አራት ማዕዘን ባለው መስቀል ላይ የመሰቀሉ ምስጢር ያልገባቸው ክፍሎች ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሳይሆን በወጥ እንጨት ላይ እጆቹን ወደ ላይ አድርጎ ተሰቅሏል እያሉ ያስተምራሉ። /ሎቱ ስብሐት/ እንዲህማ ከሆን ወንጌላውያኑ በመስቀል ላይ ተሰቀለ ከማለት ግንድ ላይ ተሰቀለ፣ መስቀል አሸከሙት ከማለት ግንድ አሸከሙት ብለው በጻፉ ነበር። ግን አላሉም። ዮሐ 19÷27 ማቴ 27÷32

እጆቹን ወደ ላይ አድርጎ የተሰቀለ ቢሆን ኖሮ ጲላጦስ የፅህፈቱን ቃል ከእራሱ በላይ አኖረ ከማለት ይልቅ ከእጆቹ በላይ አኖረ ተብሎ በተጻፈ ነበር። ማቴ 27÷37 ገና ለገና በ16ኛው መ/ክ/ዘ የተነሳው ማርቲን ሉተር ማንም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን እንደፈለገ መተርጎም ይችላል ስላላቸው ቅዱስ መጽሐፍን እንደ ሥጋ ፈቃዳቸው ባይተረጉሙት ጥሩ ነው።

ወደ ምስጢሩ ስንሄድ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አራት ማዕዘን መስቀል ላይ መሰቀሉ በአራቱ በህርያተ ሥጋ ድካመት የመጣን መርገም አራት ማዕዘን /አቅጣጫ/ ባለው መስቀል ላይ ሆኖ ድል ማድረጉን ሲያጠይቅ ነው። በአራቱ ባህሪያተ ሥጋ ድካመት ድል ያገኘ ሰይጣን በአራት ማዕዘን መስቀል ላይ ድል ተደርጎ መውደቁን ሲያሳየን ነው።

አንድም ለአራቱም ማዕዘናተ ዓለም /ለሰሜን፣ ለደቡብ፣ ለምሥራቅ እና

ለምዕራብ ሙሉ ደህንነት መስጠቱን ሲያጠይቅ ነው።

ካህናት የሚይዙት የመስቀል ዓይነት ትርጉም

የወርቅ መስቀል:- ወርቅ ነገሥታት ለክብራቸው ይለብሱታል። የነገሥታት ንጉሥ መድኃኒታችን እንደተሰዋበት ለማጣየቅ ነው። ወርቅ ክቡር ነው። መስቀልም በክርስቶስ ደም መክበሩን ለማሳየት ነው።

የብረት መስቀል:- ብረት በቀላሉ አይሰበርም። ክርስቶስ መከራን በተቀበለ ጊዜ አጥንቱ ላለመሠበሩ ምልክት ነው። አጥንቱ አለመሰበሩም ጌታችን በሥጋ እንጂ በመለኮት መከራን ላለመቀበሉ የሚያጠይቅ ነው። እስራኤል የፋሲካን በግ ሲያርዱ አጥንቱን አትስበሩ እንደተባሉ ዘፀ 12÷46 ምሳሌነቱ ለክርስቶስ ቤዛነት ነው። አንድም በብረት ቀኖት መቸንከሩን ለማሰብ አባቶቻችን ካህናት የብረት መስቀል ይይዛሉ።

የነሀስ መስቀል:-ነሀስ ፅሩይና ብሩህ ነው። በመስቀል ላይ በተደረገልን ቤዛነት ከሲዖል ድቅድቅ ጨለማ መጥተን ብሩህ /ብርሃናዊ/ ሕይወትን መኖር መጀመራችንን ለማጠየቅ ካህናት የነሀስ መስቀል ይይዛሉ።

በመስቀል ላይ የተቃዋሚዎች ጥያቄ

ለምን ትሳለሙታላችሁ? /ትባረኩበታላችሁ/

መስቀል በጌታችን ደመ መለኮት ስለተቀደሰ እንስመዋለን /እንቀደስበታለን/ የተቀደሰውን ነገር እንኳንስ መሳም ብንዳስሰው እንደምንቀደስ ቅዱስ መጽሐፍ ያስተምረናል። ዘፀ 30÷29

ያዕቆብም የልጁ የዮሴፍን ልጆች ሲባርክ እጆቹን በመስቀል

አመሳቅሎ ነበር የባረካቸው። ዘፍ 48÷14 በመስቀል ቡራኬ እንደሚገኝ ያዕቆብ ያውቃልና።

ካህናት አባቶቻችንም እግዚአብሔር ለሙሴና ለአሮን የእስራኤልን ልጆች ስትባርኩ እንዲህ በሉአቸው በተባሉበት የቡራኬ ቃል መሠረት ይባርኩናል። ዘፍ 6÷22-26

ለምን ትሰግዱለታላችሁ?

መዝ 131÷7 "እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን"
የጌታችን እግሮች በመስቀሉ ላይ ቆመዋልና እግሮቹ ለቆሙበት መስቀል እንሰግዳለን።

መዝ 98÷5 "ቅዱስ ነውና ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ።
መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራኒዮ ውሎው የእግሩ መረገጫ አድርጎ መስቀልን ተረግጦበታል። በወርቀ ደሙም ቀድሶታል። ስለሆነም ቅዱስ ነውና ለእግሩ መረገጫ መስቀል እንሰግዳለን።

ሮሜ 13÷7 "ክብር ለሚገባው ክብር መፈራት ለሚገባው መፈራትን ስጡ።
መስቀል በከበረው በክርስቶስ ደም ስለከበረ ክብር ይገባዋል። ስለሆነም የአምልኮት ያይደለ የአክብሮት ብንሰግድለት ወንጀሉ ምን ላይ ነው?

መስቀል የአባታችን ገዳይ ነው? እንዴት?

ሰይጣን ምንግዜም የሚሸነፍበትን መሣሪያ ማውገዝ ልማዱ ነው። ዛሬ የመስቀሉ ጠላቶች ፊል 3÷18 መስቀል ጣዖት እንደውም የአባታችን ገዳይ ነው ሲሉ ይሰማሉ።

መስቀል የገደለው ማንን ነው?

ኤፌ 2÷16 "ጥልን በመስቀሉ <u>ገድሎ</u> በእርሱ ሁለታችንን በአንድ

አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው።

ጥል የጥልም አባት ዲያብሎስ በመስቀል ላይ በተደረገው ቤዛነት ራስ ራሱን ተቀጥቅጦ ወድቋል ተገድሏልም።
ቆላ 2÷14 "በእኛ ላይ የነበረውን በትዕዛዛት የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም <u>በመስቀል ላይ ጠርቆ (አስጨንቆ)</u> ከመንገድ አስወግዶታል። አለቅነትና ሥልጣናትን ገፎ ድል በመንሳት በእርሱ እያዞራቸው በግልጽ አሳያቸው።

በመስቀል ቤዛነት ተጠርቆ ከመንገዳችን የተወገደው ሰይጣን ነው። አለቅነትና በሰው ልጆች ላይ የነበረውን ሥልጣን በቀራኒዮ አደባባይ ተገፎ ሽንፈትን ተከናንቧል።

መስቀል የአባታችን ገዳይ ነው የሚሉ ሰዎች ሳያውቁት መንፈስ ቅዱስ አባታቸው ዲያቢሎስ መሆኑን እያስመሰከራቸው ነው። ምክንያቱም በመስቀል የሞተው (የተቀጠቀጠው) ዲያቢሎስ እንጂ ክርስቶስ አይደለምና። <u>ክርስቶስማ በፈቃዱ የሞተ የባህርይ አምላክ ነው።</u>

ሊቀ ካህናት ሐና ብዙዎች ከሚሞቱ አንድ እርሱ ይሙት ብሎ ሳያውቀው እውነት እንደተናገረ፤ እነርሱም ሳያውቁት በመስቀል የተጠረቀው ዲያብሎስ የግብር አባታቸው እንደሆነ እውነቱን እያናገራቸው ነው።

- መስቀል ጠላታችን አይደለም። ጠላትነቱ ለሰይጣን እንጂ።
- መስቀል ጌታችንን አልገደለውም ዲያብሎስን እንጂ።
- መስቀልን አከበርን እንጂ አላመለክነውም /ጣዖት ሊባልም አይገባም/

የሚገርመን ግን መስቀልን እንደ ጣዖት በተጸየፉበት እንደበታቸው የጸሎት ቤታችን ነው በሚሉት አዳራሾቻቸው ጣሪያ ላይ መስቀል መስካታቸው ነው። እንደ ጣኦት ከተመለከቱት ለምን እንደ አርማ ይተክሉታል? የቅዱስ መጽሐፍን ትርጉም እንደማያውቁት ሁሉ የሚናገሩትንም አያውቁትም ማለት ነው። የተከሉትም ሊድኑበት ሳይሆን ለማስመሰል እንደሆነ ግልጽ ነው።

ምዕራፍ ስምንት

ስግደት በቤተክርስቲያን

ራዕ 13÷5-6 "ታላቅ ነገርና ስድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው። እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይ የሚኖሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ" ተብሏልና ሃሣዊ መሢሕ ሲገለጥ የሰማይ ቅዱሳን፣ በእግዚአብሔር ክብር፣ ማደሪያው በሆነችው በቅድስት ድንግል ማርያምና በቤተክርስቲያን ላይ የስድብ ናዳውን እያወረደ እንደሚገልጽ ቅዱስ መጻሐፍ ያስተምረናል።

የሃሣዊ መሢሕ መንገድ ጠራጊዎች ዛሬ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆነች ቅድስት ቤተክርስቲያንን የጣዖት ቤት በማለት ስድባቸውን ተያይዘውታል። እኛም ክርስቲያኖች ለጣዖት እንደምንሰግድና እንደምንሳለም አድርገው ያስተምራሉ። እንግዲያው መጽሐፍ ቅዱስ ይዳኘን።

እንኳንስ ክርስቶስ በወርቀ ደሙ የዋጀት ቤተክርስቲያን ኤልያብና ባስልኤል የተከሏትና እግዚአብሔርም ክብሩን የሚገልጽባት በኦሪት መገናኛ ድንኳን የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር የሚገባውን ስግደት እያቀረቡ ይባረኩ ነበር። ዘፀ 33÷7-10

ብሉይ ኪዳን ለሐዲስ ኪዳን ጥላ(ምሳሌ) ነውና የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች እስራኤል ዘነፍስ በመገናኛው ድንኳን በምትመሰልልን ቤተክርስቲያን ተሰባስበን ስግደትን አቅርበን ብንባረክ ይዘን የመጣነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ስርዓት እንጂ ስህተቱ ምኑ ላይ ነው?

መዝ 28÷2 "የስሙን ክብር ለእግዚአብሐር አምጡ
በቅድስናው ሥፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ"
መዝ 137÷2 "ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ"
መዝ 5÷7 "እኔ ግን በምህረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ

አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ"

ልበ አምላክ ዳዊት ለቤተ እግዚአብሔር ስግደት እንደሚያቀርብ ከነገረን በኋላ እንዲያውም ቅጽሯ ውስጥ እንኳን ልንገባ የምንችለው ምህረቱ ሲከተለን ብቻ እነደሆነ ገልጾታል።

ቅዱስ ዳዊትን የመሰለ የእግዚአብሔር ባለሟል በመቅደስ ስለሰገደ ለጣዖት ሰገደ ማለት ነው? አያደርገውም። ያዕቆብም በሎዛ ምድር ላይ ተኝቶ ራዕዩን ተመልክቶ ሲነቃ ያቺ ስፍራ ቅድስት መሆኗን መንፈስ ቅዱስ ቢያስረዳው "በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ ፈራ እንዲህም አለ። <u>ይህ ሥፍራ እንዴት ያስፈራል? ይህ ሥፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው እንጂ የሌላ አይደለም ይህ የሰማይ ደጅ ነው።</u> በዚህም የእግዚአብሔር ቤት ይታነጻል። ዘፍ 28÷10-17 " ይህች የእግዚአብሔር ደጅ ነች ጻድቃን ወደሷ ይገባሉ"። ብሏል በእውነትም መናፍቃን በእርሷ ገብተው ለዘለቄታው ኑፋቄአቸውን እንደያዙ አይኖሩባትም። ስለማይገቡባትም ነው ከውጭ ሆነው የሚሳደቡት። አይደንቀንም።

ቤተ መቅደስ እግዚአብሔር በእግረ መንፈስ ቅዱስ፣ በሀምሳለ ሀብስት የሚቆምባት ቅድስት ሥፍራ ነችና እርሱ ለቆመባት ሥፍራ እንስግዳለን።

መዝ 131÷7 "ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን እግሮቹ በሚቆሙበት ሥፍራ እንሰግዳለን።"

ዘዳ 25÷ 8 "በመካከላችሁ አድር ዘንድ መቅደስን ሥሩልኝ" ተቃዋሚዎች እንደሚሉት ቤተመቅደስ ጣዖት ቢሆን ኖሮ እግዚአብሔር ሥሩልኝ በማለት ፈንታ የተሠራውንም አፍርሱልኝ ባለ ነበር። አላለም።

ቤተ መቅደስ በሐዲስ ኪዳን አልተሻረችም

ክብር ይግባውና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ መቅደስን ባርኮ ሰጠን እንጂ ሻረው የሚል አላየንም እንዲያውም በነቢያት

ማቴ 22÷40፣ ማቴ 5÷17 ጌታችን የነበረውን ሕግ አጸናው እንጂ ማቴ 22÷40፣ በመስቀል ላይ ሲሰዋ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደዱን ማስረጃ በማድረግ ይህ የቤተ መቅደስን መሻር የሚያሳይ ነው ብለው የሚያስተምሩ ክፍሎች አሉ። ማቴ 27÷51 ነገር ግን የቤተ መቅደስ መጋረጃ ለሁለት መቀደዱ እነርሱ እንዳሉት የሚተረጎም ሳይሆን በሰው ልጆችና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው የጥል መጋረጃ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት መቀደዱን የሚያበስረን ምስጢር ነው። በጌታችን ሞት የተደረገው ተአምር የመጋረጃ መቀደድ ብቻም አይደለም። ፀሀይ ጨልማለች ያኔ የመቅደሱ መጋረጃ ተቀዷልና ቤተ መቅደስ አያስፈልግም ከተባለ በዚያን ጊዜ የጨለመችው ፀሀይም አታስፈልግማ? ብርሃኗን ትከልክል? የምድር መናወጥም ሆኖ ነበር። ዛሬም የምድር ሰላም አያስፈልግምን? ምን አለበት በጠማማ ትርጉም የሰውን ሕይወት ባያጣምሙ?

ቤተመቅደሱን ቢሽረውማ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የቤቴ ቅናት ይበላኛል ብሎ ከሻጮችና ከለዋጮች መቅደሱን ከማጽዳት ይልቅ ዝም ማለት በቀለለው ነበር፤ ማቴ 21÷12-13 ሁሉን ከእርሱ እንድንማር የሚፈልግ ጌታ ነውና እርሱ ከልጅነቱ ጀምሮ በሥጋ ወራት ሲመላለስ በመቅደስ መኖርን አሳይቶናል። ሉቃ 2÷49 "በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አታውቁምን"? አለ። የሚገርመን ግን ጌታ የአባቴ ቤት ያላትን መቅደስ መናፍቃኑ የጣዖት ቤት ማለታቸው ነው። እኛስ ቤተመቅደስ የአባታችን የእግዚአብሔር ቤት ናት። የአባታቸው ቤት መሆኑን አውቀው ሐዋ ነበር ሐዋርያት ዕለት ዕለት በመቅደሱ የሚሰበሰቡት ሉቃ 24÷53፣ ሐዋ 2÷24-47 ተቃዋሚዎች ይህን ማስረጃ ሲያቀርቡላቸው ሐዋርያት ይህንን ያደረጉት መንፈስ ቅዱስ ስላልቃኛቸው በስህተት ነው። ብለው ይናገራሉ። ነገር ግን ሐዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ከተቃኙም በኋላ በቤተመቅደስ እየተገኙ ይጸልዩ ድውያንንም ይፈውሱ ነበር። ሐዋ 3÷1-10

ሐዋ 22÷17 "ወደ ኢየሩሳሌም ከተመለስሁ በኋላ በመቅደስ ስጸልይ ተመስጠ መጣብኝ" ሲል ቅዱስ ጳውሎስ ይነግረናል። ልጁ ጢሞቴዎስንም ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በኋላ በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር እንደሚገባው ይነግረዋል። ጢሞ 3÷15

ቤተ መቅደስ በሰማይም አለ

ራዕ 15÷5 " ከዚህ በኋላ አየሁ የምስክር ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ" ራዕ 11÷19 "በሰማይ ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ የቃልኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ"። ቤተመቅደስን ጣዖት የሚሉት ክፍሎች መልስ ቢሰጡን እንወዳለን። እግዚአብሔር ጣዖትን በሰማይ ያኖራልን? ጣዖትስ በሰማይ ስፍራ አለውን? (ሎቱ ስብሐት) ምድራዊት ቤተመቅደስ በሰማይ ላለችው ቤተመቅደስ ምሳሌ ነች።

ለዚህም ነው ካህኑ በቅዳሴ ማርያም "ሐዳፌ ነፍስ" ላይ ይህችን ምድራዊ ቤተመቅደስ በሞት ስንሰናበታት በሰማያዊት ቤተ መቅደስ መኖርን እንድናገኝ እንዲህ ሲል የሚጸልይልን። ቅዳሴ ማርያም ቁ.159 "የቅዱሳን ነቢያት ማኅበር ወዳሉበት ያግባችሁ፣ ያስተማሩ የሐዋርያት ማኅበር፣ ድል የነሱ የሰማዕታት ማኅበር፣ ብሩካን የሚሆኑ የጻድቃን ማኅበር፣ የተሾሙ የካህናት ማኅበር፣ ትጉሃን የሚሆኑ የመላእክት ማኅበር፣ ፍጹማን ደናግልና የመነኮሳት ማኅበር ወዳሉበት ያግባችሁ። ከሁሉም በላይ ከሆነች ከአንዲት <u>ቅድስት ቤተክርስቲያን</u> ፍጹም አንድነቷ ሁሉ ጋር ከእነርሱም ጋር ታቦት ዘዶር ወዳለችበት ይህችውም እመቤታችን ማርያም ናት"።

እግዚአብሔር በደላችንን ሳይቆጥርብን በሰማይ መቅደሱ በክብር እንዲያኖረን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

ቤተክርስቲያን በምሳሌ

እንደሚታወቀው ሁሉ ቤተክርስቲያን መሠረቷ መጽሐፍ ቅዱስ እንደመሆኑ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ በብዙ በኅ በኅ ህብረ ነገር ተመስላ እኛ ጋር ደርሳለች። ከምሳሌዎቿ በጥቂቱ....

1. <u>ገነት</u>

ገነት መንግሥተ ሰማያት በዳግም ምጽአት እስክትከፈት ድረስ

ቅዱሳን የሚቀዩበት ቅድስት ሥፍራ ነች። የገነትን ውበትና መአዛ ይህን ይመስላል ብሎ ለመግለጽ ይከብዳል። እንዲያው ዕፁብ ማለት እንጂ። በውስጥዋ ያለው መአዛ ቅዱሳንን ሲያጠግባቸው ይኖራል።

ከመዓዛዋ ጋር የልምላሚዋ ውበት ሲደመር ለሕይወት ልዩ ተመስጦን ይፈጥራል። በገነት ሀዘን ጨርሶ አድራሻው የለም። በመንፈሳዊ ደስታ ተመልታለች በጽድቅ ተወስነው በምድር ሐዘን ያንገላታቸውን የናፈቋትን ደስታ የሚወጡት በገነት ነው። የተጎዱም ዋጋቸውን በእጥፍ እንደ አልአዛር ያገኙባታል። ሉቃ 16÷19።

ቤተክርስቲያን የገነት ምሳሌ ነች በገነት ልዩ ልምላሜ እንዳለ ሁሉ በቤተክርስቲያን ልምላሜ ጽድቅ አለ። በተጨማሪም በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ያሉ ወይራዎች፣ ጽዶች፣ ባሕር ዛፎችና የመሳሰሉት ዕጽዋት ሁሉ ያለምክንያት አልተቀመጡም። የቤተክርስቲያን የገነት ምሳሌ ስለሆነች ነው። ዕጽዋቱን ስንመለከት ልምላሜ ገነትን እንድናስብ ያደርገናል።

በገነት ደስታ እንጂ ሀዘን እንደሌለ በቤተክርስቲያንም ደስታ መንፈሳዊ አለ። በንስሐ በደላችን ሲደመሰስ፣ በክርስቶስ ሥጋና ደም ስንቀደስ፣ ጋብቻን በተክሊል ስንፈጽም፣ ከካህናቱ ቡራኬ ስንቀበል፣ እንደቅዱሳን መላእክት ስንዘምር ፣ በእግዚአብሔር ቃል ውስጣችን ሲረካ ይህንና የመሳሰሉትን ስንፈጽም ሕይወታችን በመዓዛ መንፈስ ቅዱስ ይረካል። ሀዘናችን በደስታ ይለወጣል። መንፈሳዊ ሰው ላዩ የጠወለገ ይመስላል እንጂ ውስጡ ግን በእግዚአብሔር ሰላም ደስተኛ ነው። መዝ 63÷10።

ሄኖክ ከብቃቱ (ከቅድስናው) የተነሳ ሀብቱን ለልጁ ለማቱሳላ ሰጥቶ ከገነት ስር ተሰውሮ ይጸልይ ነበር። "ወተከብተ ሄኖክ ታሀተ ዕፀ ገነት" እንዲል (ትርጓሜ አሪት) ሄኖክ ማለት ሐዲስ ማለት ነው። ሄኖክ ናዝራዊ (ለእግዚአብሔር የተለየ) ነው።

ዕድሜው 365 ሲሆን ዘመኑን በሙሉ ያሳለፈው በቅድስና ነው። ሄኖክ እስከአሁን ድረስ ሞት አላገኘውም ከገነት ስር የሰወረው ፈጣሪው ከሦስት መቶ ስልሳ አምስት ዕድሜው በኋላ ወደ ብሔረ ሕያዋን

ወስዶታል (ሰውሮታል)። ዘፍ 5÷24 "ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም። እግዚአብሔር ወስዶታልና" ሄኖክ ገነትን ተጠግቶ ቢጸልይ ከሥጋ ሞት እንደተሰወረ የገነት ምሳሌ ቤተክርስቲያንን የተጠጋ ሁሉ ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ መሰወር እንደሚቻለው የሚያስረዳን ምስጢር ነው።

2. <u>ጠፈር</u>

<u>ጠፈርን</u> ቀና ብለን ወደላይ ስናንጋጥጥ የምንመለከተው ውኃ አዘል ሰማይ ሲሆን፤ የሥነ ፍጥረት ትምህርታችን ጠፈር ይለዋል። በጠፈር ላይ ፀሐይ፣ ጨረቃና ከዋክብት ሰዓታቸውን ጠብቀው ብርሃናቸውን ያለማቋረጥ እንደየአቅማቸው ሲፈነጥቁ ይኖራሉ። ሰው ጨለማውን የሚገፍለትን ሁሉ ማፍቀሩ አያጠያይቅምና እነዚህ ጠፈርን የሙጥኝ ብለው የሚገኙ ብርሃናት በተፈጥሮአቸው ለሰው ልጅ የሚሰጡት ነፃ አገልግሎት ከእስከ ስለማይባል የሰው ልጅም ከውስጡ የሚፈነቅለው የደስታ ስሜት ፈጣሪውን እንዲያመሰግን ይቀሰቅሰዋል። ክረምት ከበጋው፣ ፀሐይ ከጨረቃው ጊዜአቸውን ጠብቀው ከተፍ ይላሉ። ይህን የሚሠራ የፍጥረታት ጌታ እግዚአብሔር ነውና ለስሙ የሚቀርበውን ውዳሴ ልንነፍገው አይገባም። በዚህ መሠረት ቤተክርስቲያን በጠፈር ትመሰላለች። ጠፈርን ቀን ከሌሊት በመፈራረቅ ብርሃን እንደማይለዩአት ቤተክርስቲያንም እንዲሁ ቀን ከሌሊት በመፈራረቅ የማይለዩአት ብርሃናዊያን ቅዱሳን መላእክት አሉ።

እናንት የዓለም ብርሃን ናችሁ ማቴ 5÷14 ያለ እግዚአብሔር በቅድስናቸው ለጨለማው ዓለም ብርሃን የሆኑለት ቅዱሳን የፈለቁባት ነችና ቤተክርስቲያን በጠፈር ትመሰላለች። ለዚህም ነው ቤተክርስቲያን የሻማውን፣ የጧፉን ብርሃን የምታበራው። ብርሃን የሆኑ ቅዱሳኖችን ስታዘክራቸው ነው። እግዚአብሔር አፍኒንና ፊንሐስን መብራቱን አታጥፉ ብሏቸው ነበር። እነርሱ ግን በድፍረት አጠፉ። ዛሬ ዓለማችን ብርሃን የሆኑ የቅዱሳንን ታሪክና ክብር የሚያጠፉ የኤሊ ልጆችን እየወለደች ነው። 1ኛ ሳሙ 4፤ <u>እንድም</u>፦ ጠፈር በሰማይ እንዳለ ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም ምድራዊ ያይደለች ሰማያዊት ነች በሌላም በኩል ጠፈር ከምድር ከፍ ያለ እንደሆነ ቤተ ክርስቲያንም ከምድራዊ ጠባይ ተለይታ

በክብር ከፍ ባለ ልዕልና ደምቃ የምትኖር ለመሆኗ ምሳሌ ነው።

3. <u>ዞአር</u>

እግዚአብሔር ወዳጆቹ በጥፋት ዓለም ውስጥ ሲጨነቁ ዝም የሚልበት አንደት የለውም። ወዳጁ ሎጥ በዝሙት እረመጥ በምትነደው በሰዶም ዓለም ውስጥ ይኑር እንጂ ከስምንተኛው የቅድስና ማዕረግ የደረሰ ጻድቅ ሰው ነውና ሰዶማውያን የሚፈጽሙት በደል እርሱን ያስጨንቀው ያስለቅሰውም ነበር። 2ኛ ጴጥ 2÷8።

እምላካችንም በኃጢአታቸው ከሚሰቁት መካከል ስለ ኃጢአታቸው የሚያነቡትን ማዳን ፈቃዱ ነውና። ሕዝ 9÷4-6 የኃጢአት ከተሞችን እንዳልነበሩ ለማድረግ ወሰነ፤ ዘፍ 18÷20 ከብስል መሀል ጥሬን የሚለይ እግዚአብሔር ወዳጁን ሎጥን ከነቤተሰቡ ሊለየው ሁለት መላእክትን ላከለት። ዘፍ 19÷1-29

እንደዘመኑ ተጠራጣሪዎች የመላእክት ክብር ያልታያቸው ሰዶማውያን የሎጥን ቤት ከበው ሴቶች ስለመሰሉአቸው ወደቤቱ የገቡትን ለዝሙት አሳልፎ እንዲሰጣቸው አስጨነቁት። የውስጣቸውን መታወር በግልጽ ለማሳየት አፍአዊ ዐይናቸውን ቅዱሳን መላእክ አሳወሯቸው። ዘፍ 18÷1

በነጋም ጊዜ ሰዎችን ለማዳን የሚፈጥኑ መላእክት ሎጥንና ቤተሰቦቹን ወደዞአር ተራራ ይዘዋቸው ተነጠቁ። እግዚ[illegible]ሔር ሰዶምና ገሞራን የእሳት ዶፍ አዝንቦ አጠፋ። ዛሬ ይህች [illegible]ፍራ በታናሽ እስያ የሙት ባሕር ተብላ ትጠራለች። ዞአር ለሎጥና ለልጆቹ የድህነት መጠጊያ ሆነች። ዞአር የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። ዞአርን የተጠጋ ሎጥ ከጥፋት እንደዳነ ቤተክርስቲያንን የሚጠጉ ክርስቲያኖች ድህነተ ሥጋ ድህነተ ነፍስ፤ በረከተ ሥጋ በረከተ ነፍስን አግኝተው ከጥፋት ለመዳናቸው ምሳሌ ነው።

ወደ ዞአር ለመጠለል የሎጥ ሚስት ታኮብኩብ እንጂ የሰዶም ፍቅር ከልቧ አልወጣምና በናፍቆት ዘወር አለች። የሞትንም ጽዋ ተጎነጨች። ብዙዎች ዛሬ በዞአር ወደምትመሰለው ቤተክርስቲያን

ያኮበኩባሉ ይሁን እንጂ ችግሩ ዞአር ደርሰው በጽናት ባለመኖራቸው የሰዶም ፍቅር ከልባቸው ስላልጠፋ መንገድ ላይ ይቀራሉ። ጌታችን ለዚህ ነው "እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚመለስ የለም" ሉቃ 9÷62 ያለው። የክርስትናን እርፍ ከያዘን በኋላ ነው ወደ ሞት ዓለም የምንመለስ እንዳንሆን በዞአር እንቀመጥ። ዞአር (ቤተክርስቲያን) ከእሳት ዲን የምታስጥለን የድኅነት ዋሻ ነች።

<u>ሎጥ ወደ ዞአር በገባ ጊዜ ፀሐይ ወጣችለት</u>:- የእግዚአብሔር ቃል በከንቱ አልተጻፈም መጽሐፍ ቅዱስ የፀሐይ መውጣት እንግዳ ሆኖበት የተናገረው አይደለም ምስጢር ስላለው እንጂ።

<u>ፀሐይ</u>:-ሙቀትን ትሰጣለች። ሎጥ ዞአር ሲገባ ፀሐይ መውጣቷ በዞአር በምትመሰለው ቤተ ክርስቲያን መኖር ስንጀምር ሙቀት መንፈስ ቅዱስ ከሰማያዊ አባታችን እንደሚሰጠን ሲያጠይቅ ነው።

<u>ፀሐይ</u>:-ብርሃንን እንደምትሰጥ በዞአር ከምትመሰለው ቤተክርስቲያን ስንገባ የወንጌል ብርሃን እናገኛለን ከድቅድቁ የጨለማ ዓለም እንለያለን። እውቀት መንፈሳዊ አገኝተን ኃጢአትን ከጽድቅ፣ ኑፋቄን ከእምነት ለይተን በብርሃን እንመላለሳለን።

<u>ፀሐይ</u>:-በሰማይ እንደምትታይ ሁሉ በዞአር ከምትመሰለው ቤተክርስቲያንም መኖር ስንጀምር ሰማያዊውን ነገር ማየት እንጀምራለን። ሀሳባችንም በሰማያዊ ፍቅር ይመሰጣል። የእኛም ሰማያዊ ዜግነት የጸና ይሆናል። አምላካችንም እኛን በሰማይ ያኖረናል። ዮሐ 14÷1-4 2ኛ ቆሮ 5÷1

4. <u>የኖህ መርከብ</u>

ምንግዜም ምሳሌ ከሚመስልለት ነገር ያንሳል። የኖህ መርከብ ለቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። ኖህ በዚያ የጥፋት ዘመን ከሞት የሚድንበት መርከብ እንዲሠራ እራሱ እግዚአብሔር ነው ያዘዘው። ዘፍ 6÷14 በታዘዘውም መሠረት መርከብን ሠራ እርሱና ቤተሰቦቹ በዚያ ሆኑ የፍጥረታቱ ዘር ወድሞ እንዳይቀርበት የፈለገ እግዚአብሔር ከእንስሳትም፣ ከአራዊትም ከአእዋፍም ሁሉ ተባዕትና አንስትን (ወንድና

ሴቱን) በመርከቡ እንዲሰፍሩ አደረገ ወዳጆቹን ከጥፋት መሰወር ልማዱ የሆነ እምላክ ዓለምን በጥፋት ውኃ ሲያንፍረው ኖህንና በመርከቧ ውስጥ ያሉትን ነፍሳት አንሳፈፈ። ኖህ ጥንትም እራሱን ከኃጢአት ባህር ያንሳፈፈ ሰው ነበር። መርከቧ ከሞተ ሥጋ ሰወረችው። የዛሬይቱ መርከብ (ቤተክርስቲያን) በውስጧ ልጅነትን ተቀብለው በቅድስና የሚመላለሱትን ከሞተ ነፍስ ትሰውራቸዋለች። የኖህ መርከብ በውስጧ ሦስት ክፍል ነበራት ቤተክርስቲያንም ሦስት ክፍል አላት። መቅደስ፣ ቅድስትና ቅኔ ማኅሌት። ኖህ በሦስቱ ክፍል ውስጥ ቀላል፣ መአከላዊያን ክቡዳን ብሎ በመለየት በደረጃ አስቀምጧቸዋል። ይህም በመቅደስ ካህናት፣ በቅድስት ንስሐ የገቡ ሥጋ ወደሙ የተቀበሉ ምዕመናን፣ በቅኔ ማኅሌት ሃይማኖትን በንዑስ ክርስቲያንነት ገና ደጅ የሚጠኑ ሰዎች በየደረጃቸው ለመቆማቸው ምሳሌ ነው። አንድም:- በአንዲት የኖህ መርከብ ውስጥ ሦስት ክፍል መኖሩ በአንዲት ቤተክርስቲያን የሦስትነትና የአንድነት ነገር ለመነገሩ ምሳሌ ነው። የኖህ መርከብ የሰው ልጆችን ብቻ አላዳነችም። አራዊቱንም ጭምር እንጂ። አራዊቱ የአሕዛብ ምሳሌ ናቸው። ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ክርስቲያን የተባሉትን ብቻ የምታድን ሳይሆን አራዊት (አሕዛብም) አዲስ ልደትን ተቀብለው ክፉ ግብራቸውን ጥለው ወደእርሷ ከመጡ ታድናቸዋለች። ቤተክርስቲያን ሰዎችን ከአራዊትነት ጠባይ ለውጣ ከቅዱሳን ጋር በክብር የምታቆም መንፈሳዊት እናት ነች።

ኖህ የካህን፣ በመርከብ ውስጥ ያሉት ነፍሳት የአንድ ቤተሰብ ምሳሌ ናቸው። ይህም ለአንድ ቤተሰብ አንድ ካህን ለማስፈለጉ ምሳሌ ነው። ካህን አልባ ክርስትና በዲያቢሎስ እጅ ይጥላልና።

የሚደንቀው ነገር አውሬ ሌላውን አራዊት አይቶ ዝም አይልም አንዱ በአቅም ሊያጠቃ የሚችለውን አጥቅቶ ይመገበዋል። እርስ በርሳቸውም ይነካከሳሉ። በኖህ መርከብ ውስጥ ይህ አልተፈጸመም። ሁሉም በተሰበረ ልብ ጸጥ ብለው ኖረዋል።

ሐመረ ኖህ (ቤተክርስቲያን) ዛሬም በውስጧ ለሚገቡት ሁሉ እንዲህ ያለውን ጸጋ ነው የምትሰጣቸው። እንደ አራዊት ከሰዎች ጋር በነገር መነካከስና በቦጫጨቅ የሁል ጊዜ ሕይወቱ የሆነ ሰው በቤተ ክርስቲያን ሲገባ፣ በቃሉ መደሻነት ውስጡ ሲፈርስ ያኔ ከክርስቲያኖች ህብረት ሲቀላቀል የፍቅር ተገዢ ሆኖ ይኖራል። ቤተ ክርስቲያን ሰዎችን

መለወጥ ቀዳሚ ሥራዋ ነው በቤተ ክርስቲያን አንዱ ሌላውን ሊያጠቃ አይችልም። ቤተ ክርስቲያን አጺትና የሁሉም ስለሆነች።

5. ትዕማር

የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ ሴዋ የምትባል ሚስት አግብቶ ከእርሷም ኤርን፣ አውናንና ሴሎምን ወለደ። ኤር ማለት ፀሐይ፣ አውናን ወይን ሴሎም ማለት መስተሰላም (አስታራቂ) ማለት ነው። ይሁዳ የበኩር ልጁ ኤርን ከአሕዛብ ወገን መልከ መልካም የምትሆን ትዕማርን መርጦ አጋባው። ኤር ግን አባቱ የአሕዛብን ሴት ስላመጣለት የንዴት እረመጥ በውስጡ ተፋፋመ ስለሆነም የሥጋ ተራክቦን ለመፈጸም አልወደደም ትዕቢት የማይስማማው እግዚአብሔር ትዕቢቱን አይቶ ቀሰፈው ሞተም።

በኦሪት ሕግ ወንድም ሲሞት ታናሽ ወንድም የወንድሙን ሚስት ተቀብሎ ያገባ ስለነበር ታናሽ ወንድሙ አውናን ትዕማርን ገንዘቡ አደረጋት። አውናንም በልቡ ከዚች ሴት ዘር ባስቀር በወንድሜ እንጂ በእኔ ስም አይጠራም ምን እጠቀማለሁ? ብሎ ተራክቦን በሚፈጽምበት ጊዜ ዘሩን ከማህፀንዋ በአፍአ አፈሰሰው። እግዚአብሔር ዘሩን ከጥቅም ውጭ በማድረጉ አንድም ምቀኝነቱን በመጥላቱ እዚያው ቀሰፈው የሞት ሰለባ ሆነ።

ሁለቱንም ልጆች በአንድ ጊዜ ያጣው ይሁዳ የሐዘን ቀንበር በላዩ ላይ ወደቀበት። ስለሆነም የወለተ ራጉኤልን ልጅ "እስማንድሮስ" የተባለ ጋኔን ከጭንዋ ላይ ቢያድርባት ሰባቱን ባሎቹን እንደጨረሰባት ይህችም ልጅ ልጆቼን ልትጨርስብኝ አይደለምን? ብሎ በልቡ አሰበ። በሀሳብ አልቆመም ከታናሽ ልጁ ከሴሎም ጋር እንዳያገባት በፈሊጥ ሊያሰናብታት ከልቡ መላን አፈለቀ። ትንሹ ልጄ እስኪያድግ ድረስ ወደቤተሰቦችሽ ሂጂ እያለ አደን እያለ አላደገም በማለቱ ልቧ በሀዘን እየቀለጠ ወደ ቤቷ ሄደች።

ትዕማር ዝሙት ቀረብኝ ብላ አልነበረም ያዘነችው። እመቤታችንና ጌታችን ከቤተ ይሁዳ እንደሚወለዱ በትንቢተ ነቢያት የተነገረውን ቃል ትሰማ ስለነበር ከባለተስፋ ቤት ወጣሁ ምነው ከቤተ ይሁዳ ጋር በዘር ተሳስሬ እመቤታችን፣ ጌታም ከእኔ ወገን ቢወለዱ የሚል በጎ ምኞቷ

መክና የቀረ መስሎ ስለታያት እንጂ።

በዚያን ወራት ይሁዳ ሚስቱ ሴዋ ዓለሙን በሞት ተሰናበተችው። ሀዘን የተደራረበበት ይሁዳ መዋዕለ ሀዘኑን ከፈጸመ በኋላ ቴምናታ ወደምትባል ሀገር በጎቹን ሊሸልት ወጣ። ወዳጆቿ መጥተው ለትዕማር እንዲህ አሏት "ናሁ ይሁዳ ሐሙኪ የአርግ ውስተ ቴምናታ ከመይቅርጽ አባግኢሁ" እነሆ አማትሽ ይሁዳ በግ ሊሸልት ወደ ተምና ይወጣል። ቢሏት ከሴት መላ አይጣፋምና እንዳታለለኝ ላታለው ብላ የዘማውያንን ልብስ ለብሳ፣ ሸንጥላ አስጥላ ድንኳን አስተክላ ከተመሳቀለ መንገድ ዳር በኤናይም ደጅ ቆመች እርሱም ዐይኖቹን ወደርሷ ቢያማትር ትዕማር መሆኗን አላወቀምና በሐፀ ዝሙት ተነደፈ። ሚስቱ ሞታለችና ወደአንቺ ልግባ አላት "ምንተ ትሁበኒ አሰበ ደነስየ" ወደእኔ ብትገባ ምን ትሰጠኛለህ አለችው። ብልህ ሴት ነች የኋላውን ገጠመኝ አስባ ነው። እንዳይከዳት መያዝ ጠየቀችው። እርሱም "እፌኑ ለኪ አሐደ ማሐስዓ" የፍየል ጠቦት ከመንጋዬ እሰድልሻለሁ አላት። እርሷም እስክትሰድልኝ መያዣ ስጠኝ አለችው ምን መያዣ ልስጥሽ አላት፣ ቀለበትህን፣ ዘንግህን፣ ኮፍያህን ስጠኝ አለችው። ሳያቅማማ ሰጣት ያኔውኑ በግብር ደረሰባት ከአይሁድ ወገን የምትፈልገውን ዘር ካገኘች በኋላ ልብሷን ለውጣ በቤቷ ተቀመጠች። እርሱም ሄደ።

በቤቱ ኤራስ የሚባል አዶሎማዊ ሰው ያገለግለው ስለነበር ሂድና ለዚያች ለዘማ ሴት ይህን የበግ ጠቦት ስጣትና እርሷጋር ያለኝን መያዣ ተቀብለህ ና ብሎ አሸከሞ ላከው ልብሰ ዘማ ለብሳ ስለነበር ዘማ መሰለችው። እርሷስ ለጥበብ ነበር እንጂ ዘማ አይደለችም። ኤራስ ጠቦቱን ተሸክሞ ቢመላለስ ቤቷን አጣው "አይቴ ቤታ ለዘማ" የዘማይቷ ቤት የት ነው? እያለ ቢጠይቅ እኛስ በሀገራችን ዘማ የለብንም ብለው የመንደሩ ሰዎች አሰናበቱት ጠቦቱን ይዞ ተመለሰ።

እንዳላገኛት ለይሁዳ ቢነገረው ካላገኘሃት ገንዘባችን ይመለስ ደግሞ የያዕቆብ ልጆች ዛሬ በትዕቢት ተወጠሩ። ብለው ብለው የዘማያንን ቤት ይፈልጉ ጀመር ብለው ይዘባበቱብናል ብሎ በጉን ተቀበለው።

ከሦስት ወር በኋላ ወዳጆቹ መጥተው የትዕማርን ነገር ነገሩት ለልጆችህ የዳርካት ትዕማር በዝሙት ጸነሰች አሉት። ይሁዳ የገዛ ሥራውን

ዘንግቶ በንዴት ተዋጠ እሳት ጎርሶ እሳት ለብሶ ተነሳ። ሰይጣን ሰዎች ላይ ሲሰለጥንባቸው የሠሩትን ኃጢያት እንዳያስቡትና እንዳይጸጸቱበት ከልባቸው ይሰርቃል። ሁሌም ሰይጣን አመንዝራን ሰው በሌላው ላይ ፈራጅ ያደርገዋል። በዚህ ውስጥ እስቲ ቆም ብለን የእኛን ሕይወት እንየው?

ይሁዳ በዚያን ዘመን አሕዛብን በሚገዛበት የስልጣን ኮርቻ ላይ ስለተቀመጠ በትዕማር ላይ የሞት አዋጅ አወጀባት በድንጋይ ተወግራ በእሳት ተቃጥላ ከእንጭንሷ ትሙት ብሎ ትዕዛዝ አስተላለፈ። ትዕማር የሞቷን ሰዓት በምትጠብቅበት በዚያን ቀን ተጠርታ በይሁዳ ፊት ቀረበች እንዲህም አለችው "ዘ ህልቀት ዘመኑ" ይህ ቀለበት የማነው? "ዘኩፌት ዘመኑ" ይህ ኮፍያ የማነው? "ዘሕለት ዘመኑ" ይህ በትር የማነው? ብላ ቃሉን እንዳያጥፍ የሰጣትን መያዣ መልሳ አሳየችው ያኔ ወደልቡ ተመለሰ ጥበቡን እንደበለጠችው አውቆ "ጸድቀት እምኔየ ትዕማር" ከእኔ ይልቅ ትዕማር ጸደቀች አለ። ትዕማር የመንታ ልጆች እናት ሆነች አስቀድማ ስትወልድ የበኩር ልጇን ቀይ ሀር እጣቱ ላይ እንድታስርለት ለአዋላጅዋ ነገረቻት። እርሱም ዛራ የሚባለው ነበር። ይሁን እንጂ ቀይ ሐሩን ስቦ ሁለተኛው ልጅ ፋሬስ አስቀድሞ ተወለደ ዘፍ 38÷30።

<u>ይህ ሁሉ ምሳሌ ነው</u> ይሁዳ የእግዚአብሔር አብ፣ መልዕክተኛው ኤራስ የቅዱስ ገብርኤል፣ በጉ የጌታችን የእየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው። የዓለምን ኃጢአት ያስወገደ እውነተኛ በግ እርሱ ነውና። ሕልቀት (ቀለበት) የሃይማኖት። ኮፍያ የአክሊለ ሶክ። በትር የመስቀል ምሳሌ ይህን መያዣ ብታደርግ ትዕማር ከሞት እንዳዳነች ዛሬም ሃይማኖት፣ መስቀልን ይዘው አክሊለ ሶኩን እያሰቡ ለሚኖሩ ሁሉ ከሞተ ነፍስ ለመዳናቸውም ምሳሌ ነው።

የትዕማር ልጆች ፋሬስ የኦሪት፣ ዛራ የወንጌል ምሳሌ ናቸው። ዛራ አስቀድሞ በመውጣት ታይቶ እንደጠለቀ ወንጌልም በመልከ ጼዴቅ ታይታ ጠፍታለች። ፋሬስ ዛራን ስቦ እርሱ እንደተገለጠ በመካከል ኦሪት ተገልጣለች። ዛራ ኋላ እንደተወለደ ወንጌልም ከኦሪት ኋላ ተሠርታለች።

ትዕማር የቤተ አይሁድ ምሳሌ ነች ትዕማር መያዣን በተስፋ ያዘች እንጂ በጉን አልተቀበለችም። ቤተ አይሁዳም የጌታችንን ተስፋ ሰሙ እንጂ አምነው አልተቀበሉትም። (አልተጠቀሙበትም) <u>አንድም</u>

ትዕግር የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። ትዕግር ልጆችን ከአባት ከይሁዳ እንጂ ከልጆች ከእነአውናን አላገኘችም። ቤተክርስቲያንም ምዕመናንን ከአባት ከኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ከልጆች ነብያት፣ ከልጆች ካህናት አላገኘችም። ክርስቲያኖች የመገናኛ ምንጫችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

<u>አንድም</u> ትዕግር ከልጆችም ከአባትም ዘርን ለመቀበል እንዳልተጸየፈች ቤተክርስቲያንም ከአማኒውም፣ ከኢአማኒውም፣ ከህዝብም ከአሕዛብም፣ ከግዙርም ከቆላፋውም፣ ደሃ፣ ሀብታም ልጅ አዋቂ ሳትል አምነው የተመለሱላትን ሁሉ ሳትጸየፍ ትቀበላቸዋለች። ቤተክርስቲያን ሁሉን በእኩል ዓይን የምታይ ከእናትነት ጡቷ የሚፈልቀውን የፀጋ ምንጭ ለሁሉ የምታጠጣ የእውነት እናት ነች።

ትዕግር ለዘመናት ትናፍቀው የነበረው የልቧን መሻት አግኝታ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ የዘርሀረግ ተወልዶላት የጌታ ቅድመአያት ተብላ በዘር ሐረግ ለመቆጠር በቅታለች ማቴ 1÷3

6. <u>የአብርሃም ድንኳን</u>

ሰዓቱ ስድስት ሰዓት /ቀትር/ ነው። አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ እንግዶች ቀርተውበታልና ዓይኑን እያማተረ ይጠብቃል። ዓይኑን ቢያነሳ ሥላሴ በሦስት ሰዎች አምሳል ወደ እርሱ መጡ። ልቡን ያስጨነቀው የእንግዶች ናፍቆት ተለውጦ በደስታ ተሞላ የሚገባውን መስተንግዶ አደረገ። መንሳትም መስጠትም የራሱ የሆነ እግዚአብሔር ማጣትን ከእርሱ ሊያርቅለት ወደደ "የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሣራ ልጅን ትወልድልሃለች" አለው አብርሃምና ሣራ ለዘመናት የተያዙበት የልጅ ናፍቆት ተለውጦ ጥማቸው ተወገደ። የሣራ ምክነት ለመለመ በአብርሃም ድንኳንም በረከት መላ። ዘፍ 18÷1-15

የአብርሃም ድንኳን የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት አብርሃምና ሣራ በዚች ድንኳን የልባቸውን መሻት (ይስሐቅን) እንዳገኙ ምእመናንም በቤተክርስቲያን ተገኝተው ቢለምኑ የልባቸውን መሻት ያገኛሉ። ማቴ 7÷7 ሐሴትን ተመልተው ይመለሳሉ።

የሥላሴ ክብር በአብርሃም ድንኳን እንደተገለጠ ቤተክርስቲያንም ለእግዚአብሔር የክብሩ መገለጫ የፀጋው ግምጃ ቤት ናት። ፍጻሜው ግን የእግዚአብሔር በስድስት ሰዓት ወደ አብርሃም ድምኳን መግባት አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ተፈጸሞ በስድስተኛው ሺህ ዘመን ላይ የአብርሃም ወገን ከሆነችው ከአማናዊቷ ድንኳን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ማሕጸን ጌታችን መድኅን ዓለም ክርስቶስ ለማደሩ ምሳሌ ነው።

7. <u>ምሥራቅ</u>

ቤተ ክርስቲያን ምሥራቃዊት ነች የተመሰረተችውም በስተምሥራቅ ኢየሩሳሌም ነው። ዛሬ ወደ ቤተክርስቲያን ስንመለከት ክርስቶስ የተፀነሰባትን ኢየሩሳሌምን እናስባለን አሁንም ቤተክርስቲያን ስንመለከት ሕሊናችን በሃሳብ ሠረገላ ተጭኖ በኢየሩሳሌም ቀራንዮ የተደረገልንን አባታዊ ፍቅር ያስባል። ይህ ብቻ አይደለም። የምንጠገንበት የወንጌል አዝመራ መብቀል የጀመረው ኢየሩሳሌም ነውና አምሳለ ኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያንን ስናይ የወንጌልን መስፋፋት እናስብበታለን።

8. <u>ደብረ ሲና</u>

ሙሴ ከፈርኦን ቤተ መንግሥት መጥቶ ወደ ምድያም ተሰዶ ነበር። ምድያም ጥንት ሰሜናዊት የኢትዮጵያ ግዛት ነች። ሙሴ የኢትዮጵያን ማንነት ጠንቅቆ ያውቃል በስደት ኖሮባታልና። ሀገራችንን ኢትዮጵያ ሀገረ ቅዱሰን የምንላት ያለምክንያት አይደለም። የታሪክ ማኅደሩን ያጨናነቀው የቅዱሳን መጠጊያ መሆኗን ስለሚያበስረን ነው። እንደውም ሙሴ ኢተዮጵያ ውስጥ መኖር ብቻ አይደለም ኢትዮጵያዊት ሴት እንዳገባ መጽሐፍ ቅዱሳችን ይነግረናል። ዘኍ 12÷1 በዚህ ስደት ውስጥ ሆኖ ሙሴ በሌላ የፈተና አጣብቂኝ ውስጥ ገብቷል። አኀቱ ዮቶር አስማርቶ ሳለ የእግዚአብሔር ድምፅ ወደ እርሱ መጣ የእግዚአብሔር መልአክ በእሳት ነበልባል በእሾህ ቁጥቋጦ መካከል ታየው። እነሆ በቁጥቋጦው እሳት ሲነድ ቁጥቋጦውም ሳይቃጠል አየ። ዘፀ 3÷1-5

ሙሴም ቁጥቋጦው ስለምን አልተቃጠለም? ይህን ታላቅ ራዕይ ልይ አለ። እግዚአብሔርም ይመለከት ዘንድ እንዲመጣ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር ከቁጥቋጦው ውስጥ እርሱን ሙሴ ሙሴ ሆይ ሲል ጠራው። እርሱም እነሆኝ አለ ወደዚህ አትቅረብ። አንተ የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ነችና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው። ይህ ምሳሌ ነው። ሐመልማል የትስብዕት ነበልባል የመለኮት ምሳሌ ነው። ነበልባሉ ሐመልማሉን ሐመልማሉ ነበልባሉን ሳያጠፋው ተዋህደው ማየቱ መለኮት ትስብዕትን ሳይመጠው ትሰብዕት መለኮትን ሳያጠፋው በተዋህዶ ከሁለት ግብር አንድ ግብር ለመሆናቸው ምሳሌ ነው። ደብረ ሲና የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት ሙሴም አንተ የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ። ማለቱ ለጊዜው ከዮቶር የተማርከውን "ፋል" የሚባል የጥንቁልና ትምህርት ከእግረ ልቡናህ አውልቀህ (አውጥተህ) ና ሲለው ነው። ፍጻሜው ግን ለእኛም የተላለፈ ሥርዓት ነው። በደብረ ሲና (ቤተክርስቲያን) ምስጢረ ሥጋዌ የተዋህዶ ነገር ይነገራልና የትስብዕትና የመለኮት ነገር ከሚነገርባት፣ ሥጋ ወደሙ ከሚፈተትባት ቤተ ክርስቲያን ከነጫማችን እንዳንገባ ጌታችን ሥርዓት ሲሠራልን ነው። የቆምክባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናት አለ። አዎ ቤተ ክርስቲያን በበግና በፍየል ደም ሳይሆን በክርስቶስ ደም የተቀደሰች ሥፍራ ነች።

በእስራኤላውያን ልማድ ማንም ሰው ሲሸጥ፣ ሲለውጥ ነገሩን ለማጽናትና ቃል ለመገባባት ጫማ አውልቆ ለባልንጀራው ይሰጠው ነበር። ሩት 4÷7 የዚህ ሥርዓት የምሳሌው ፍጻሜ ቀስቱን የሚያንጣጥረው ወደእስራኤል ዘነፍስ ወደ ሐዲስ ኪዳን ክርስያኖች ነው። ዛሬ የጸጋው ግምጃ ቤት ወደሆነችው ቤተክርስቲያን ስንገባ ጫማችንን ስናወልቅ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል እየተግባባን ነው። ጫማ የኃጢአት ምሳሌ ነው አውልቀን መግባታችን በልባችን የተጫማነውን ስክ ኃጢአት ከቤትህ አውልቀናል ደግሞ የኃጢአትን ጫማ በልባችን አንሰካውም ብለን ቃል እየተገባባን ነው። ታዲያ ቃል ኪዳኑን እየተጠቀምንበት ነው ወይስ እያላገጥንበት? ከጠላነው ኃጢአት ጋር መልሰን በፍቅር አልተሳሰርንም?።

9. <u>ቤትኤል</u>

ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነስቶ ወደ ካራን ጉዞውን አቀና። ብርሃን ለጨለማው ስፍራውን የሚልቅበት ሰዓት ስለደረሰ ፀሐይ ጠለቀች። የጨለማውን ጊዜ በእንቅልፉ ለመሸኘት ያዕቆብ ድንጋይ ተንተርሶ በሉዛ ምድር ተኛ። ህልም አለመ። የወርቅ መሰላል ከምድር እስከ ሰማይ ተተከላ፣ መላእክት ሲወጡና ሲወርዱባት፣ ዙፋን በላይዋ ተዘርግቶ፣ ንጉሥ በላይዋ ተቀምጦባታ አየ። የእግዚአብሔርንም ድምጽ ሰማ የሰማዩ ኅህ ሲቀድ ከእንቅልፉ ነቃ። ተነስቶም ድንጋዩን ሐውልት አድርጎ ተከለው። ዘይትም አፈሰሰበት በውኑ እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ነው እኔ አላወቅሁም ነበር አለ። ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል "ዛቲ ይእቲ ኆኆታ ለሰማይ ዝየ ይትሐነጽ ቤተ እግዚአብሔር" ይህች የሰማይ ደጃ ናት። በዚህ ቤተእግዚአብሔር የታነጻል። ብሎ በተሰጠው ሀብተ ትንቢት ስለቤተክርስቲያን ተናገረ ዘፍ 28÷10-22 ይህ ምሳሌ ነው። የወርቅ መሰላል የእመቤታችን፤ ወርቅ መሆኑ የንጽህናም የቅድስናዋ ምሳሌ ነው። ደንጊያ የትንቢተ ነበያት ምሳሌ እመቤታችን በትንቢተ ነብያት ተገኝታለችና። መላእክት በመሰላሏ መውጣት መወረዳቸው እመቤታችን ጌታን ከወለደች በኋላ መላእክት ለተልዕኮ መፋጠናቸው ምሳሌ ነው። ብሉይ ኪዳን ሰውና መላእክት የተጣሉበት ዘመን ስለነበር እምብዛም አይፋጠኑም ነበር። ዙፋን የማሕጸኗ ምሳሌ ነው። ማሕጸኗን ዙፋን አድርጎ ንጉሠ ነገሥት ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን አድሮባታልና።

ያዕቆብ የካህን ዘይት የሜሮን ድንጋይ የአሕዝብ ምሳሌ ነው። ስለምን ቢሉ ድንጋይ ከባድ ነው። አሕዛብም ክቡዳን አይምሮ ናቸውና። በቀላሉ የእግዚአብሔርን ቃል አይቀበሉም። ነው። አሕዛብም ለእምነት ቀዝዛዛ ናቸው። <u>አንድም</u> ድንጋይ ቀዝቃዛ የላቸውም ስለሆነም በመጽሐፍ ቅዱስ ድንጋይ በአሕዛብ ተመስሏል። ሙቀት መንፈስ ቅዱስ 3÷9 ያዕቆብ የቦታውን ስም <u>ቤትኤል</u> አለው። ትርጓሜውም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው። በእውነትም የቦታውን ክብር አውቆ ፈራ የእግዚአብሔር ቤት ያላስፈራ ማን ያስፈራል?

ይህም የሰማይ ደጅ ነው አለ። ቤትኤል /ቤተክርስቲያን/ የሰማይ ደጅ ናት ከውስጧ የወጡ ከመንግሥት እግዚአብሔር ለመውጣታቸው ምሳሌ ነው። የሰማይ ደጅ በሆነችው ቤተክርስቲያን ከሰማያዊ ሥራ ውጪ

ሥጋዊ ግብር አይፈጸምባትም።

ያዕቆብ የመታሰቢያ ድንጊያ አቁሞባት ሄዷል። ፍጻሜው በዚህ ሥፍራ ቤተክርስቲያን እንደሚታነጽ አውቆ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በፊሊጲስዮስ ከሦስት ድንጋይ በእናቱ በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የመጀመሪያዋን ቤተክርስቲያን ያነጸው በዚህ ስፍራ ነው። (ሰኔ 21 የሚከበረው የእመቤታችን የድንግል ማርያም በዓል)

<u>ለቤትኤል የሚገባው</u> ዘፍ 35÷1 ያዕቆብ በሰኬም ሲኖር ብዙ ሃብት ከማጠራቀሙ ባሻገር ከእንግዶች አማልክት ጋር ተለማመደ። “ብዙ ጊዜ ሰው ውሎውን ይመስላል” በአሕዛብ መንደር ውስጥ ከሚኖሩት ልጆች መካከል ሴት ልጁ ዲና የሴኬማውያንን ጭፈራ ለማየት ተጣደፈች ሄዳም ጭፈራውን መሰለችው። ዓለም ለፍቅሯ የሚጣደፉላትን አቅርባ ኋላ መርገጧ አይቀሬ ነው። የኤሞር ልጅ ሴኬም በያዕቆብም ልጅ በዲና ፍቅር ተነደፈ ልቧንም ደስ የሚያሰኛትን ቃላት በውስጧ ሞላ። ኋላም ከድንግልና ክብሯ አሰነወራት። የዓለም ማባበል ፍጻሜው ከዚህ አያልፍም። ይህንን የሰሙ የያዕቆብ ልጆች ሌዊና ስምዖን የእህታቸው ንጽሕና መደፈር ፋታ ስላልሰጣቸው ዘገር ነጥቀው፣ ሰይፍ ታጥቀው ወደ ኤሞር ልጅ ወደሴኬም አቀኑ አንገቱንም በሰይፍ ቀሉት። የኣመንዝራ ትውልድ ዕጣው ይህ ነው። ከተማውን ሁሉ ዘረፉ፣ ሰውንም አራቆቱ ለአባቱንና ለወንድሞቹም የሞትን ፅዋ ጋቷቸው።

ወዳጆቹን ከሞት ዓለም ውስጥ መለየት የሚያውቅበት ጌታ ያዕቆብን ተነሥተህ ወደ ቤትኤል ውጣ አለው። የእግዚአብሔር ሰዎች ለእግዚአብሔር ቃል አያቅማሙም። እርሱም ቤተሰቡን እንዲህ አለ “እንግዶች አማልእክትን ከፊታችሁ አስወገዱ ንጹሐንም ሁኑ፣ ልብሳችሁንም ለወጡ ተነሥተን ወደ ቤትኤል እንውጣ። ልጆቹም በእጆቻቸው ያሉትን እንግዶች አማልክትና ጌጣጌጦቻቸውን ሰጡት እርሱም ከሴኬም አጠገብ ካለችው የአድባር ዛፍ በታች ቀበራቸው።”

ያዕቆብ የካህን፣ ሴኬማውያን የአጋንንት፣ ጌጣጌጥና አማልክት የኃጢያት ምሳሌ ናቸው። ወደ ቤትኤል /ቤተክርስቲያን/ ስናመራ ጉዞአችን ይህን መምሰል አለበት። የኃጢአትን ሸክም ሳያራግፉ ወደ ቤትኤል መንዝ ብቻውን ለውጥ አያመጣም። የኃጢያትን ጌጣጌጥ በኑዛዜ

በካህናት ጆሮ አድርሰን እዚያው ሴኬም ቀብረን ልንመጣ ይገባናል። ሕይወታችን ለውጥ አልባ የሆነው የሰኬምን ወደ ቤትኤል ይዘን ስለምንገባ ነው። ሴኬም የዓለም ምሳሌ ነውና። የሴኬምን ለሴክም የቤትኤልን ለቤትኤል ልንተው ይገባል። ሴኬማዊ ኑሮን ስንሰናበት ንብረቱን ይዘን ሳይሆን እንግዶች አማልእክትን በንስሐ አስወግደን ነው። ይህ ካልሆነ ቤትኤል እንኳን ብንገባ የሴኬም ፍቅር በልባችን ስለተሰነቀ በክርስትና ሕይወት ያለን እድገት ይቀጭጫል። ነገር ግን ለቤትኤል የሚገባው ኑሮ የዓለምን ሕይወት ለውጦ ንጹህ የቅድስና ልብስ ሕይወት ለብሶ መኖር ነው። ኤፌ 14÷15 ቆረ 5÷6-7

10. <u>ጌልጌላ</u>

የእስራኤል ልጆች ከግብጽ የባርነት ኑሮ ወጥተው ግዝረት የፈጸሙባት ስፍራ ጌልጌላ ናት። ኢያ 5÷2-9 እስራኤላዊያን ወደምድረ ርስት ከመግባታቸው በፊት አላስፈላጊ የሆነ /ሸለፈታቸውን/ ማስወገድ ነበረባቸውና በኢያሱ ምክንያት ይህን ስርዓት በጌልጌላ ፈጽመዋል። ጌልጌላ ማለት አበሳ ማስወገጃ ቦታ ማለት ነው። የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። በብሉይ ኪዳን ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነውና ዛሬ ጥምቀትን በጌልጌላ ቤተክርስቲያን እንፈጽማለን። ኢያሱ የካህናት ምሳሌ ነው። ይህም ጥምቀት በካህናት አማካኝነት የሚፈጸምልን ምስጢር እንደሆነ ያጠይቃል።

ዛሬ የእኛ ጌልጌላ /ቤተክርስቲያን/ ለእኛ ለእስራኤል ዘነፍስ የሐዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ኃጢአት አበሳችን ሁሉ የሚወገድባት ቅድስት ሥፍራ ነች። በኃጢያት የተዳደፉ ንስሐ ገብተው አበሳቸው የሚርቅላቸው ወደ ቤተክርስቲያን ሲቀርቡ ነው።

ስለሆነም ዛሬ ከሕይወታችን ጋር ተጸናውተን ያለውን አላስፈላጊ የኃጢአት ሸለፈት በቤተክትስቲያን ተገኝተን በቃሉ ሰይፍነት ቆርጠን ልናስወግደው ይገባል።

በሌላም በኩም እስራኤላዊያን ዮርዳኖስን ከተሻገሩ በኋላ ከአስራ ሁለት ድንጋዮች የመታሰቢያ ሐውልት ያቆሙት በዚሁ በጌልጌላ ነበር።

ኢያ 4÷19-20 ይህን ሐውልት ያቆሙት ከእግዚአብሔት ጋር ያላቸውን ፍቅር ለማጽናት ያደረጉት የቃልኪዳን መግለጫ ነበር። ዛሬም በጌልጌላ ከምትመለሰው ቤተክርስቲያን ተሰብስበን ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን ፍቅር በምስጋና፣ በጸሎት፣ በዕንባ፣ በውዳሴ በዝማሬ፣ ንስሐ በመግባት፣ ሥጋ ወደሙን በመቀበል ልንገልጽ ያስፈልጋል። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር አበሳችን ሁሉ በሚርቅባት በቅድስት ቤተክርስቲያን እንዲያጸናን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን። አሜን።

11. <u>ቀርሜሎስ</u>

የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወቱ የመላ ነብዩ ኤልያስ በዘመኑ ከነበረው ከንጉሡ ከአክአብ፣ ከንግሥቲቱ ከኤልዛቤል ጀምሮ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ክብር በጣዖት ፍቅር ለውጦ ሳለ ነብዩ ለአምላኩ በመቅናት የእውነት ጌታ ማንነቱን እንዲገልጽ በቀናኢነት ወደ እግዚአብሔር ለመነ። ለእግዚአብሔር ክብር ግድ ከሌለው ህብረተሰብ ውስጥ ለእግዚአብሔር ቀናኢ ሆኖ መገኘት ከምንም በላይ መመረጥ ነው።

ኤልያስ ሰዎች ለእግዚአብሔር ጌትነት ጀርባቸውን በሰጡት በዚያ ዘመን እርሱ ግን የአምላኩን ክብር ከፍ አድርጎ በማውለብለብ ለዓለም ለማሳየት ቆርጦ ተነሳ። ንጉሡን ሳይፈራ ለአክአብና ለህዝቡ በቀርሜሎስ ተራራ ሁለቱም መስዋዕት እንዲሰው፣ መስዋዕቱን የተቀበለ እርሱ የእውነት አምላክ እንዲባል መልእክት ላከበት "ወይ በዓሊም ወይ እግዚአብሔር" አክአብም 450 የጣኦት ካህናት 400 የማምለኪያ አፀድን የሐሰት ነብያቱን ይዞ ቀርሜሎስ ተራራ ላይ ወጣ። ኤልያስም እግዚአብሔርን መጠጊያ አድርጎ ወደ ቀርሜሎስ አቀና።

በመጀመሪያ አክአብ የራሱን መስዋዕት በጣኦቱ ስም አቀረበ። ወደ በዓሊም ጩኸቱን አበዛ፣ ፊቱን ቧጨረ፣ ደረቱን ደቃ፣ የሐሰት ነብያቱም ከሀፍረት ለማምለጥ ዕንባቸውን እረጩ፣ ደማቸው እስኪፈስ ድረስ ሰውነታቸውን በካራና በቀጭኔ ይመቱ ጀመር። ነገር ግን ጣዖት ከንቱ የሰው የእጅ ሥራ በመሆኑ መልስ ሊሰጣቸው አልቻለም። ድምጹ የውኃ ሽታ ሆኖ ቀረ። እዚህ ላይ ሳንገልጽ የማናልፈው ነገር አለ። ሰይጣን በጣዖት ላይ የእውነት በማስመሰል የሐሰት ተአምራቱን የሚያሳይበት ጊዜ አለ። ነገር ግን ይህንን ማድረግ ሲችል በኤልያስ ላይ ያደረ መንፈስ ቅዱስ

ግን ሊያስቀርበው አልቻለምና የጣዖት ባዶነት በግልጽ ታየ።

ኤልያስ የእነ አክአንብ ደማቸውን እያፈሰሱ ወደ ጣዖት መጮኽ አስገርሞት ይዘብትባቸው ጀመር። "ምናልባት አምላካችሁ ሀሳብ ይዞት ይሆናል ቀስቅሱት ወይም መንገድ ሄዶአል ወይንም ተኝቶ ነው የማይሰማችሁ" ይላቸው ነበር። በዚህ ጊዜ ውስጣቸው በሀዘን ቀለጠ ለአክአብ የተሰጠው የመሰዊያ ጊዜ አለቀ።

ሰዓት ስፍራዋን ለኤልያስ ለቀቀች እርሱም ፈርሶ የነበረውን የእግዚአብሔርን መሰዊያ ሰራ። አስራ ሁለት ድንጋዮችን ወስዶ ድንጋዩም ቆፍሮ እንጨት እረበረበ አሥራ ሁለት ጋን ውሃ እንዲደፋበት አዘዘ። በዚያም ወይፈኑን መስዋዕት አድርጎ አቀረበ። ዛሬ እኛ የቅዱሳንን ስም እየጠራን እግዚአብሔርን እንደምንማጸን እርሱም የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብን ስም እየጠራ ተማጸነ። ወዲያውም የእግዚአብሔር እሳት ከሰማይ ወረደች የሚቃጠለውን መስዋዕት እንጨቱንም ድንጋዩንም አፈሩንም በላች በጉድጓድ ውስጥ ያለውን ውኃ ላሰች /ተቀበለች/ የኤልያስ ቅድስናው፣ የእግዚአብሔር ጌትነቱ፣ የአክአብና የሐሰት ነብያቱ ከንቱ አምልኮት፣ የተመኩበት የበዓሊም ባዶነት በቀርሜሎስ ተራራ ተገለጠ። 1ኛ ነገ 18÷7-40

<u>ምሳሌነቱ</u> እንጨቱ የመስቀል፣ አሥራ ሁለቱ ጋኖች የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት፣ ውኃው በአሥራ ሁለቱ ጋን መሞላቱ ጌታችን በአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ልብ ውስጥ ቃሉን የመሙላቱ፣ የተሰዋው ወይፈን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ፣ ቀርሜሎስ የቀራንዮ ምሳሌ ነው። አክአብ የሰይጣን፣ የሐሰት ነብያቱ የሠራዊተ አጋንንት ምሳሌ ናቸው። አክአብ በቀርሜሎስ በተሰዋ ጊዜ አክአብና ነብያቱ እንደፈሩ ጌታችን በቀራኒዮ በተሰዋ ጊዜ ሰይጣን ከነሠራዊቱ አፍሮና ተንኮታኩቶ ወድቋል። የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ የባህርይ አምላክነት ተገልጧል።

<u>የምሳሌ ምሳሌ</u> ቀሜሎስ የቤተክርስቲያን፣ አክአብ የአርዮስ፣ የሐሰት ነብያቱ የመናፍቃን፣ ኤልያስ የሊቅ ምሳሌ ነው። ኤልያስ አክአብንና የሐሰት ነብያቱን በቀርሜሎስ እንዳሳፈራቸው /ድል እንደነሳቸው/ ሊቅ አትናቴዎስ በቤተክርስቲያን ጉባኤ የተሰበሰቡ አርዮስንና ተከታዮቹን በትምህርቱ ድል ነስቶ ለማሳፈሩ ምሳሌ ነው።

ኤልያስ አክአብን በጣኦቱ እንዳሳፈረው አትናቴዎስም አርዮስን በትምህርቱ አሳፍሮታል።

የእኛ ቀርሜሎስ /ቤተክርስቲያን/ እውነተኛ /የቅዱሳን/ ክብር ይንጸባረቅባታል። ሐሰተኞች መናፍቃን ግን ቢሰገስጉ አፍረው ይመለሱባታል።

ቀርሜሎስ /ቤተክርስቲያን/ እውነተኛ ክርስቲያኖች የሚያቀርቡት የመዝሙር፣ የጸሎት የሽብሸባ፣ የምዕዋት... ወዘተ መስዋዕት ሁሉ ፈጥኖ የሚያርግባት ቅዱስ ስፍራ ነች።

<u>እስከመቼ ድረስ በሁለት ሀሳብ ታነክሳላችሁ፤</u> ይህ ኤልያስ ለአክአብና ለሐሰት ነብያት የተናገረው ቃል ነው። እስቲ በዚህ ቃል እራሳችንን እንምከርበት። እኛስ እስከቼ በሁለት ሃሳብ እናነክሳለን? ዛሬ ዓለሙን ያጨናነቅነው በሁለት ሀሳብ የምናነክስ ሰዎች ነን። ብርሃንን ወይ ጨለማ፣ ህይወትን ወይ ሞትን፣ ዓለምን ወይ እግዚአብሔርን የምናመልከውን ዛሬ እንምረጥ። ኢያ 24÷15

ዳሩ እኛ የምንመርጥ ሰዎች ሳንሆን ብርሃንን ከጨለማ ጋር አዋህደን እንኑር የምንል ሰዎች ነን። መንፈሳዊውን ከሥጋዊው ጋር አቀላቅለን ለመኖር እንፈልጋለን። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ህይወታችን የሚመሰቃቀልብን። ግን ምስቅልቅል ሕይወት ተሸክሞ <u>እስከመቼ</u>! እንዲህ ሆነን ከእነ ኤልያስ ጋር ቀርሜሎስ ብንወጣ ከህፍት በቀር ይዘን የምንመለሰው ፋይዳ አይኖርምና እናስብበት።

12. <u>የኤልሳዕ ሰገነት</u>

የእግዚአብሔር ሰው ኤልያስ ወደ ሱነም ሲያልፍ በስፍራው እግዚአብሔርንና ቅዱሳኑን በማክበር የከበረች ሱናማዊት ሴት ነብዩ ወደ ቤቷ ገብቶ እንጀራ እንዲበላ ግድ አለችው። የእግዚአብሔርን ሰዎች ብንቀበል ክብራቸውን እንቀበላለን። ማቴ 10÷40-43 ይህች ሴት የእግዚአብሔርን ሰው ኤልሳዕን እንጀራ በማብላት ብቻ አልረካችም በግቢዋ ውስጥ ሰገነት ልታቆምለት በውስጡም አልጋ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ መቅረዝና የመሳሰሉትን መገልገያ ልታሟላለት ከባሏ ጋር

ተማከረች። ምክራቸውም ጸና።

ሴቲቱ የነበረባትን ውስጣዊ የልጅ ችግር ያወቀ ኤልሳዕ በተማሪው በግያዝ አስጠርቷት ቃል ተናገራት “ይህን ሁሉ ሀሳብ አስብሽልኝ አሁንስ ምን ላድርግልሽ? ለንጉሥ ወይስ ለሠራዊት አለቃ ልንገርልሽ”አላት እርሷም “እኔ በወገኔ መካከል ተቀምጫለሁ” ስትል መለሰችለት ኤልሳዕም “በሚመጣው ዓመት በዚህ ወራት ወንድ ልጅ ትታቀፊያለሽ” አለ። ሴቲቱም ከውስጧ በሚፈነቅል የደስታ ስሜት “ጌታዬ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ ባርያህን እንዳትዋሻት እለምንሃለሁ” አለችው። እርሷም ጸነሰች ኤልሳዕ በተናገረ በአመቱ ወንድ ልጅ ታቀፈች ሕጻኑም አደገ። ጤንነትና በሽታ ለሰው ልጅ ህይወት ተፈራራቂ ክስተቶች ናቸውና ልጇ በበሽታ ጠወለገ ህመሙን መቆጣጠር ያልቻለ እንቡጥ ሰውነቱ በእናቱ አቅፍ እያለ ለሞት በቃ።

ሴቲቱ የእምነትን ዝናር የታጠቀች ብጽዕት ሴት ስለነበረች ማልቀስን አላስቀደመችም። እኛ ብንሆን ደረት ለመድቃት እንቸኩላለን። የእግዚአብሔር ሰዎች በጸሎታቸው ለችግሮች ሁሉ መቀረፍ ቁልፍ መሆናቸውን ስለምታውቅ ኤልሳዕን ለማግኘት አህያዋን አስጭና፣ ሎሌዋን አስከትላ ወደ ቀርሜሎስ ተራራ እየተጣደፈች ሄደች።

በሴትነት አቅሟ ተራራውን እየተቻኮለች ስትወጣ ቁልቁል ያያት ኤልሳዕ ነፍሷ እንዳዘነች ቢረዳ ተማሪው ግያዝን እሮጦ ደህንነቷን እንዲጠይቃት ላከው። ለተማሪው ብዙም መልስ ለመስጠት ያለፈለገችው ሱናማዊቷ ሴት በኤልሳዕ እግሮች ስር ተደፋች። እንዲህም አለችው “በውኑ ከጌታዬ ልጅን ለመንሁን? እኔንም አታታልለኝ አላልሁምን” ስትል ተሰጥቶ የተነፈገ ልጅ ማጣቷን በሀዘን ገለጸችለት በሕያው ነፍስህ እምላለሁ አልተውህም ብላ ወደ ቤቷ ሄደች የሕፃኑንም በድን በሰገነት አስገብታ በአልጋው ላይ አኖረችለት ኤልሳዕም ሰውነቱን ከሰውነቱ አድርጎ ተጋደመበት ያልተቋረጠ ጸሎት ለሕፃኑ ቢያደርስለት ሰውነቱ ሞቀ። ዐይኑም ተከፈተ ድህነትን አገኘ። ሱናማዊቷም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ልጅዋንም ይዛ ደስታ ባጥለቀለቀው ህይወት አመስግና ሄደች 2ነገ 4÷8-37።

የተጻፈ ሁሉ ልንመከርበት ለትምህርትና ለተግሳጽ ልብንም

ለማቅናት ስለሆነ ከዚህ ብዙ ልንማር ያስፈልጋል። 2ጢሞ 3÷16

የእግዚአብሔርን ሰው ኤልሳዕ የተቀበለች ሱነማዊት ልጅ ማጣቷ ወደማግኘት ተለውጦላታል። ተጠቀመች እንጂ አልተጎዳችም እኛም ቅዱሳንን፣ እመቤታችንን ብንቀበል፣ ወደልባችንም ሰገነት ብናስገባቸው ማጣታችን ወደ ማግኘት፣ ስብራታችን ወደ መጠገን ይለወጥልናል። ብንጠቀም እንጂ አንጎዳም።

<u>የልጇን ታሪክ አስቀየረች፦</u> ይህች ሴት የልጅን ሞት ያህል መራር ኃዘን ችግር ሲገጥማት ወደየትም አልሮጠችም በጸሎት የኃዘኗን ቀንበር ወደሚሰብርላት ወደ ነብዩ ኤልሳዕ አማላጅነት ተጠጋች እንጂ። ይህም እሩጫ ያለ ውጤት ተንኖ አልቀረም። የልጇን ሞት ወደ ህይወት በማስለወጥ ታሪኩን አስቀየረች። የቅዱሳን ጸሎት ታሪክ መቀየር ይቻለዋል። በኃጢአት ሙታን የሆንን እኛ ዛሬ በቅዱሳን ጸሎት ህያዋን ለመሆን ወደ ቅዱሳን ጸሎት አንጠጋ። ሕይወታች ይለወጣል።

የኤልሳዕ ሰገነት የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። በኤልሳዕ ሰገነት ውስጥ ሱነማዊቷ ሴት የልጇን መሻት /ልጅ/ አግኝታለች። ኋላም ቢሞትባት የሞተው ልጇ ተነስቶበታል። እንዲሁም በቤተክርስቲያን የሞቱ በሥጋ ወደ መ... መዕመናን የልባቸውን መሻት ያገኛሉ። በኃጢአት የሞቱ በሥጋ ወደ... ህያዋን ሆነው ተቀድሰው ይሄዳሉ። በአጠቃላይ በቤተክርስቲያን የችግራችን ሰንሰለት ሁሉ ይበጣጠሳል።

የሶሪያውም ንጉሥ ንዕማን ከለምጽ ሊነጻ ወደ ነብዩ ኤልሳዕ ቢመጣ በኤልሳዕ ሰገነት ደጃፍ /ውጭ/ ቆመ 2ነገ 5÷9 ውጭ መቆሙ ውስጥ አለመግባቱ የኤልሳዕ ሰገነት የቤተክርስቲያን የንዕማን ለምጽ የኃጢአትና የበደል ምሳሌ በመሆኑ ነው።

የኃጢአትን ለምጽ ሳይታጠቡ ቤተክርስቲያን መግባት ድፍረት እንደሆነ የሚያስረዳ ምስጢር ነው።

13. <u>ቤተሳይዳ</u>

በዕብራይስጥ ቤተሳይዳ የምትባል አንዲት መጥመቂያ ነበረች። በዙሪያዋ ቅጥር አምስት በሮችና እርከን ነበራት ቤተሳይዳ ለተአምራት እንግዳ አይደለችም ጎባጣው እየቀና፣ ዐይነ ስውሩ እየበራ፣ ሰውነቱ የሰለለው /paralyzed/ ሰውነቱ እየተመለሰለት፣ እንከሳው አየዳነ ይሸኛል። ባጠቃላይ ቤተሳይዳ በፈውስ ያጌጠች ናት። የእግዚአብሔር መለአክ መጥቶ ውኃውን ያናውጠዋል /ይባርከዋል/። ከበሽተኞች አንዱ ቀድሞ የገባ የናፈቀችው ጤንነቱን አግኝቷት ይመጣል። ቤተሳይዳ በብሉይ ኪዳን ዘመን ለመሥዋዕት የሚቀርቡ በጎች የሚታጠቡባት ስለሆነች ውኃው ንጹህ አልነበረም። ይሁን እንጂ በፀጋ የከበረ የፈውስ ኃይል በውስጧ የሞላ ነው። ጌታችን ወደ ቤተሳይዳ አመራ 38 ዓመት ሙሉ ከአልጋው ጋር ተጣብቆ ወገን ርቆት፣ ብቸኝነት ውስጡን አፍርሶት፣ ነገር ግን ቤተሳይዳን የሙጥኝ ብሎ በታውን ሳይለቅ የነበረው መጻጉን በዚህ ስፍራ ነው የዳነው። "አልጋህን ተሸክመህ ሂድ" ዮሐ 5÷2-8 ቤተሳይዳ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። ቤተሳይዳ ማለት የምህረት ቤት ማለት ነው። የኛይቱ ቤተሳይዳ /ቤተክርስቲያን/ የበደሉና ከእግዚአብሔር አንድነት የተለዩ በንስሐ ሲመለሱ ምህረትን የሚያገኙባት የምህረት ቤት ናት። የቤተሳይዳ አምስት በሮች የቤተክርስቲያን መሠረት የአምስቱ አዕማደ ምስጢር ምሳሌ ናቸው። አምስቱ እርከኖች የአምስቱ ጾታ ምዕመናን ምሳሌ ናቸው። "አዕርጉ፣ ወራዙት፣ አንስት፣ ካህናት፣ መነኮሳት" የብሉይ ኪዳን ሰዎች በጉን ለመሰዋዕት ከማቅረባቸው በፊት ቤተሳይዳ ወስደው ማጠብ ነበረባቸው። ዛሬም ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መስዋዕት አድርገን ከማቅረባችን በፊት በንስሐ ጥምቀት /በዕንባ/ መታጠብ ይኖርብናል። ሮሜ 12÷1 ንስሐ ባልጎበኘው ሕይወት የእግዚአብሔር ነኝ ማለት አይቻለምና። ቤተሳይዳ /ቤተክርስቲያን/ ተአምራት ርቋት አያውቅም መለአኩ መጥቶ ጸበሉን እንደሚባርከላቸው ዛሬም በመላእክት በጻድቃን በሰማዕታት በእመቤታችን ቡራኬ የከበሩ ጸበሎች በየአብያተ ቤተክርስቲያናቱና በየገዳማቱ አሉን። ብዙዎች መዳን በጌታ ብቻ ነው። ጸበል እንዴት ያድናል ትላላችሁ? ይላሉ የማያድንና አላስፈላጊ ቢሆን ኖሮ ጌታችን ቤተ መቅደሱን እንዳጸዳ የቤተሳይዳንም ቅጥር ባፈራረሰ ወይም በሽተኞችን ከዚያ አስወጥቶ አምስቱ በሮች ጠርቅሞ በዘጋው ነበር። አላደረገውም። በጸበል ውስጥ የማዳኑን ኃይል

<u>እያስተላለፈልን</u> በቅዱሳን በረከት ፈውሱን እንድንላበስ ያደረገ እርሱ ፈቅዶ ነውና። ስለዚህ ዛሬ በቤተክርስቲያን ያሉን ጸበሎች እግዚአብሔር ኃይሉን የሚገልጥባቸው ስለሆነ የተጠራጣሪዎቹን ቃል አንገዋለን በመጣል እኛ ግን እንዳንባቸው። እንደመጻጉ መሰል በሽተኞች የምህረት ቤት ቤተክርስቲያንን የሙጥኝ እንበል። ስፍራችንን /ሃይማኖታችንን/ አንልቀቅ እኛም ህመምተኞች ነንና። በሃጢያት ዓለም ውስጥ መመላለስ ህመም ነው። በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር አለመመላለስ ሽባነት ነው። ከዚህ ልንፈወስ ያስፈልጋል። የቤተሳይዳ ቅዱስ ውሃ በጎች ስሚታጠቡበት ንጽህ አልነበረም እንዲሁም የቤተክርስቲያን ጸበል ድፍርስ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔር ኃይል በውስጡ ነውና፤ ፈውስ አለው <u>እምነን</u> እንጠመቅበታለን። እንድንማለን። ማር 5÷36 "<u>እመን</u> ብቻ እንጂ አትፍራ"

14. <u>ገዳመ ቆረንቶስ</u>

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራውን በጾም ጀመረ። ከጥምቀት በኋላ የትም ሳይሄድ ገዳመ ቆረንቶስ ገብቶ አርባ ሌሊት አርባ መዓልት ጾሟል። ሰይጣን በሦስቱ አርዕስተ ኃጣውዕ ጌታችንን ፈትኖታል። በስስት፣ በትዕቢትና በፍቅረ ነዋይ። በትዕቢት ቢመጣበትም በትህትና፣ በስስት ቢመጣበትም በትዕግስት በፍቅረ ነዋይ ቢመጣበት በጸሊአ ነዋይ ድል አድርጎ ሰይጣንን አሳፍሮታል። እኒህ ሦስት የኃጢያት አውራዎች ለበደል ሁሉ ምንጭ ናቸው። እኒህን ድል ላደረገ በሰውነቱ ጸር አይጸናበትም። ማቴ 4÷1-11 ቤተክርስቲያን አማናዊት ገዳመ ቆረንቶስ ነች። በገዳመ ቆሮንቶስ ሰይጣን ድል እንደተመታ በቤተክርስቲያንም በጾም በጸሎት በስጊድ ሰይጣን ድል ተደርጎ ይወድቃል። በገዳመ ቆሮንቶስ ፈተና እንዳልታጣ በቤተክርስቲያን ፈተና አይታጣም። ይሁን እንጂ የገዳመ ቆሮንቶስ ባህታዊ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ አብሮን ስላለ በድል ያሰናብትልናል።

15. <u>ደብረ ታቦር</u>

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘጠኙን ደቀ መዛሙርት ከእግረ

ደብር ትቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሦስቱን (ጴጥሮስን፣ ያዕቆብን፣ ዮሐንስን) ይዞ ወደ ደብረ ታቦር ተራራ ወጣ። በዚያም የክብር ጸዳሉን፣ ብርሃናዊ ግርማውን ገለጠላቸው። ኤልያስ ከብሔረ ሕያዋን ሙሴም ከመቃብሩ መጥተው በቀኝና በግራ ቆመው የጌታችንን የባህሪይ አምላክነት መሰከሩ ማቴ 17÷1-8 ደብረ ታቦር የቤተክርስቲያን ምሳሌ ነች። ጌታ ግርማ መለኮቱን ለመግለጽ ደብረ ታቦርን እንደመረጠና በዚያ ክብሩን እንደገለጸ ቤተክርስቲያንም የእግዚአብሔር ክብሩና አድሀኖቱ የሚገለጽባት ነች። የብሉይ ኪዳን ነቢያትና የሐዲስ ኪዳን ሐዋርያት በደብረ ታቦር እንደተገኙ ቤተክርስቲያን የብሉይም የሐዲስም ቅዱሳን የስማቸው መታሰቢያ ይገኝባታል። ቤተክርስትያን በነብያትና በሐዋርያት መሠረት ላይ ታንጻለችና። ኤፌ 2÷20 አንድም ቤተክርስትያን ብሉይን ከሐዲስ አስማምታ ለማስተማሯ ምሳሌ ነው።

በደብረ ታቦር ታራራ ምስጢረ ሥላሴ እንደተገለጠ በቤተክርስትያንም የሥላሴ አንድነት ሦስትነት ሲነገር፣ ሲወደስ፣ ሲቀደስ ይኖራል።

ደብረ ታቦር ከመሬት ከፍ ያለ ነው /ወደ ሰማይ/ ቤተክርስቲያንም መሠረቷ በምድር ሲሆን ራሷ /ክርስቶስ/ ሰማያዊ ነው። የቤተክርስቲያን መስራቾች ቅዱሳን የተመረጡት ከምድር /ከዓለም/ ሲሆን ክብራቸው ግን ምድራዊ ያይደል ሰማያዊ ነው።

16. <u>የእንግዶች ማደሪያ</u>

እራሱን በትዕቢት ዙፋን ሊያስቀምጥ የወደደ አንድ ፈሪሳዊ ጌታችንን ሊፈታተነው ወደ ባልንጀራዬ ማነው ሲል ጠየቀው ጌታችንም በምሳሌ ሊያስተምረው ፈቅዶ እንዲህ አለው አንድ ሰው ከእየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከል ትተውት ሄዱ ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶም ገለል ብሎ አለፈ እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ስፍራ መጣና አይቶት ሸሸ እንዲሁም አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቁስሎቹ ላይ አፈሰሰ ቁስለኛውን በራሱ አህያ ላይ አስቀምጦ ወደ እንግዶች ማደሪያ ወሰደው በዚያም ሌሊት ለአገልጋዮቹ

ሁለት ዲናር አውጥቶ ሰጣቸውና ጠብቁት እኔ እስክመጣ ከዚህ በላይ የምትከፈሉትን እኔ እከፍላችኋለሁ አላቸው። በዚያም ከስብራቱ ተጠግኖ ከበሽታው ተፈወሰ ሉቃ 10÷29-36 ምሳሌ ነው ደብዳቢ ወንበዴዎች የአጋንንት፣ ተደብዳቢው አዳም በበረሃ ወድቆ ያነሳው ደጉ ሳምራዊ መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ነው።

ምሳሌ ምሳሌ "ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎች እጅ ወደቀ" ክርስቲያኖች በኢየሩሳሌም ከምትመስለው ቤተክርስቲያን ወጥተው በኢያሪኮ ወደምት መስለው ዓለም መሄድ ሲጀምሩ ወንበዴዎች አጋንንት በኃጢያትና በክህደት ፍላጻ ወግተው ያደሟቸዋል። በበደል ስብራት ይጥሏቸዋል ሆኖም ግን ልጆቹ ጠፍተው እንዲቀሩበት የማይሻ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እንግዶች ማደሪያ /ወደ ቤተክርስቲያን/ በይቅርታው ተሸካሚነት ያመጣቸዋል። በዘይትም / በሥጋ ወደሙ/ ቁስላቸውን ይጠግናል ለአገልጋዮቹ ለካህናትም የድካማቸውን ዋጋ ሰጥቶ በኃጢያት የታመመውን እንዲፈውሱት ያዕ 5÷14-15 አደራ ይላቸዋል። በሽተኛው ከህመሙ ይፈወሳል። ቤተክርስቲያን ህሙማን ሥጋ ህሙማን ነፍስ የሚፈወስባት የእንግዶች ማደሪያ ነች።

17. ታንኳ /ጀልባ/

ብዙ ጊዜ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጀልባ ላይ እየተመላለሰ ተማሪዎቹን ያስተምር ነበር። ማር 4÷36 በዚህ ም... እንደምንረዳው ጌታችን የተቀመጠባት መርከብ ከባድ አውሎ ነፋስ ያናውጣት ነበር። ደቀመዛሙርቱ በጭንቀት ተዋጡ ጌታችንም እንቅልፍ የሚስማማው ሥጋ መልበሱን ለማጠየቅ አንቀላፍቶ ነበር። እግዚአብሔር በመለኮቱ አያንቀላፋም "ኖላዊ ትጉህ ዘኢያነውም" የማይተኛ ቸር ጠባቂ ነውና መዝ 120÷21-4 መርከቧ ትናወጥ እንጂ ደቀመዛሙርቱ ከመርከቧ እንወጣ አላሉም እንዲያውም ማዕበሉን ጸጥ ወደሚያደርገው ጌታ "ሊቅ ኢየ ኃዝነከኑ እንዘ ንመውት" መምህር ሆይ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት እርሱም ተነሥቶ ማዕበሉን ገስጸው ጸጥ አለ።

ጀልባዋ የቤተክርስቲያን ምሳሌ ናት። ማዕበሉ ፈተና ነው። ጌታ ያለበት ጀልባ ማዕበል ነበረባት። በቤተክርስቲያን ጌታችን ከቅዱሳን ጋር

ስላለባት ፈተናዋ ብዙ ነው። ይሁን እንጂ አትሰጥምም ማዕበሉን የሚገስጽላት ጌታ በውስጧ ነውና። በዮዲት 40 ዘመን መሉ፣ በግራኝ መሐመድ 15 ዓመት፣ በጣሊያን 5 ዓመት በማዕበል ተናወጠች ግን አልሰጠመችም። ዛሬም ተጠራጣሪዎች ማዕበል /ፈተና/ ይሆኑባታል ግን አትፈርስም በጽኑ መሠረት ላይ ነችና ማቴ 16-18

የእኛ ቤተክርስቲያን በ.ጊዜው ፈታኝ የሚነሳበት በውስጧ እውነት የሆነ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላለባት ነው። ዓለም የእውነት ጠላት ነችና።

ደቀመዛሙርቱ ማዕበል ስለመጣ ተስፋ ቆርጠው ከጀልባዋ አልወጡም። ቢወጡም ከሞት አይተርፉምና። ይልቁንስ ወደ አምላካቸው መጮኸን መረጡ የኃጢአት ሁሉ ቁንጮ ተስፋ መቁረጥ ነው። ዛሬ ብዙዎች መከራ መስቀሉን መታገስ ተሰቅቀው ቤተክርስቲያን ስትፈተን እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንጹህ ነኝ ብለው ከቤተክርስቲያን የሚወጡ የሰላም ቀን ክርስቲያኖች ብዙ ናቸው። በሰላም ጊዜ ሁሉም አርበኛ ነው ይልቁንስ ማዕበሉ ሲበረታ ወደ ፈጣሪአችን እንጬኸ አርሱ ማዕበሉን ጸጥ የሚያደርግበት ክንዱ የታመነ ነው። የቅዱሳን አምላክ እግዚአብሔር በመከራ ጊዜ የምንጸናበትን የእዮብን ጽናት እንዲያድለን ፈቃዱ ይሁንልን። አሜን!!

18. ቀራንዮ

ቤተክርስቲያን አማናዊት ቀራንዮ ነች ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትን በምድረ ቀራንዮ ፈጽሟል። ሥጋውን ቆርሷል ደሙን አፍስሷል አጋንንትን በነፍስ አውታር በእሳት ጅንደር አስሮ አስጨንቋቸዋል ቀራንዮ ህይወት የተገኘባት የህይወት ምንጭ ናት። ቀራንዮ እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያም ዮሐንስና ቅዱሳት አንስት በሐዘን ተውጠው የከበቧት ቅድስት ስፍራ ነች።

ቤተክርስቲያን ቀራንዮ እንደመሆኗ ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ይፈተትባታል የህይወት ምንጭ እንደመሆኗ በእውነት የተጠሙት ሁሉ የመዳን ጥማቸውን ይወጡባታል፤ አጋንንት ይታሰርላቸዋል። ቤተክርስቲያን ቀራንዮ ነችና ቅዱሳን ይገኙባታል መታሰቢያቸውም

ይደረግባታል።

ቀራንዮ ማለት የራስ ቅል ማለት ነው። በአንዳንድ የጌታችን ሥነ ስቅለት ስዕል ላይ ከጌታችን እግረመስቀል ስር የአዳምን አጽም /የራስ ቅል/ እናያለን አዳም በሥጋ ቀራንዮ ሲቀበር በነፍሱ በሲኦል ርደተ መቃብር ውስጥ ነበር። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በርደተ መቃብር ርደተ ሲኦል ያገኘው ልጁ አዳምን ከገባበት የሞት አዘቅት ለማውጣት የመጣ ነውና። በመቃብሩ ላይ በሃኑቱን ፈጽሟል። እናም ክርስቲያኖች ነፍሳችን ከሥጋችን ስትለይ በቀራንዮ /ቤተክርስቲያን/ የቀብራችን ሥነ ሥርዓት የሚፈጽመው ከዚህ በመነሳት ነው። አፈሯም በጌታችን ደም ተቀድሷልና። የአዳም ሥርዓተ ቀብር ቀራንዮ ተፈጽሟል።

19. <u>ጽርሐ ጽዮን</u>

ይህ ቅዱስ ስፍራ የማርቆስ እናት የማርያም ቤት ነው።

የዚህ ቤት አገልግሎት ከዕርገት በኋላ ኃይልን እስክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ ሉቃ 24÷49 በተባሉት አምላካዊ ቃል መሠረት በኢየሩሳሌም ባለችው የማርያም ቤት በጽዮን አዳራሽ በታቦት የምትመሰል እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምን ከመሃል አድርገው በጸሎት ሲተጉ ድንገት እንደሚነጠቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምጽ መጣ ተቀምጠውበትም የነበረውን ቤት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ ሞላው። እንደ እሳት የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዱ ያደረ መንፈስ ቅዱስ ምስጢርን አናገራቸው። ሉቃ 22÷7-23 ሐዋ 2÷42 ሐዋ 2÷1

የመጀመሪያዋ የሐዲስ ኪዳን ቤተክርስቲያን ጽርሐ ፅዮን ናት። በጽርሐ ጸዮን የሞላ የመንፈስ ቅዱስ ሀብት ዛሬም ቤተክርስቲያንን አይለያትም። ሐዋሪያት የትም ሄደው ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ሊሰከሩ የቻሉት እመቤታችንን ከመሃል አድርገው በጽዮን አዳራሽ በተቀመጡበት ጊዜ ነው። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሌለችበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ አይወርድምና። መንፈስ ቅዱስን የሚሻ እመቤታችንን መጠጊያ አድርጎ በጽዮን አዳራሽ /በቤተክርስቲያን/ ጸንቶ መቀመጥ አለበት። ቤተክርስቲያን የመንፈስ ቅዱስ ግምጃ ቤትና የምስጢር መፍለቂያ ምንጭ ናትና።

በንብዝና ወረታቸው ላይ ላሉ ክርስቲያን
<u>ወገኖቼ የማስተላልፈው መልዕክት</u>

- ቸኩልና ስሜታዊ አትሁን። ለእኩይ ስሜት ሳትንበረከክ ክርስቲያናዊ ዓላማህን ከዳር ለማድረስ ትጋ። ቸኩለህ የገነባኸው ሁሉ መሠረት ያጣ ሥራ ሆኖ ሊፈርስብህ ይችላልና። ስለዚህ ከሁሉ አስቀድመህ እርጋታን ገንዘብ በማድረግ ለምትሠራው ሥራ ፈቃደ እግዚአብሔርን ጠይቅ። እግዚአብሔር ያነጸው ሕንፃ ሁሉ አይፈርስምና።

- ሁሌም ለእውነት ቁምላት። ሐሰት እንደ ውቅያኖስ ግዛቷን ብታንሰራፋ ጤዛ በምታክል እውነት ልታሸንፋት ትችላለህ። የእውነት ጉልላት ክርስቶስ ነውና ዮሐ 14÷6 ያንተን እውነተኛነት እንደበትህ ሳይሆን ሥራህ ቢገልጸው ይመረጣል። ከሰዎች ፍቅርን አተርፋለሁ ብለህ እነርሱን ለማስደሰት ውሸትን አትናገር እውነትን ተናገር ሰነፎች ይጥሉህ።

- ሁሌም እኔ ብቻ ካልተናገርኩ አትበል። ማዳመጥ ከሰነፎች መስዋዕት እንደሚበልጥ እወቅ። 1ኛ ሳሙ 15÷22 ይልቁንም መንፈሳዊ ሰው ለመናገር የዘገየ ለመስማት የፈጠነ ጠቢብ መሆኑን አትርሳ። በአፈ ጮሌነትህ ለመከበር አትሻ። የአንተ የክብርህ ጉልላት አፍህ ሳይሆን ሥራህ ሊሆን ይገባል።

- እኔ ያልጋገርኩት እንጀራ ከምጣድ አይወጣም አትበል። ብዙዎች እነርሱ እጃቸውን ያላስገቡበት ሥራ አይጥማቸውም። ይህ እራስን ማምለክ ይባላል። አንተ ግን ወሳኙ እኔ ነኝ ሳትል ትህትናን ገንዘብህ አድርጋት።

- ወደ ቤተእግዚአብሔር ስትገዝ የምታስቀረው የአካልህ ክፍል አይኑር። የሎጥ ሚስት አካሏ ወደ ዞአር ተራራ እየሄደ ልቧ እስራኤል ከግብጽ ይውጡ እንጂ ልባቸውን ግብጽ ስላስቀሩ በበረሃ ቀርተዋል። ስለሆነም ልብህን አስቀድመህ ለፈጣሪ ስጥ።

- በሕይወት ውስጥ ደስታና ሀዘን ሊፈራረቁ ይችላሉ። ታዲያ

ሁለቱንም በመጠኑ አድርጋቸው።

- በሆነ ባልሆነው ውዳሴ ከንቱን የምትወድ አትሁን። ከሰዎች ሽንገላ ፈቀቅ በል። ከንቱ ውዳሴ ከልጅነትህ ጀምሮ የደከምክለት የክርስትና ሕይወትህን ድባቅ ይመታብሃል። አንተም እርባና ቢስ ትሆናለህ። አንዳንዶች በአገልግሎታቸው ሁሉ ካልተመሰገኑ ይከፋቸዋል። የሚያገለግሉትን ሰለማያውቁና ሁሉን ከሥጋውያን የሚጠብቁ ሥጋዊያን በመሆናቸው ነው።

- ምናልባት ያወቅህና የመጠቅህ መስሎ ሊታይህ ይችላል። ነገር ግን አላዋቂነቱን የሚያውቅ ሰው ብስለቱ በዚህ ይለካል። ስለዚህ የሌሎችን ምክርና ትምህርት አያስፈልገኝም አትበል። እግዚአብሔር ጆሮህን ከሰጠኸው ስብራትህን የሚጠግንበት ቃሉን ሳይነግርህ አይቀርም። ትንሿ እውቀትህ የትዕቢት ፈረስ ሆና የሽምጥ ይዛህ ገደል እንዳትጥልህ በትህትና ልጓምነት አጥብቀህ ያዛት። መጽሐፍ ቅዱስ ያወቅህ ቢመስልህም ከማንበብ አትቦዝን። መጽሐፍ ቅዱስ ወዳጅ የሆነ ሰው የራሱን ምንነት አንጥሮ ያውቀዋልና።

- ክርስቲያን መሆንህን አትርሳ በይሉኝታ ገመድ ተሸብበህ የኃጢያት ተባባሪ አትሁን

- የሰዎችን መልካም ሥራ ብቻ አድናቂ አትሁን። አንተም የሥራ ተቋዳሽ ሁን። በሰዎች ሥራ ብቻ ከምትደሰት ይልቅ አንተም በሥራህ ውጤት ደስታን ለመፍጠር ሞክር።

- በሠራኸው መንፈሳዊ ሥራና አገልግሎት አትመካ። ይልቁንም የሥራው ባለቤት እግዚአብሔር መሆኑን አውቀህ ምስጋናህን አበርክት "ያለ እኔ ምንም ምን ልትሠሩ አትችሉም"ብሏልና ዮሐ 15÷5

- መንፈሳዊነትን የስንፍናህ ሽፋን አታድርገው። ብዙዎች የማንበብና የመሥራት ልምድ ሲያጡ በመንፈሳዊነታቸው አሳብበው መንፈሳዊነትን የድንቁርና ምልክት ያደርጉታል። ይህ ነው "ትልቁ ኢክስ"

- ሥራና አገልግሎትህን በጣም አክብረህ ያዘው። ብትችል ከሆድ ይልቅ ለአለገልግሎትህ ቦታ ስጠው። ጌታችን ደቀመዛሙርቱ ሀብስት ይዘውለት መጥተው ብላ ብለው በለመኑት ጊዜ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው" ብሎ ወደ እርሱ የመጡትን የሰማርያ ሰዎች ማስተማሩን የቀጠለው ለዚህ ነውና። ዮሐ 4÷34 ደቀመዛሙርቱ ካመጡለት መብል ይልቅ የሰዎች መዳን እርሱን ያጠግበዋል። አንተም ሕይወት በሚያሰጠው አገልግሎትህ የምትጠግብ ሁን እንጂ ሰዎች በሚያቀርቡልህ ስጦታ ብቻ የምትረካ አትሁን።

- ዓለም እንደ አበባ ፈኪታ ልትታይህ ጠረኗም ሊስብህ ይችላል። አንተም ጸዳሏ ማርኮህ ወደ እርሷ ዘንበል ልትል ታኮበክብ ይሆናል። ነገር ግን አስተውል "ከአበባ ሥር እሾህ መኖሩን አትርሳ"ፍቅሯን ብለህ ስትጠጋት በእርኩሰት እሾኳ ወግታ ታደማሃለች። በደም የተበከለ ሰውነትህን እርሷው ትጸየፍሃለች። ከሁለት ያጣ ሆነህ ትቀራለህ። ይልቁንስ እሾህ ከሌለበት ከመንፈሳዊ አበባ ጣፋጭ ምርትን የሚያመርት ትጉህ ንብን ምሰል።

- መድኃኔዓለም ክርስቶስ ሰዎች በገሊላ ተሰብስበው በሥልጣን ኮርቻ ላይ ሊያስቀምጡት ሲሹ እርሱ ግን ወደ ተራራ ፈቀቅ አለ /ሸሸ/ ዮሐ 6÷15 አንተም የእግዚአብሔር ልጅ ነህና ብትችል ሥልጣንን ሽሽ። በሥልጣን ለመክበር አትሻ ሰዎች በሥልጣንህ ቢያከብሩህም የፍራቻ ክብር እንጂ እውነተኛና ከልብ የመነጨ ክብር እንዳልሆነ እወቅ።

- ዝናና ስምን ለማትረፍ ብለህ የምትሠራው አንዳች አይኑር። ይህንንም ሰራሁ አትበል። አንተ እውነትን ሰርተህ ካለፈክ ሥራህ እራሱ አፍ አውጥቶ ይናገርልሃል።

- "ልትናደድ" ትችላለህ በንዴት እረመጥ ውስጥ ሆነህ ውሳኔ ባትወስን መልካም ነው። እራስህን እስክታውቅና ውሳኔህም ከእግዚአብሔር እንዲያጣላህ አንተነትህን በጸሎት አረጋጋው። ስትጸልይ የግብር ይውጣ /አውተፍትፈህ/ አትጸልይ።

የምትነጋገረው ከማን ጋር እንደሆነ እወቅ።

- ሰዎች ለመንፈሳዊ ሕይወትህ ፈተና የሚሆኑበት ጊዜ ይኖራል። በዚህ ጊዜ በኃይል ለመርታት እና ለማሸነፍ እንዳትሞክር። ሰው ካወቀበት እንኳን ሰብአዊ ፍጥረትን ይቅርና እግዚአብሔር እንኳን የተሸነፈበት ትልቅ ኃይል አለ። እርሱም "ፍቅር" ነው። ፍቅር ኃያሉን አምላክ እንኳን አሸንፎ እስከሞት አድርሶታል። "ፍቅር ጉልበተኛ ነው"አንተም ፍቅርህን ለሰዎች አትንፈግ። ሰውን በፍቅር ካሸነፍክ የአሸናፊዎች አሸናፊ ትባላለህ። ለሚወድህ ብቻ ሳይሆን የሚያጠቁህንም በፍቅር ጸልይላቸው።

- ሰዎች ለምታደርጋቸው በጎ ነገር ሁሉ "ለራሱ ጥቅም ሲል ነው" ብለው ቅኝቱ ባልተስተካከለ አነጋገራቸው ሊፈርዱብህ ይችላሉ። አንተ ግን አላማህን አውቀህ ጽና።

- በየትኛውም አጋጣሚና ሥፍራ ወገንህ በችግር ቆስሎ ልታየው ትችላለህ። ያንን ሰው አንተ ስለማታውቀው እግዚአብሔር አያውቀውም ማለት አይደለም። ይልቁንም አንተም እርሱም የአንድ አባት የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችሁን አስብና ብትችል እንደ ሳምራዊው ሁን ሉቃ 10÷29-37 ለመርዳት አቅም ከሌለህ በጸሎትህ እርዳው እንጂ የሞት ጣር ድምፁን እየሰማህ ጆሮ ዳባ ብለህ አትለፍ። "ይህ ክርስትና ሊሆን አይችልም"።

- ምን እሆናለው አትበል። ሰይጣን የማይተኛልህ ባለጋራህ ነው። ለምሳሌ ቤተክርስቲያን ስላልሄድኩ፣ መናፍቃን ጉባኤ ብሄድ፣ መዝሙራቸውን ብሰማ ... ወዘተ ምን እሆናለሁ አትበል። "አሰበው" መናፍቃን ጉባኤ ሄድክ ግን ወፍጮ ቤት የገባ ሰው ዱቄት ሳይነካው ይመጣል? አንተም አንድ ነገራቸው ሳይነካህ አትመጣም። ብዙ ጊዜ እንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች ናቸው ለቤተክርስቲያን የውስጥ ሆድ ቁርጠት የሚሆኑባት። ስለዚህ "ውሎህን እወቅ"።

ምንጭ መጽሐፈ ምዕዳን
"ይትባረክ እግዚአብሔር አምላክ አበዊነ"

ዋቢ

- መጽሐፈ ምዕላድ
- መጽሐፈ ዕቀበኒ
- መጽሐፈ አርድኢት
- ክብረ ነገሥት
- መጽሐፈ ምስጢር .... ኢትዮጲያዊው አባ ጊዮርጊስ
- ዘጋስጫ /ስንክሳር/
- አክሲማሮስ.............................. ኤጲፋንዮስ ዘቆጵሮስ /ስንክሳር በአማርኛ/
- መጽሐፈ ምዕዳን .... ቅዱስ ጢሞቲዮስ ፓትርያርክ
- ዘግብጽ
- ገድለ ተ/ሃይማኖት
- ኮኩሐ ሃይማኖት .... በመለአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ 1949ዓ.ም አ.አበባ
- መለከተ መጽሔት................ አምስተኛ አመት ቁ. 6 1990 ዓ.ም አ.አበባ
- ሃይማኖተ አበው................ 1982 ዓ.ም አዲስ አበባ
- ነፀብራቅ መጽሔት .... ቁ.4እና5 1985ዓ.ም አዲስ አባባ
- የሐዋርያት ሥራ .... አድቨርሲስ ትርጓሜ በእንግሊዘኛ ቋንቋ
- ውዳሴ ማርያም ትርጓሜ .... 1983 ዓ.ም አዲስ አበባ
- መዝሙረ ዳዊት ንባብና ትርጓሜ .... 1979 ዓ.ም አ. አበባ
- ቅዱስ ወንጌል ንባብና ትርጓሜ .... 1985 ዓ.ም አ አበባ
- ወርቃማ አባባሎች .... ከጌትነት አማረ 1989 ዓ.ም አ.አበባ